# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

### የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር


# የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓት ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ከፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንጻር


በ

ሰራዬ እንዳለው



ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ከዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ

# ከፎክሎር ከዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንጻር

በ


ስራዬ እንዳለው


ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ- ግብር


# የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓት ከዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ

# ከፎክሎር ከዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንጻር


በ

ስራዬ እንዳለው


ለአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር መርሐ- ግብር ኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት

ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት


አማካሪ፡- ባይለየኝ ጣሰው (ዶ/ር)



ሰኔ 2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ

# ከፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንጻር

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| አማካሪ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ባይለየኝ ጣሰው (ዶ/ር) | | 2/11/05 |
| የውስጥ ፈታኝ | | 02/11/05 |
| የውጭ ፈታኝ | | 02/11/05 |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ILS LIBRARY
ADDIS ABABA

# መታሰቢያነቱ

ለውድ እህቴ ለ መልካም እንዳለው ይሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

በመጀመሪያ ርዕስ ከመጠቆም ጀምሮ ሳይሰለቹ እያንዳንዱን የጥናቴን ክፍል በማየት አስተያየትና ማስተካከያ ለሰጡኝ አማካሪዬ ለዶክተር ባይለየኝ ጣሰው ምስጋናየ ላቅ ያለ ነው፡፡ ለምርምሬ ገንቢ አስተያየት በመስጠት እንዲህ ያለ ምርምር እንድሰራ ስላደረጉኝ በድጋሚ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመቀጠል በፍኖተ ሰላም አካባቢ ለሚኖሩ መረጃ ሰጭዎቼ፡- ተዝቆ ከማያልቀው እውቀታችሁ የምፈልገውን ያህል በፍቅር ስለሰጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ መልዓከ ጥበብ መሪጌታ ስሜነህ አበበ እና ወ/ሮ ድንቃየሁ አለሙ ከእናንተ ያገኘኋቸው ቁልፍ መረጃዎች ጥናቴ ሚዛን እንዲደፋ አድርገውልኛል፡፡ ከልብ የመነጨ ምስጋናየ ባላችሁበት ሁሉ ይድረሳችሁ፡፡ ለሁላችሁም ረጅም እድሜና ጤና ይስጥልኝ፡፡ እንዲሁም ለፍኖተ ሰላም ከተማ እና ለጃቢ ጠህናን ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰራተኞች ስለረዳችሁኝ ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ የመስክ ረዳቶቼ ጌታቸው እና አዱኛ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ልዩ የትምህርት እድል ከመስጠት ጀምሮ ለጥናቴ የሚሆን ገንዘብ እስከመበጀት ድረስ ረዳቶኛልና አመሰግናለሁ፡፡

አባቴ አቶ እንዳለው ውበቴ፣ እናቴ ወ/ሮ ቦሰና አለሙ ሳትሰለቹ ያደረጋችሁልኝ ድጋፍ ለምርምሬ መጠናቀቅ ትልቁን ድርሻ አበርክቷል፡፡ እናንተ ባልኖራችሁበት የትምህርት አለም እንድኖር ስላደረጋችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ፤ ሁሌም ኑሩልኝ፡፡ ወንድሞቼ ዶ/ር አለኸኝ ውበቴ፣ ጌታሰው እንዳለው፣ መንግስቴ እንዳለው እና በላይ ዘለቀ ካደረጋችሁልኝ የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ አይዞሽ! የሚለው ወንድማዊ ድጋፋችሁ ብርታት ሆኖኛልና እጅግ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡ እህቶቼ አዳሜ እንዳለው እና ብርቱካን እንዳለው በስራዬ ሁሉ ስለደገፋችሁኝ አመሰግናችኋለሁ፡፡ እሎኛየ እሸቴ ጥናቴ የአንተ የሚያበረቱ ምክሮች፣ ሀሳቦች፣ አስተያየቶች ውጤት ነው፡፡ በተለይ "ጎበዝ፣ ጠንካራና ጥበበኛ ሴት ሁሉንም ማሸነፍ ትችላለች፡፡" የምትላት ምክርህ ህይወቴን ለውጣዋለች፡፡ ይኸው ቃልህ ብርታት ሆኖኝ ምርምሬ ተጠናቀቀ፡፡ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

የክፍል ጓደኞቼ በጥናቴ ዙሪያ የሰጣችሁኝ አስተያየትና ያደረጋችሁልኝ ድጋፍ በጥናቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ሁላችሁንም በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት "የህይወት ዘመን ሁደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ከዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ" የሚል ርዕስ አለው፡፡ በዚህ ርዕስ ላይ ምርምር የተካሄደው የተጠቀሰው አካባቢ ማህበረሰብ ለዋና ዋና የህይወት ዘመን ሁደት ሽግግር ደረጃዎች ያለውን አመለካከት በስነ-ቃሉ አማካኝነት እንዴት እንደሚገልጽ ማወቅ፣ የህይወት ሽግግሮችን ምክንያት በማድረግ የሚከናወኑ ክብረ በዓላት፣ አከባበር በሚከወኑበት አውድ ተገኝቶ መረዳት፣ በጉዳዩ ላይ ጥናት ባለመካሄዱ የተፈጠረውን የእውቀት ክፍተት ማጥበብ የሚሉ የምርምር ፕሮብሌሞችን መነሻ በማድረግ ነው፡፡

እነዚህን የምርምር ፕሮብሌሞች ለመመለስ ዋና ዋና የህይወት ሽግግር ደረጃዎች ለማህበረሰቡ ምንድን ናቸው? የአከባበር ስርዓታቸው እንዴት ይከናወናል? የሚሉ ዋና ዋና ጥያቄዎች ተዋቅረዋል፡፡ እነዚህን የምርምር ጥያቄዎች በመመለስ የህይወት ሽግግር ደረጃዎችች ክብረ በዓል እና በአከባበር ሂደታቸው ውስጥ የታዩ ትእምርቶችና ባህላዊ አገላለጾች በተከወኑበት አውድ መሰረት በመግለጽ፣ በመተንተን እና በመተርጎም የፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ በሽግግሮች ዙሪያ ያለውን አመለካከት ማሳየት ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት ከዚህ በፊት ትኩረት ተሰጥቶት ስላልተጠና የተለያዩ ምንጮችን መጠቀም አጅግ አስፈላጊ ነበር፡፡ በመሆኑም ቤተ መጻህፍት እና የመስክ ስራ ላይ በማተኮር በንባብ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካኝነት መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣ አውዳዊ ትንተና በማካሄድ እና በመተርጎም ከላይ የተጠቀሱትን የምርምር ፕሮብሌሞች ለማሟላት ተሞክሯል፡፡

የፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ በህይወት ዘመን ሁደት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ የሚያከናውናቸው ክብረ በዓላት ከአምልኮ ስርዓት ጋር የተያያዙ መሆናቸው፣ ከመልካም እሴቶች ጋር የተቆራኙ መሆናቸው፣ የማህበራዊ ግንኙነት ማጠንከሪያ መሆናቸው፣ ለሽግግር ደረጃዎች ያላቸውን አመለካከት የሚገልጹባቸው መሆናቸው፣ ግላዊ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ማሳያ መሆናቸው እና ስነ-ልቦናዊ እርካታ ማግኛ መሆናቸው ከመረጃ ትንተናው የተገኘው ውጤት አመላክቷል፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና……………………………………………………………………………i

መታሰቢያነቱ……………………………………………………………………ii

አጠቃሎ………………………………………………………………………iii

ምዕራፍ አንድ ……………………………………………………………1

1 መግቢያ ……………………………………………………………………1

1.1 የጥናቱ አቀራረብ……………………………………………………1

1.2 የጥናቱ ዳራ ……………………………………………………………2

1.3 የምርምር ፕሮብሌሞች ……………………………………………4

1.4 የምርምር ጥያቄዎች…………………………………………………6

1.4.1 የምርምሩ ዋና ጥያቄ ………………………………………………6

1.4.2 ዝርዝር ጥያቄዎች …………………………………………………6

1.5 የጥናቱ ዓላማዎች …………………………………………………6

1.5.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ …………………………………………………7

1.5.2 ዝርዝር ዓላማዎች…………………………………………………7

1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ ……………………………………………………7

1.7 የጥናቱ ወሰንና ውስንነት …………………………………………8

1.8 የአጠናን ዘዴዎች …………………………………………………10

1.8.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ……………………………………10

1.8.1.1 ምልከታ …………………………………………………………10

1.8.2.2 ቃለ መጠይቅ……………………………………………………14

1.8.1.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት ………………………………………16

1.8.2 የመረጃ ትንተና ዘዴ……………………………………………17

ምዕራፍ ሁለት ....................18
ክለሳ ድርሳን ....................18
2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ....................18
2.1.1 የፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ምንነት ....................19
2.1.2 የአውድ ተኮር ጥናት መታገጊያ ....................21
2.1.3 የክብረ በዓል ምንነት ....................25
2.1.4 የክብረ በዓል ባህሪያት ....................27
2.1.5 የክበራ ሽግግር ደረጃዎች ....................28
2.1.5.1 መነጠል ....................28
2.1.5.2 ሽግግር ....................29
2.1.5.3 አዲስ ማንነት ማግኘት ....................30
2.2 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ....................30
ምዕራፍ ሶስት ....................36
3 የጥናቱ ሰላም አካባቢ ዳራዊ መግለጫ ....................36
ምዕራፍ አራት ....................39
4 መረጃ ትንተና ....................39
4.1. የልደትና ክርስትና ስርዓተ ክዋኔ ....................39
4.2 የሰርግ ስርዓተ ክዋኔ ....................48
4.2.1 የሰርግ ክብረ በዓል ላይ የሚከወኑ ቃል ግጥሞች ....................56
4.2.2 የሰርግ ስነ-ስርዓት ማሳረጊያ ምርቃቶች ....................61
4.3 የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ....................65
4.3.1 በለቅሶ ስነ-ስርዓት የሚከወኑ ቃል ግጥሞች ....................70
4.3.2 በለቅሶና በተዝካር ስነ-ስርዓት ማሳረጊያ የሚቀርቡ ምርቃቶች ....................74
4.4 የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮች ክብረ በዓል መዋቅር ....................76

ምዕራፍ አምስት ........ 82
5 መደምደሚያ ........ 82
5.1 ማጠቃለያ ........ 82
5.2 የምርምር ግኝቶች ........ 83
5.3 የምርምር ግኝቶች ጠቀሜታ ........ 85
ዋቢ ጽሁፎች
አባሪዎች

# ምዕራፍ አንድ

## 1 መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ አቀራረብ

ይህ ጥናት በዋናነት "የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ከፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንጻር" የሚል ርዕስ አለው፡፡ የሰው ልጅ ህይወት ዘመን ዑደቶች ማለትም የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ስርዓት ሲከወን ያለውን አጠቃላይ ገጽታ ከመግለጽም ባሻገር ለማህበረሰቡ ምን ማለት እንደሆኑ፣ እንዲሁም በስነ-ቃሎቻቸው አማካይነት እንዴት እንደሚገልጿቸው ያሳያል፡፡ ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ ምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የምርምር ፕሮብሌሞች[1]፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አላማዎች እና የአጠናን ዘዴዎች የቀረቡበት ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት እና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት የሚሉ ርዕሶችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ማለትም የፍኖተ ሰላም አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ የቀረበበት ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ አራት የመረጃ ትንተናን የያዘ ሲሆን በገለጻ፣ በትረካ እና በትርጉማ ላይ ተመስርቶ ቀርቧል፡፡ ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ፣ የምርምር ግኝቶች እና ጠቆሚታ እንዲሁም ዋቢ ጽሑፎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡

የጥናቱ አቀራረብ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በጥናቱ በተቻለ መጠን የአማርኛ ቋንቋን አቻ ትርጉም ያላገኘሁላቸውን ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦችን ደግሞ እንዳለ የአማርኛ ቋንቋ ፊደልን ለመጠቀም ሞክሬያለሁ፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ ቋንቋዎችን ቀላቅሎ መጠቀም ተገቢ ካለመሆኑም በተጨማሪ አንባቢን እንዳያሰለች በማሰብ ነው፡፡ እንዲሁም ከሌላ ቋንቋ በቀጥታ የተወሰዱ ቃላት፣ ጽንሰ ሀሳቦች እና ንድፈ ሀሳቦች በመገኛ ቋንቋቸው በግርጌ ማስታዎሻ ቀርበዋል፡፡ ምክንያቱም የትርጉም መዛባት ሊፈጠር ስለሚችል አንባቢ እዚያው ላይ እንዲያገናዝብ የሚያስችል በመሆን ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱን የሚያነብ ሰው እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ በቅድሚያ አሳውቃለሁ፡፡

[1]ፕሮብሌም፡-በብዛት ችግር የሚለውን ቃል ቢተካም በዚህ ጥናት ጉዳዩን ስለማይገልጸው እና በብዛት ወደ አማርኛ የገባ ስለሆነ በቀጥታ ተጠቅሜበታለሁ፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዳራ

ሰው በህይወት ሲኖር ከልደት እስከ ሞት (መለየት) ድረስ የሚያልፍባቸው በርካታ የህይወት ዑደት ሽግግሮች አሉ፡፡ ከህይወት ሽግግሮች መካከል ልደት፣ ሰርግና ለቅሶ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ምንነት ቫን ዠኔፕ[2] እንደሚከተለው ገልጸዋቸዋል፡፡ "በማንኛውም ማህበረሰብ ያለ ግለሰብ በህይወት ሲኖር በተከታታይ የሚያካሂደው የእድሜ፣ የስራ፣ የአካል፣ የማህበራዊ ደረጃ፣ የመኖሪያ ቦታን ለውጥ ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ስነ-ስርዓቶች ሁሉ የህይወት ዘመን ሽግግሮች ናቸው (ዠኔፕ፣ 1960፣ 2-3)፡፡"[3]

ካትሪን ቤል የዠኔፕን ሀሳብ እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡፡ በብዙ ልማዳዊ ማህበረሰብ ተፈጥሯዊ የሆነውን ክስተት መሰረት አድርገው የሚከበሩ ስነ-ስርዓቶች የተዋቀሩት በማህበረሰቡ ባህል አማካይነት ነው፡፡ ለሁሉም ሽግግሮች የሚፈጸሙ ስነ-ስርዓቶች ሂደት የሚከናወነው ማህበረሰቡ በሰራው ደንብ ውስጥ ነው፡፡ አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ የሚያከብራቸውን፣ የህይወት ሁነቶችና የሚያልፍባቸውን መንገዶች እንዲሁም ከአንዱ ወደ ሌላው የሚደረጉ ሽግግሮች በሙሉ የህይወት ዘመን ዑደቶች ናቸው የሚል ሀሳብ እንዳለው ቤል ይገልጻሉ (ቤል፣ 1997፣ 95)፡፡

የህይወት ዘመን ሽግግሮች ልደትን፣ ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን መድረስን፣ ጋብቻን እና ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚከወኑ ስነ-ስርዓቶች ሲሆኑ ሰዎችን ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ያሸጋግራሉ፡፡ እነዚህ ስነ-ስርዓቶች ከሰዎች ተፈጥሯዊ እድገት ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ወሊድን፣ ጉርምስናን፣ እርጅናን እና ሞትን መነሻ በማድረግ በማህበረ-ባህላዊ ደንባቸው መሰረት የተለያዩ ክብረ በዓላት ይፈጽማሉ (ቤል፣ 1997፣ 94)፡፡

---

[2] ቫን ዠኔፕ ምንም እንኳን ለዚህ ጥናት መነሻና መድረሻየ የእሳቸው ስራ የሆነውና በ1960 እ.ኤ.አ ያሳተሙት "The Rites of Passage" የሚለው መጽሀፋቸው ቢሆንም ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ሆኖም ድረ-ገጽ ላይ በቀጥታ ያገኘሁትን የመጽሀፉን ክፍል እንዳለ፣ ማግኘት ያልቻልኩትን ደግሞ እሳቸውን ጠቅሰው የሰሩ ሰዎችን እየጠቀስኩ ለመስራት ተገድጃለሁ፡፡

[3] The life of an individual in any society is a serious of passage from one age to another and from one occupation to another. Whenever there are fine distinctions among age or occupational groups progression from one group to the next is accomplished by special acts, like those which make up apprenticeship in our trades. (Gennep, 1960፣ 2-3).

አንድ ክብረ በዓል ለማክበር መነሻው ተፈጥሯዊ ቢሆንም በብዛት ማህበረሰቡ ባዋቀረውና በሚኖርበት ደንብ አማካኝነት ይከናወናሉ፡፡ ማህበረሰቡ የሚከተላቸውና የሚያከብራቸው በርካታ ህጎች የመኖራቸውን ያህል ሁሉም ስነ-ስርዓቶች የሚከተሏቸው የአከባበር ሂደቶች አሏቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፍራንክ ኤ. ሳላሞን እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡፡

የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች አንድን ግለሰብ ከነበረበት ማህበራዊ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ የሚያሸጋግሩ ሁነቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ ከመሆናቸውም በላይ ከሃይማኖታዊ ወይም ከሌሎች ትዕምርታዊ ተቋማት ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚከበርላቸው ሰዎች የማህበረሰቡን ባህላዊ ማንነት የሚጋሩበት ብሎም የተቋሙን እሴት የሚያውቁበት ነው (ሳላሞን፡ 2004፡ 311)፡፡

የሰው ልጅ ህይወት ከነበረበት ማህበራዊና አካላዊ ደረጃ ወደ ሌላ ይሸጋገራል፡፡ የሽግግሮች ተከታታይነት የሚወሰነው በግለሰቡ ስነ-አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ብስለት እንዲሁም በሚከወንበት ማህበረ-ባህል እምነትና አመለካከት ነው፡፡ ከሽግግሮቹ ጥቂቶች (እንደ ልደት፣ ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን መድረስ እና ሞት) በህይወት ዘመን አንድ ጊዜ ብቻ የሚከሰቱ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ተደጋግመው ሊፈጸሙ የሚችሉ የህይወት ዑደቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ጋብቻ ከአንድ ጊዜ በላይ ሊፈጸም ይችላል፡፡ እንዲሁም አንድ ክፉ የነበረ ሰው ወደ ደግነት ከተለወጠ አንዳች የህይወት ሽግግር አካሂዷል ማለት ነው (ኮርሚክ እና ኋይት፣ 2011፡ 732)፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ማንነት፣ አስተሳሰብ ብሎም አመለካከት ለመረዳትና ለመተርጎም የሚከውነውን ክብረ በዓል ማጤን ተገቢ እንደሆነ የፎክሎር ምሁራን ይጠቁማሉ (ሚርቮልድ፣ 2007፡ 30)፡፡ በመሆኑም የፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ከበራዎች በመመርመር የማህበረሰቡን ማንነት፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት መግለጽ፣ መረዳትና መተርጎም የዚህ ምርምር መሰረታዊ ሀሳብ ነው፡፡

## 1.3 የምርምር ፕሮብሌሞች

የምርምር ፕሮብሌሞች ማለት ጥናቱ እንደመነሻ የሚያጠነጥንባቸው መሰረታዊ ሀሳቦች ሲሆኑ ምርምሩ በህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ላይ እንዲሆን ያስቻሉ ምክንያቶች የሚቀርቡበት ክፍል ነው፡፡

የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች በህይወት ዘመን የሚከሰቱ ወሳኝ ሁነቶችን ምክንያት በማድረግ የሚከናወኑ ስነ-ስርዓቶች ናቸው፡፡ ሰዎች በነዚህ ስነ-ስርዓቶች ምክንያት ከነበራቸው ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ አዲስ ማንነት እና ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡ ልደትን፣ ስነ-ልቦናዊ ዕድገትን፣ ጋብቻን፣ ዓይንን በዓይን ማየት እና ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡

በበርካታ አካባቢዎች ዘንድ ልደትን ክርስትናን፣ ትምህርት ጨርሶ መመረቅን፣ ጋብቻን እና ሞትን ምክንያት በማደረግ እንደየማህበረሰቡ ባህል በርካታ ስርዓተ ክዋኔዎች ይፈጸማሉ፡፡ እንዲሁም ከስርዓተ ክዋኔዎች ጋር የሚነገሩ ባህላዊ አገላለጾች አሉ፡፡ እነዚህ ባህላዊ አገላለጾች ለአፈጻጸሙ ሂደት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ስርዓተ ክዋኔውን ለመረዳትና ለመተርጎም የሚነገሩ ባህላዊ አገላለጾችን ጨምሮ በመመርመር መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ምርምሩ በዋናነት የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምንነትና ክዋኔ እንዴት እንደሚፈጸም መግለፅ፣ መተንተንና መተርጎም እንዲሁም የህይወት ሽግግሮች በስነ-ቃል አግካኝነት እንዴት እንደሚገለፁ ማሳየት ላይ የሚያተኩር እንደመሆኑ መጠን የሚከተሉትን የምርምር ፕሮብሎሞች መሰረት አድርጎ ይካሄዳል፡፡

1. ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን መለየትና መግለፅ ያስችላል፡፡

ወሳኝ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮች ምንነት እንደየማህበረሰቡ አረዳድ እና አስተሳሰብ የተለያዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ለፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ምን ማለት እንደሆኑ መግለጽ የመጀመሪያው ፕሮብሌም ነው፡፡

2. የፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ለዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ያለውን አመለካከት በስነ ቃሉ አማካይነት እንዴት እንደሚገልፅ ማወቅ ያስችላል፡፡

የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ በስነ-ቃል ክምችቱ በህይወት ዘመኑ የሚከሰቱ ሁነቶችን ይገልጻል፡፡ ስለ ህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮችም በዘመኑ የተረዳውንና የተገነዘበውን ያህል በስነ-ቃሉ አማካኝነት ይገልጻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለማህበሩ ህልውና ጠቃሚ የሆኑ እሴቶችን አጠናክሮ ለማስቀጠል፣ አላስፈላጊ የሆኑትንም ለመቃወም እና የማህበሩ አባል ሁሉ ስለ ባህሉ፣ ስለሚኖርበት አለም ተቀራራቢ ግንዛቤ እንዲኖረው ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ አባባሎችን፣ ተረቶችንና ሌሎች የስነ-ቃል ዘርፎችን በመጠቀም ሀሳቡን ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ በስነ-ቃሉ አማካኝነት የህይወት ዘመን ሽግግሮችን እና እሴቶቻቸውን እንዴት እንደሚገልጽ እና እንዴት እንደሚያስቀጥል መፈተሽ ሁለተኛው የምርምር ፕሮብሌም ነው፡፡

3. ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ስርዓተ ክዋኔ መረዳትና መተርጎም ያስችላል፡፡

አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ በተሻለ መልክ ለመረዳትና ለመተርጎም የሚከናወንበትን አውድ መመልከት ተገቢ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ምርምሩ ጥሩ ግኝት እንዲያስገኝ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ በማን፣ መቼ፣ ለምን፣ በምን አይነት ሁኔታ እና እንዴት እንደሚፈጸም በመመርመር የሚከወኑበትን አውድ ያገናዘበ ትንታኔ መስጠትና መተርጎም ሶስተኛው የምርምር ፕሮብሌም ነው፡፡

4. በህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮች ዙሪያ አጥጋቢ ጥናት ባለመካሄዱ የተፈጠረውን ክፍተት ማጥበብ የመጨረሻው የምርምር ፕሮብሌም ነው፡፡

የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ሽግግር ደረጃዎች በማንኛውም ሀገርና በየትኛውም ማህበረሰብ ባህል የሚተኮርባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮችም በተለያዩ ምሁራን ትኩረታቸውን በተለያዩ ማህበረሰቦች ማንጸሪያነት ሲጠኑ ቆይተዋል፣ አሁንም እየተጠኑ ነው፡፡ የጥናት መስኩም ሁለንተናዊ ባህሪያት ላይ በማተኮሩ ተመሳስሎ ቢኖርም በተለያየ ጊዜና በተለያየ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ ሲጠኑ የተለየ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የህይወት ዘመን

ሽግግሮች በፍኖተ ሰላም አካባቢ ምን ገጽታ እንዳላቸው በማጥናት የተፈጠረውን የእውቀት ክፍተት ማጥበብ፣ እንዲሁም የአካባቢው ተወላጅ በመሆኔ የማህበረሰቡን እውቀትና አመለካከት ማሳየት የመጨረሻው የምርምር ፕሮብሌም ነው፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ ከላይ የተገለፁትን የምርምር ፕሮብሌሞች በመነሳት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች መልሷል፡፡

### 1.4.1 የምርምሩ ዋና ጥያቄ

ምርምሩ ሁለት ዋና ዋና ጥያቄዎች አሉት፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምንድን ናቸው?
2. የህይወት ዘመን ሽግግሮች ስርዓተ ክዋኔ የሚፈጸምበት አውድ እንዴት ያለ ነው?

   የሚሉ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ጥያቄዎችም ምላሽ አግኝተዋል፡፡

### 1.4.2 ዝርዝር ጥያቄዎች

1. ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደቶች ሽግግር ደረጃዎች የአከባበር ቅደምተከተል ምን ይመስላል?
2. በህይወት ሽግግሮች ስርዓተ ክዋኔ ላይ የሚቀርቡ ስነ-ቃሎች የሚያነሷቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
3. የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ክዋኔ እንዴት ይፈጸማል?
4. በዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት ምን ይመስላል?

## 1.5 የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት ዋና እና ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ ዋናው አላማ ሁሉንም ዝርዝር አላማዎች ያማከለ ሲሆን ዝርዝር አላማዎች ደግሞ ዋናውን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱና ግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡ እነሱም፡- የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.5.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ የሰው ልጅ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ክብረ በዓልና በአከባበሩ ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን አገላለጾች በሚከወኑባቸው ማህበረ-ባህላዊ አውድ በሙተንተን የፍኖተ ሰላምን አካባቢ ማህበረሰብ አመለካከት ለማሳየት፣ ለመግለጽና ለመተርጎም ሲሆን ይህን ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች መሟላት አለባቸው፡፡

### 1.5.2 ዝርዝር ዓላማዎች

የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ከላይ የተገለፀው ዋና አላማ ከግብ እንዲደርስ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

1. የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን አከባበር መዋቅር ለማሳየት፣
2. የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ክብረ በዓላት የሚፈፀሙባቸውን አውዶች ለመረዳት፣ ለመግለፅ፣ ለመመርመር፣
3. በዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ የሚነገሩ ስነ-ቃላዊ አገላለጾችን ለመተንተን፣ ለመተርጎም፣
4. ማህበረሰቡ በዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ ያለውን አመለካከት ለመረዳት የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ጠቀሜታ

ምርምር ማካሄድ አካባቢያዊና ሀገራዊ ችግሮችን ለመፍታት ብሎም በትምህርቱ አለም አንዳች እውቀት ለመጨመር እንደሚያስችል መረዳት አያዳግትም፡፡ በስርዓት የተካሄደ ምርምር ችግር ፈቺ በመሆኑ ለሀገር እድገት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ይህም ምርምር የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ምንነት የማሳወቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይህ ምርምር በአንድ በኩል የህይወት ሽግግር ደረጃዎችን ምንነት በንድፈ ሀሳብ ደረጃ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ምን ዓይነት ፍቺ እንደሚሰጣቸው እውቀት ያስጨብጣል፡፡

2. ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ የሚፈፀሙባቸውን እውዶች በመመርመር የማህበረሰቡ ጥልቅ አስተሳሰብ ምን እንደሆነ ያሳውቃል፡፡
3. በዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ በቂ ጥናት ባለመካሄዱ ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት በማጥበብ በኩል የራሱ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደቶች የሽግግር ደረጃዎች ምንነት፣ ማህበረሰቡ በስነ-ቃል አማካኝነት እንዴት እንደሚገልጽና አከባበራቸው ምን እንደመሚመስል አጥጋቢ ምርምር አልተካሄደም፡፡ በመሆኑም ምርምሩ ስለ ህይወት ሽግግሮች እውቂያ ከመፍጠሩም ባሻገር በዙሪያው ምርምር ማካሄድ ለሚፈልጉ ምሁራን እንደ መነሻ በመሆን ይጠቅማል፣

## 1.7 የጥናቱ ወሰንና ውስንነት

ሁሉንም የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች የሚገልጹ ስነ-ቃሎችንና ስርዓተ አፈፃፀማቸውን ሰፊ እና ጥልቅ በሆነ መንገድ በማጥናት የማህበረሰቡን እውቀት መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ካጋጠመው የጊዜና የገንዘብ እጥረት ጥናቱ በቦታም ሆነ በጉዳይ ሊወሰን ችሏል፡፡

ጥናቱ የሚያተኩረው በፍኖተ ሰላም አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ ሲሆን ስያሜውም ለፍኖተሰላም ከተማ አስተዳደርና በዙሪያው የሚገኙ የጃቢ ጠህናን ወረዳ ቀበሌዎችን እንዲያጠቃልል ተብሎ የተሰጠ ነው፡፡ እንዲሁም በፍኖተ ሰላም አካባቢ አብዛኛው ህዝብ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ በመሆኑ የሀይማኖቱ ተከታዮች ባህልና እምነት ላይ ያተኩራል፡፡ ምክንያቱም በፍኖተ ሰላም አካባቢ በህይወት ዘመን ዑደቶች ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ ምንም አይነት ጥናት ስላልተጠና፣ የትውልድ አካባቢየ በመሆኑ ባህሉን በቅርበት ስለማውቀው ማህበረሰቡ በህይወት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ በሚከወኑ ከበራዎች የሚታዩ ትእምርቶችን እና ባህላዊ አገላለጾች በመረዳት እና በመተርጎም የማህበረሰቡን አመለካከት በመግለጽ ለማሳየት በመፈለጌ ምርምሩ በዚህ አካባቢ እና በዚህ ጉዳይ አተኩሯል፡፡

በአካባቢው ከሚከናወኑ በርካታ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች መካከል የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ምን እንደሚመስል፣ ከስርዓተ ክዋኔው ጋር ከሚከወኑ ስነ-ቃላዊ አገላለጾች በመነሳት ማህበረሰቡ በህይወት ዘመን ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ ያለውን

አመለካከትና እውቀት መግለጽ፣ መተንተንና መተርጎም ላይ ያተኩራል፡፡ ምልከታ ባደረግሁባቸው በሰርግና በለቅሶ ስርዓት ከበራ ላይ በብዛት የተከወኑት ቃል ግጥሞችና በምሳሌያዊ ንግግሮች የዳበሩ ምርቃቶች ናቸው፡፡ ከከዋኔውም በተጨማሪ በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ ክርስትና ላይ የሚቀርቡ ምርቃቶች ላይ አተኩሯል፡፡ ትንተናው የተካሄደውም እነዚህን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ለምርምሩ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋለው ዋና ዘዴ ምልከታ ቢሆንም የህይወት ዘመን ሽግግሮችን ስርዓተ ከዋኔ ከጅመሩ እስከ ፍጻሜው ያለውን ሂደት በተሟላ ሁኔታ መመልከት ያልቻልኩባቸው አጋጣሚዎች ተከስተዋል፡፡ በመሆኑም ምልከታዬ በአንድ የለቅሶ እና በሁለት የሰርግ ስነ-ስርዓቶች ላይ ሊወሰን ችሏል፡፡

የህይወት ዘመን ሁደት ሽግግር ደረጃዎችን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ስርዓተ ከዋኔዎች በባህሪያቸው ብዙ ጊዜ እና ቦታ የሚወስዱ በመሆናቸው ነው፡፡ የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ስነ-ስርዓቶች ከዋናው ከዋኔ በፊት ቀድመው የሚመጡና ከከዋኔው በኋላ የሚቀጥሉ ተግባራት አሏቸው፡፡ ከዋናው ከዋኔ በፊትና በኋላ የሚከናወኑ ተግባራትን በሚፈጸሙበት አውድ ተገኝቶ ለመመልከት አለማስቻሉ አንዱ የምልከታ ዘዴ ውስንነት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ያልተገኙ መረጃዎችን የቃለ መጠይቅ ዘዴን በመጠቀም ለመሙላት ችያለሁ፡፡ እንዲሁም ሴት በመሆኔ ምክንያት የቀብር አፈጻጸም ስርዓት ለመመልከት አለመቻሌ የመረጃ ክፍተት ቢያስከትልም በመስክ ረዳቶቼ አማካኝነት በማስቀረጽ በመጠኑም ቢሆን ለመፍታት ችያለሁ፡፡

በሌላ በኩል የሰርግና የለቅሶ ስርዓተ ከዋኔዎች የሚከወኑት በቡድን በመሆኑ የሁሉንም ቡድኖች ሙሉ ክንውን ለመመልከት ተቸግሬያለሁ፡፡ የሰርግ ስነ-ስርዓት ደግሞ ከወንዱ እና ከሴቷ ቤት የሚከናወኑ የተለያዩ ጉዳዮች በተመሳሳይ ቀናት የሚፈጸሙ በመሆናቸው ሁለቱም ላይ መገኘት ባለመቻሌ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ተቸግሬያለሁ፡፡ ይህንንም በተለያዩ ቀናት በተፈጸሙ የሴትና የወንድ ቤቶች በመገኘትና በመመልከት መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ በለቀስተኛውና እና በቁሶች የሚከወኑ ጉዳዮች በተመሳሳይ ጊዜ በመቅረባቸው ምክንያት ፍታትና ለቅሶ ለየብቻቸው የሚፈጸሙ በመሆናቸው ለመመልከት ብቸገርም የመስክ ረዳቶቼን እንዲቀርጹ በማድረግ እየተዘዋወርኩ ለመመልከት ችያለሁ፡፡ ከዚህም ባሻገር ልደት በተፈለገው ጊዜ የሚገኝ

የህይወት ሽግግር ባለመሆኑ መስከ በወጣሁበት ጊዜ የወለዱ እናቶችን ማግኘት ባለመቻሌ ልደትን የሚመለከቱ መረጃዎች የተገኙት በቃለ መጠይቅ አመካይነት ነው፡፡

## 1.8 የአጠናን ዘዴዎች

ይህን ምርምር ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ከመስክ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካኝነት የተሰበሰቡትን የያዘ ሲሆን ካልዓይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ ከቤተ-መጻህፍት ከርዕሱ እና ከጥናቱ አካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንድፈ ሀሳቦችና ጻሁፊ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ነው፡፡

### 1.8.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በፎክሎር ላይ ለሚደረግ ምርምር ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የየራሳቸው ጠንካራ ጎን ቢኖራቸውም የመረጃ ክፍተት ሊያስከትሉ የሚችሉ ደካም ጎንም ስላላቸው በተናጠል መጠቀም አይመከርም፡፡ በመሆኑም በአንዱ ዘዴ ድክመት የተፈጠረውን ክፍተት በሌላው ጥንካሬ ለመሙላት ሶስቱንም ዘዴዎች አዋህዶ መጠቀም ተገቢ ነው (ግሬይ፣ 2004፣ 33)፡፡ በዚህ ጥናትም እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

#### 1.8.1.1 ምልከታ

ምልከታ አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከናወን ተመራማሪው በአካል ተገኝቶ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው፡፡ የምልከታን ዘዴ ምንነትና አስፈላጊነት ጎልድስቴን እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> የምልከታ ዘዴ፣ በቀጥተኛ ምልከታ አማካኝነት መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን መስከኛው ከሚከወነው ጉዳይ ውጭ ወይም ውስጥ በመሆን የተመለከተውን ጉዳይ ለመግለጽ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ የሚለው ቃል ፍቺ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን ሁሉንም የስሜት ህዋሳት በመጠቀም መረዳትንም ይጨምራል፡፡ ማለትም በቀላሉ

በአይን ከማየት ባሻገር በትኩረት በማዳመጥ፣ በማሽተትና በመቅመስ የክዋኔውን አጠቃላይ ድርጊቶችን መረዳትና መተርጎም ማለት ነው (ጎልድስቴን፣ 1964፡77)፡፡[4]

በሌላ በኩል ቫንደርስቴፕ እና ጆንስተን ምልከታ ሰዎች የራሳቸውን ጉዳይ ሲተገብሩ በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ እንደሆነ ጠቅሰው ምልከታ ሲካሄድ የራሱ የሆኑ ሂደቶች የሚከተሉት እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ በመጀመሪያ በቀላሉ የመቼቱንና የሰዎችን አጠቃላይ እንቅስቃሴ መመልከትና መከታተል፣ መቼቱን፣ ተሳታፊዎቹንና እንቅስቃሴያቸውን መግለፅ፣ በመጨረሻም ከቡድኑ ወይም ከተሳታፊው ግለሰብ እንቅስቃሴ በመነሳት ማንነታቸውንና የሚሰጡትን ፍቺ መረዳት የሚሉ ናቸው፡፡ በነዚህ ሶስት ደረጃዎች ተመራማሪው ማስታዎሻ መያዝና ጠለቅ ያለ ገለፃ መስጠት እንዳለበትም አስቀምጠዋል (ቫንደርስቴፕ እና ጆንስተን፣ 2009፣ 239)፡፡

በዚህ ጥናትም ምልከታ አንዱ ዘዴ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ምክንያቱም የአንድን አካባቢ ማህበረሰብ ባህል ለመረዳትና በማህበረ-ባህላዊ አውዱ ውስጥ ለመተንተን የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በምልከታ አማካኝነት ዋና ዋና የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ እንዴት እንደሚፈጸም እና ሰዎች በስነ-ቃሎቻቸው አማካይነት እንዴት እንደሚገልጿቸው እንድረዳ አስችሎኛል፡፡ በመሆኑም ስለ ህይወት ዘመን ዑደቶች ምንነት ማህበረሰቡ የሚሰጣቸውን ባህላዊ ትርጉሞች ለመረዳት፣ ስርዓተ ክዋኔያቸው የሚፈጸምበትን ማህበረ-ባህላዊ አውድ ለመገንዘብ እንዲሁም ለጉዳዩ ትርጉምና ትረካ ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

ምልከታ እንደሚጠናው ጉዳይ መለያየት በሁለት አይነት መንገድ ይካሄዳል፡፡ ተሳትፏዊ ምልከታ እና ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታ ይባላሉ፡፡ ተሳትፏዊ ምልከታ ማለት ተመራማሪው ከሚጠናው ባህል ባለቤቶች ጋር ጉዳዩን የሚከውንበት ሲሆን ተሳታፊዎች ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ተመራማሪው ይህንን ዘዴ ለመጠቀም የሚያጠናውን ማህበረሰብ ባህል፣ ደንብ፣ ወግ፣ ልማድ፣ ቋንቋ ማወቅ አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ በሚፈጽሟቸው ስርዓተ ክዋኔዎች ሁሉ እየተሳተፈ የሚፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ያስችለዋል፡፡

---

[4] Observation method: those methods used by the field worker in obtaining data by direct observation, looking from the outside in and describing the situation as he sees it. The term 'observation', as used in this context, is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting, when ever this may be appropriate (Goldstein, 1964፡ 77).

ተሳትፏዊ ምልከታ ከላይ የተዘረዘሩት ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም የሚከተሉት ድክመቶችም አሉት፡፡ በተወሰነ ጊዜና ቦታ ተጀምረው የማይጠናቀቁ ስርዓተ ክዋኔዎችን ለመረዳት ያስቸግራል፤ በቡድን ተከፋፍለው የሚከናወኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በተመሳሳይ ጊዜና ቦታ ለመመልከት ስለማያስችል መረጃዎችን ያሳጣል፡፡ በነዚህ ምክንያቶች የማይገኙ መረጃዎችን ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታን በመጠቀም መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡ ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታ ብዙ ሁኔታዎችን በአንድ ጊዜ ለመመልከት፣ ስለ ጉዳዩ ማስታዎሻ ለመያዝ፣ ስርዓተ ክዋኔውን በቴፕ ወይም በቪዲዮ ለመቅረፅ፣ በክዋኔው ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ነገሮችን ለመከታተልና ለመረዳት ያስችላል፡፡ በመስክ ስራ ላይ ማስታዎሻ መያዝ ለሚቀርቡት ሀሳቦች ምላሽ፣ ፍቺና ትንታኔ ለመስጠት ዕድል ይፈጥራል (ጎልድስቴን፣ 1964፣ 81)፡፡

በዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት ሁለቱንም የምልከታ አይነቶች እንደአመቺነታቸው በመጠቀም ነው፡፡ ተሳትፏዊ ምልከታ የሰርግና የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች ሲፈጸሙ በመገኘት የባህላዊ ክዋኔዎችን አቀራረብ ቅደም ተከተልና የሚጠቀሟቸውን ስነ-ቃሎች ከነአውዳቸው እንድረዳ አስችሎኛል፡፡ በሌላ በኩል የልደት አከባበር በታቀደው ጊዜ ባለመገኘቱ፣ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ደግሞ ከጾታ አኳያ ሙሉውን ስርዓተ ክዋኔ (በተለይ የቀብር ስርዓቱን) ለመመልከት ባለመቻሌ ተሳትፏዊ ባልሆነ ምልከታ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ ይህም የሰርግና የለቅሶ ክዋኔዎች ሲፈጸሙ ማስታዎሻ ለመያዝና በቪዲዮ ለመቅረጽ አስችሎኛል፡፡ ነጻ፣ በከፊል የተወሰነ እና ውስን የተሰኙ የምልከታ ቴክኒኮች እንደአስፈላጊነታቸው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ስርዓተ አከዋወን እና በስነ-ቃል አማካኝነት እንዴት እንደሚገለጹ ለመረዳትና ለመግለጽ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ሁሉንም እንደአመቺነታቸው መጠቀም ተገቢ በመሆኑ ነው፡፡

ምልከታ ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ለማግኘት ጠንካራ ዘዴ ቢሆንም ብቻውን ለመጠቀም የሚያስቸግሩ ድክመቶች አሉት፡፡ ከድክመቶቹ መካከል ጎልድስቴን የሚያነሱት ጉዳዩ እንደሚቀርብበት የአውድ ዓይነት የምናገኛቸው መረጃዎች ሊለያዩ እንደሚችሉ ነው፡፡ በምልከታ አማካኝነት የሚገኝ መረጃ ሁሉጊዜ መቼና እንዴት መመልከት እንዳለበት መወሰን ዋናው ጉዳይ ነው፡፡ ሁልጊዜም ተመራማሪው ቀረጻ የሚያካሂደው ጉዳዩ በሚከናወንበት ቅጽበት መሆን አለበት፡፡ ይህም ጉዳዩ እንዳይረሳ ያደርጋል (ጎልድስቴን፣ 1964፣ 94)፡፡

### 1.8.2.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ አንዱና በጣም የተለመደው መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ በተመራማሪውና በተጠኚው ማህበረሰብ አባል መካከል የሚደረግ የሃሳብ ልውውጥ ነው (ግሬይ፣ 2004፣ 212)፡፡ ተመራማሪው በምልከታ ማግኘት ያልቻላቸውን መረጃዎች ወይም ያልተረዳቸውን ክንውኖች ለመረዳት ቃለ መጠይቅ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ የቃለ መጠይቅን አስፈላጊነት ቫንደርስቴፕ እና ጆንስተን እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

በስርዓት የተዋቀረ ቃለ መጠይቅ የማህበረሰቡን እይታ፣ አመለካከትና ለኑሮው የሚሰጠውን ፍቺ ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ያስገኛል፡፡ እንዲሁም በቃለ-መጠይቅ የሚገኝ መረጃ የተሳታፊዎች እውቀት፣ እምነት፣ ስሜት፣ ፍላጎት፣ ስራ እንዲሁም ለሚያከናውኗቸው ድርጊቶች የሚሰጧቸውን ምክንያቶች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ተመራማሪው ቃለ መጠይቅን በዘዴነት ሲጠቀም ስለሚጠይቀው ጉዳይ ጥልቅ እውቀት፣ ልምድ፣ ችሎታና ብቃት ሊኖረው ይገባል፡፡[5] የቃለ መጠይቅን አስፈላጊነት ጎልድስቴን እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ የመረጃ ሰጪዎችን የግል ታሪክ፣ የሚያቀርቡትን ጥበብ፣ የዕውቀታቸውንና የስሜታቸውን ፍቺ፣ የፎክሎራዊ ጉዳዩን ተስተላልፎ፣ እንዲሁም በምልከታ ስላልተገኙ ስርዓተ ክዋኔዎች ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል (ጎልድስቴን፣ 1964፣ 104-108)፡፡

በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በምልከታ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማነፃፀር ተቀራራቢነታቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ተመራማሪው በቃለ መጠይቅ ያገኛቸውን መረጃዎች በተለያዩ ጊዜዎች በሚፈጠሩ ተመሳሳይ አውዶች ውስጥ መመርመር አለበት፡፡ አንድ ጉዳይ በተለያዩ መረጃ አቀባዮች ምን ገፅታ እንዳለው መፈተሽ አለበት፡፡ መረጃን መመዘን ቅደም ተከተል ለማስያዝ፣ የተደጋገሙ ምላሾች ትኩረት የሳቡ መሆናቸውን ለመረዳት እንዲሁም ተመሳሳይ መረጃዎችን በማጤን የጥያቄዎቹን መልስ ለማዳበር ያስችላል፡፡ ይህንንም አንድ ጉዳይ የሚያወሩ የተለያዩ ቃለ መጠይቆችን ለተመሳሳይ መረጃ አቀባዮች በመጠየቅ ምን ምላሽ እንደሚሰጥባቸው ለመለየት፣ ቅደም ተከተል

[5]Beginning researchers typically recognize the need to learn the skills of experimental design or content analysis, but many erroneously presume that interviewing is like chatting. After all, if you can talk, you can interview, right? In reality, interviewing requires a great deal of knowledge, experience, skill, and finesse. (Vanderstep and Johnston, 2009፣ 224)

ለማስያዝ፣ የተደጋገሙ ምላሾች ትኩረት የሳቡ መሆናቸውን ለመረዳት እንዲሁም ተመሳሳይ መረጃዎች በማጤን የጥያቄዎቹን መልስ ለማዳበር፣ በማህበራዊ አውድ መለያየት ምክንያት ሊገኝ የሚችለውን የተለያየ መረጃ ለመረዳትና ለመተርጎም ያስችላል (ጎልድስቴን፣ 1964፣114)፡፡

ቃለ መጠይቅ በዘዴነት ጥቅም ላይ ሲውል መቅረጸ ድምጽ መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ ጎልድስቴን አጠንክረው ገልጸዋል፡፡ መቅረፀ ድምፅ በተመራማሪውና በመረጃ አቀባዩ መካከል ያለውን የሀሳብ ልውውጥ በሙሉ ለመያዝ ምቹ ከመሆኑም ባሻገር ስህተት ቢፈጠር እንኳን ካቆመበት ለማስቀጠል ያስችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በንግግር የሚቀርቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን (ምሳሌያዊ ንግግር፣ ቀልድ፣ ተረት እና ልዩ ልዩ ባህላዊ እምነቶች፣ ወዘተ.) በሚቀርቡባቸው ተፈጥሯዊ አውዶች ተገኝቶ ለመሰብሰብም አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡

ተመራማሪው መረጃዎችን ደጋግሞ ለማረጋገጥም ሆነ በጥልቀት ለመረዳትና ለመመዘን ከማስቻሉም በላይ የመረጃ ክፍተት ካጋጠመ እንደገና ለማዘጋጀት የሚያስችል ወሳኝ መሳሪያ ነው (ጎልድስቴን፣ 1964፣119-120)፡፡ በዚህ መሰረት ስለ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች የሚነገሩ ስነ-ቃሎችን ለመሰብሰብ፣ የሰዎችን አመለካከት ለመረዳት፣ የስርዓተ ክዋኔውን አፈጻጸምና ለምን እንደሚፈፅሙ ለመረዳትና ለመመርመር የሚያስችለኝን መረጃ ለመሰብሰብ በቃለ መጠይቅ ጊዜ መቅረፀ ድምፅ ተጠቅሚያለሁ፡፡

ሁለት አይነት የቃለ መጠይቅ አዘገጃጀቶች አሉ፡፡ ነፃ ቃለ መጠይቅና ውስን (ተመራማሪው አቅጣጫ የሚሰጥበት) ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ ነፃ ቃለመጠይቅ ተመራማሪው ለመረጃ ሰጪዎች ያልተገደበ ነፃነት በመስጠት ስለተጠየቁት ጉዳይ የፈለጉትን ያህል እንዲናገሩ ዕድል ይፈጥራል፡፡ ውስን ቃለ መጠይቅ ደግሞ ተመራማሪው ስለ ጉዳዩ ውስን መረጃዎችን ሲፈልግ የሚጠቀመው ነው፡፡ የቃለ መጠይቅ ዘዴ ሶስት ቴክኒኮች አሉት፡፡ ገደብ የሌለው፣ በከፊል የተገደበ እና የተገደበ ይባላሉ (ፍሊክ፣ 2006፣150)፡፡

የህይወት ዘመን ዑደቶችን ሽግግር ደረጃ፣ ስርዓተ አፈፃፀማቸው እንዴት እንደሆነ፣ በስነ ቃል አግባብነት እንዴት እንደሚገለጹ ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ቃለ መጠይቅ አንዱ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለዋና ዋና የህይወት ዑደት ዘመን ሽግግር ደረጃዎች

የሚሰጠውን ፍቺ ለመረዳት አይነተኛ ዘዴ ነው፡፡ በሌላ በኩል በምልከታ መገኘት ያልቻሉ መረጃዎችን ለማግኘትም ጠንካራ ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ ባለመካሄዱ የተፈጠረውን የመረጃ ክፍተት በመሙላት በኩል ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡

የቃለ መጠይቅ ቴክኒኮች እንደተጠየቁት ሰዎች ሁኔታ፣ እንደሚፈለገው የመረጃ ዓይነት ሁሉም እንደአመቺነታቸው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ እነዚህም በዋና ዋና የህይወት ዘመን ሁደት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ የሚነገሩ ስነ-ቃሎችን እና ስለ ስርዓተ ክዋኔያቸው አፈፃፀም የምፈልገውን ያህል መረጃ ለማግኘትና የተለያዩ ባህላዊ ትዕምርቶችን ባህላዊ ትርጉም ለመረዳት እንዲሁም ፍቺ ለመስጠት አስችሎኛል፡፡

### 1.8.1.3 የተተኳሪ ቡድን ውይይት

ከምልከታና ከቃለ መጠይቅ ቀጥሎ የሚጠቀሰው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የቡድን ውይይት ነው፡፡ የቡድን ውይይት ማለት በተመራማሪውና ከአንድ በላይ በሆኑ መረጃ አቀባዮች መካከል የሚደረግ የሀሳብ ልውውጥ ነው (ስቸንሴል እና ሌሎች፣ 2009፡ 51)፡፡ ውይይቱን የሚያካሂዱ ሰዎች ቁጥርም ከ6-10 (ከ5-15) ያህል ሰዎች መካከል የሚደረግ የጥያቄና መልስ ሂደት ነው (ቫንደርስቴፕ እና ጆንስተን፣ 2009፡ 235)፡፡

የቡድን ውይይት ሁለት አይነት ነው፡፡ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆነ በመባል ይታወቃሉ፡፡ መደበኛ የሚባለው ተመራማሪው ወካይ ያላቸውን ግለሰቦች ስለ ጉዳዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሁሉንም የቡድኑ አባላት የሚያሳትፍበት ሲሆን መደበኛ ያልሆነ የሚባለው ደግሞ መረጃን በተፈጥሯዊ መቼት ለመሰብሰብ ተመራማሪው እየተገኘና ራሱም እየተሳተፈ መረጃ የሚያገኝበት ነው፡፡

የቡድን ውይይት ባህላዊ ትርጉሞችን ለመረዳት፣ ተሳታፊዎች ስለ ጉዳዩ ያላቸውን የእውቀት መጠን ለመለየት፣ በህይወት ልምድ የዳበረ ቀላልና የሚጨበጥ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ መሆኑን ቫንደርስቴፕ እና ጆንስተን ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአጭር ጊዜ ብዙ መረጃ ለማግኘት፣ የተሳታፊዎችን የአተረጓጎም ስልት ለማወቅ እና ተመራማሪው ግልፅ የሆነ መላምት እንዲኖረው ያግዛል፡፡

በዚህ ጥናት ሁለቱም እንደአመቺነታቸው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በተፈጥሯዊ መቼት ያልተገኙ መረጃዎች መደበኛ ባልሆነ መንገድ ተሰብስበዋል፡፡ ከዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች መካከል በተፈጥሯዊ መቼት ያልተገኙ፣ በቃለ መጠይቅም ያልተብራሩ ጥልቅ ጉዳዮችን፣ ባህላዊ ትርጉሞችን ለመረዳት ከባህሉ በተመረጡ መረጃ ሰጪዎች መካከል ውይይት በማካሄድ በቂ መረጃ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ ሲከናወን ሁሉንም በማስታዎሻ ለመያዝና በቪዲዮ ለመቅረፅ አመቺ ባለመሆኑ ስለ ጉዳዩ የሚያውቁ ሰዎችን በማሰባሰብ መደበኛ የሆነ የቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡ ባጠቃላይ በዚህ ምርምር በምልከታ ያልተገኙ መረጃዎች ከስድስት ሰዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና አምስት አባላት ያሉት የቡድን ውይይት[6] በማካሄድ ተሰብስበዋል፡፡

### 1.8.2 የመረጃ ትንተና ዘዴ

የህይወት ዘመን ሽግግር ደረጃዎች ክብረ በዓላት በሚከበሩበት ማህበረ-ባህላዊ አውድ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በአውዳዊ ስነ-ዘዴ እተያይ የመተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ የተተነተኑት መረጃዎች ተተርጉመው በገለጻ የአቀራረብ ስልት ቀርበዋል፡፡ ምክንያቱም ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምንነት፣ የአከባበር ስርዓታቸውን ሂደትና በስነ-ቃል አማካኝነት እንዴት እንደሚገለጹ በሚከወኑበት ማህበረ-ባህላዊ አውድ ውስጥ ለማሳየት፣ ለመግለጽ፣ ለመተንተንና ለመተርጎም የሚያስችል የትንተና ዘዴ እና የአቀራረብ ስልቶች በመሆናቸው ነው፡፡

---

[6]ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች መልዓከ ጥበብ መሪጌታ ስሜነህ አበበ፣ ቄስ ሚናስ ሀሩይ፣ አቶ ሙሉ ያታይህ፣ ወ/ሮ ድንቃየሁ አለሙ፣ አቶ ዘለቀ መንግስቱ፣ ወ/ሮ ዝይን አለሙ ይባላሉ፡፡ የቡድን ውይይት ያካሄዱ ሰዎች ደግሞ አቶ በቀለ ቸሩ፣ ቄስ ሚናስ ሀሩይ፣ መሪጌታ ስማኔ ገብረ እየሱስ፣ እማሆይ አሚምታ የደሴ፣ አቶ ለገስ እምሩ ይባላሉ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2 ክለሳ ድርሳን

ይህ ምዕራፍ ሁለት ዋና ዋና ርዕሶችን የያዘ ነው፡፡ እነሱም ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝትና የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ናቸው፡፡ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ምርምሩን ለማካሄድ ተገቢነት ያላቸው፣ የህይወት ዘመን ሽግግር ደረጃዎችን ምንነት ለመረዳት አስፈላጊ የሆኑ ንድፈ ሀሳቦችና ጽንሰ ሀሳቦች የቀረቡበት ነው፡፡ የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ላይ የተካሄዱ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች የተቃኙበት ክፍል ነው፡፡ በአንድ ምዕራፍ እንዲጠቃለሉ የተደረገበት ምክንያት ሁለቱም ርዕስ ጉዳዮች የህይወት ሽግግር ደረጃዎች ክብረ በዓል አጠናን ንድፈ ሀሳባዊ ምንነት፣ የምርምሩን አስፈላጊነት በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ለማሳየት እንዲሁም ከተሰሩ ተዛማጅ ምርምሮች የሚለይበትንና የሚመሳሰልበትን ጉዳይ የሚያሳይ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከቤተ መጻሕፍት የተሰበሰቡ በመሆናቸው በአንድ ምዕራፍ ስር ሊቀርቡ ችለዋል፡፡

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

የዚህ ጥናት ትኩረት ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች አከባበር የሚከወኑ ባህላዊ ተምሳሌቶችን በመለየትና በመተንተን ማህበረሰቡ በስነ-ቃል ክምችቱ እንዴት እንደሚገልጻቸው ማሳየት፣ መተንተንና መተርጎም ነው፡፡ በመሆኑም የዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ክዋኔ ለመረዳት የፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብን መደገፍ አስፈላጊ ነው፡፡ የሽግግር ደረጃዎችን አከባበር ለመረዳት ደግሞ የሚቀርቡበትን አውድ ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ርዕስ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ምንነት፣ የአውድ ተኮር ጥናት መታገቢያዎች እና የክብረ በዓል ምንነትና አከባበር የሚሉ ርዕስ ጉዳዮች ከህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮች ጋር ያላቸው ዝምድና እና የሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ አከባበር በአውድ ውስጥ እንዴት እንደሚጠና የሚቀርብበት ነው፡፡

### 2.1.1 የፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ምንነት

የፎክሎር ክዋኔን ምንነት የተለያዩ ምሁራን እንደየመጡበት የትምህርት አቋም በተለያየ መንገድ ይበይኑታል፡፡ ቦውማን ስለ ክዋኔ ምንነት የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡

> ክዋኔ ማለት በዋናነት እንደ ተግባቦት ባህሪና ዓይነት የሚወሰድ፣ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ሲከወን የሚፈጸሙ ኪናዊ ጉዳዮችን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ክዋኔ በራሱ መንገድ ተቀምሮ ለታዳሚ የሚደርስና የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የሚታወቅበት እንዲሁም ሰዎች በተግባቦት ሂደታቸው ውስጥ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮቻቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው (ቦውማን፣ 1992፣ 3)፡፡[7]

ከዚህም በተጨማሪ (ቦውማን፣ 1992፣ 4) እንደገለጹት ክዋኔ መጠናት እንደተጀመረ በጽሁፍ ያለና በድርጊት የሚገለጽን ፎክሎራዊ ጉዳይ ለመለየት የተሰጠ ስያሜ ነበር፡፡ የአንድ ነገር ወካይ ሞዴል ወይም ምስል ተደርጎም ይታሰብ ነበር፡፡ ነገር ግን ክዋኔ የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፊና ጥልቅ የሰው ልጅ ባህሪያት መገለጫ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በሌላ በኩል ክዋኔ ማለት አንድ የባህል ስምምነት ውጤት የሚቀርብበት መንገድ ነው በማለት ሀሳባቸውን የሰነዘሩት (ቤን አሞስ፣ 1993፣ 218) ናቸው፡፡ የባህሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ አቅምና አቅሙን የሚያሳይበት ድርጊት፣ እውቀትና እውቀቱን የሚገልጽበት መንገድ፣ እምነትና እምነቱን የሚያከብርበትን ስርዓት ክዋኔ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በንግግር፣ በሙዚቃ፣ በዳንስና በድራማ ውስጥ የሚታዩ ክንውኖችን ሁሉ እንደሚያጠቃልል ገልጸዋል፡፡

አሁን አሁን ክዋኔ በድርጊት የሚቀርቡ ጉዳዮች ፍቺ ከጥንታዊ ጽሁፎችና ከሚቶች ጋር የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው የሚጠቁሙ ነጥቦችን ለመለየት የሚቀርቡበትን አውድ መረዳት ተገቢ በመሆኑ በቃልና በድርጊት ብቻ የሚቀርቡ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ ከማተኮር በተጨማሪ ልዩ ልዩ ትውፊቶች፣ ተረቶች፣ ባህላዊ ትዕምርቶችና ማህበራዊ ተምሳሌቶች ላይ

---

[7]Performance is a mode of communicative behavior and type of communicative event. While the term may be employed in an aesthetically neutral sense to designate the actual conduct of communication (as opposed to the potential for communicative action), performance usually suggests an aesthetically marked and heightened mode of communication, framed in a special way and put on display for an audience. The analysis of performance- indeed, the very conduct of performance-highlights the special, cultural, and aesthetic dimentions of the communicative process (Bauman,1992፡3).

ትኩረት እየሰጠ መጥቷል፡፡ በመሆኑም ፎክሎርን እንደ ልዕለ መዋቅርና አንድን ጉዳይ የመግለጫ ስልት ወይም እንደ ባህል ማሳያ መስታወት ከማሰብ ይልቅ ማህበረሰቡ በህይወት ዘመኑ የሚያከናውናቸው ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ፖለቲካዊ ስርዓተ ክዋኔዎችን መግለጽ፣ መተንተንና መተርጎም ላይ አተኩሯል (ሳላሞን፣ 2004፣ 325)፡፡

በክዋኔ ተኮር ፎክሎራዊ ጥናት የማህበረሰቡን የተግባቦት መንገድ፣ በክዋኙ የመከወን ብቃት፣ እንዲሁም በታዳሚው አተረጓጎም ላይ የተከሰቱ ለውጦችን በመመርመር አስተሳሰቡንና አመለካከቱን ማሳየት ይቻላል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በደንብ ለመረዳት ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጉዳዩን እንዴት እንደሚተርት፣ እንደሚያዜምና እንደሚናገር መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም ክዋኔ አንድ ማህበረሰብ በፈጠረው ማህበረ-ባህላዊ አውድ ውስጥ ባህሉን፣ እሴቱንና አስተሳሰቡን በድርጊት የሚገለጽበት ዘዴ ነው (ቤን አሞስ፣ 1993፣ 223)፡፡

የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ክዋኔ ለማጥናት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁለት መሰረታዊ አተያዮች እንዳሉ እና የሚከተሉት እንደሆኑ (ቦውማን፣ 1992፣ 5) ጠቁመዋል፡፡ የመጀመሪያው ማህበረሰቡ ጉዳዩን የሚያከናውነው ተስማምቶ ባዋቀረው ስርዓትና ደንብ መሰረት በመሆኑ ታዳሚው አዳዲስ ፎክሎሮችን የመፍጠር እድል ሊኖረው እንደሚችል የሚያመለክት ሀሳብ ሲኖረው፤ ሁለተኛው ደግሞ ከዋኙ በተሳታፊዎች ብሎም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚጠቀመው ቋንቋ፣ የአነጋገር ለዛ እና የአከዋወን ሂደት መመራት እንዳለበት የሚያመለክት ሀሳብ አለው፡፡

የአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ አቀራረብ በሚከውነው ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች እንዲሁም እንደ ከዋኙና ተሳታፊው አቅም ይለያያል፡፡ በዚህ ምክንያት መልዕክቱም ስለሚለያይ የክዋኔው ደረጃ በሚቀርብበት አጋጣሚ ይወሰናል፡፡ በሌላ በኩል የከዋኙና የተሳታፊው ጾታ፣ እድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፣ ክዋኔውን ለመከወን የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣ ጉዳዩ የሚቀርብበት ወቅትና ጊዜ እንዲሁም የፎክሎራዊ ጉዳዩ ዓይነት፣ ጭብጥና የአቀራረብ ስልት ሁሉ በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉ በመሆናቸው ለሚከወኑበት አጋጣሚ የሚመጥኑ ሆነው መቅረብ አለባቸው፡፡

ከላይ ዘርዘር አድርጌ ለማቅረብ እንደሞከርኩት አንድን ማህበረሰብ በፎክሎሩ አማካኝነት ለመረዳት ጠንካራው ዘዴ ክዋኔውን ማጥናት ነው፡፡ ነገር ግን ከሁሉም የበለጠ ውስብስብና

የሚፈጸሙ ስኑ ስርዓቶችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ፎክሎሩ ነፍስና ስጋ የሚኖረውም በዚህ መንገድ ከተጠና ነው፡፡ በመሆኑም የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ የተሟላ ፍቺ ይኖረው ዘንድ በሚቀርብበት ማህበረ-ባህላዊ አውድ ውስጥ መተንተን አለበት፡፡

አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ በሚከወንበት አውድ ውስጥ ስናጠና ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ስድስት ነጥቦችን መመልከት ተገቢ እንደሆነ (ቦውማን፡ 1983፡ 367) ጠቁመዋል፡፡ እነሱም ፍቻዊ አውድ፣ ተቋማዊ አውድ፣ የማህበረሰቡ የተግባቦት ሂደት አውድ፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ግለሰባዊ አውድ፣ እና ሁኔታዊ አውድ ናቸው፡፡ ምንነታቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ፍቻዊ አውድ የመጀመሪያው አውድ ውስጥ የሚነሳ ጉዳይ ሲሆን በዋናነት የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ስለሚከውናቸው ልምዶችና እውቀቶች ምን ግንዛቤ እንዳለው፣ እንዴት እንደሚረዱት፣ የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያሳዩ እና ለመከወን ያነሳሳቸው ጉዳይ ምን እንደሆነ ለመገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ጉዳዩ በተለያዩ ሰዎች ምን ትርጓሜ እንዳለው ከማሳወቅም ባሻገር ከብዙው የተለየ ፍች ሊያስገኝ ስለሚችል በጥንቃቄ መታየት አለበት፡፡

በመሆኑም የፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ስለ ዋና ዋና የህይወት ሽግግሮች ምን ግንዛቤ እንዳለው፣ እነዚህን ሁነቶች እንዴት እንደሚረዱቸው፣ ከበራቸው የማህበረሰቡን የትኛውን የህይወት ገጽታ እንደሚያሳይ እና ጉዳዩን ለመከወን ምን እንዳነሳሳቸው ያስገነዝባል፡፡ ዋና ዋና የህይወት ሽግግሮች በሁሉም የማህበረሰቡ ክፍል የሚከወኑ በመሆናቸው አዳዲስ ፍቺ ለማስገኘት ረድቷል፡፡

ተቋማዊ አውድ ሁለተኛው በአውድ ተኮር ጥናት የሚተኮርበት ሲሆን ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው፡፡ ጉዳዩ የሚከወንበት ተቋም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ወይስ ሃይማኖታዊ መሆናቸውን ከመመርመር ባሻገር ምን ዓይነት ተቋማዊ ፋይዳ ያበረክታሉ የሚለውንም ያመላክታል፡፡ ማህበረሰቡ የልደት፣ ሰርግና ለቅሶ ስርዓተ ከዋኔዎች የሚከወኑት የት እንደሆነ ከማስገንዘቡም በላይ መከወናቸው የሚያስገኘውን ተቋማዊ ፋይዳ ለመመርመር አስችሏል፡፡

የተግባቦት ሂደት አውድ ሶስተኛው አውድ ተኮር ጥናት ውስጥ የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ ትኩረቱም የሚጠናው ጉዳይ ከሌላ የፎክሎር ቅርጽ ጋር እንዴት ይዛመዳል? የሚለውን

ጥያቄ መመለስ ነው፡፡ ማለትም የሚጠናውን ጉዳይ ቅርጽ ምንነት፣ አንዱን ከሌላው ለመለየት ማህበረሰቡ የሚጠቀምበት ሀገርኛ ሰያሚ ምን እንደሆነና ከሌሎች ጋር ያለውን ዝምድና እንዴት እንደሚረዱት ማመላከት ነው፡፡ በእነዚህ የፎክሎር ዘውጎች ዝምድና፣ በተናጠል መቼ፣ በማን፣ እንዴት፣ መነገር፣ መዘፈን፣ መነብነብ፣ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የእያንዳንዱ ዘውግ ይዘት፣ ፍቺ እና ቅርጽ ምን መሆን እንዳለበት ይወስናል፤ የእያንዳንዱን ዘውግ አገልግሎትና አጠቃቀም ይወስናል፣ የእያንዳንዱ ዘውግ ተገቢነትና ተበባዊ ዋጋ የሚመዘንባቸውን መስፈርቶች ይገልጣል፡፡

አራተኛው በአውድ ተኮር ጥናት የሚተኮርበት ማህበራዊ መሰረት ነው፡፡ ማህበራዊ መሰረት የማህበረሰቡን የኑሮ ሀልውና የማጤን ተገቢነትን የሚያመለክት ሀሳብ ነው፡፡ ይህም ማለት የሚጠናው ቅርጽ የሚከወነው በየትኛው የማህበረሰብ ክፍል እንደሆነ፣ የትኛውን ማህበራዊ ደረጃ እንደሚያሳይ፣ በክዋኔው የሌላው ማህበረሰብ ተሳትፎ ምን እንደሆነ በመረዳት የተሻለ አውዳዊ ትንታኔ መስጠት ይቻላል፡፡ እንዲሁም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በጾታ፣ በእድሜ፣ በሙያ/በሥራ፣ በማህበራዊ ደረጃ፣ በእምነት/ በሀይማኖት፣ በልዩ ልዩ ቡድኖች (ማህበራዊ አደረጃጀት መርሆች) ይከፈላሉ፡፡ እነዚህ ለአንድ ህብረተሰብ መለያየትና መከፋፈል መነሻ የሆኑ መሰረታዊ ጉዳዮችና ቡድኖች ለፎክሎራዊ ጉዳዩ መለያየትም ምክንያቶች ናቸው፡፡

በአምስተኛነት የሚጠቀሰው ግለሰባዊ አውድ ነው፡፡ በዋናነት የሚከወነው ፎክሎራዊ ጉዳይ ከግለሰቡ ኑሮ፣ ሀሳብና ስሜት ጋር እንዴት ይሄዳሉ? የሚለው ጥያቄ ላይ ያነጣጥራል፡፡ በመሆኑም የግለሰብን ስሜት የመግለጽ አቅማቸውን እና ፎክሎራዊ ቅርጹ ለግለሰቦች የሚሰጠውን ቦታ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ሁኔታዊ አውድ ስድስተኛው በአውድ ውስጥ የሚነሳ ጉዳይ ሲሆን ማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ቅርጹን የሚከውነው በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው? የሚለውን የሚመልስ ነው፡፡ ለአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ መፈጠር ምክንያት የሚሆን ማህበረሰባዊና ግለሰባዊ አጋጣሚ ነው፡፡ ሁኔታዊ አውድ በባህሉ የተወሰነ የአንድ ባህሪ ወይም ገጠመኝ መግለጫ አንድ ትርጉም ያለው ድርጊት/ተግባር የሚከናወንበት አውድ ማለት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ አካላዊ መቼቱ፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና፣ ክዋኔውን የሚገዙባቸው የተለያዩ ህጋጋት፣ በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለው ተግባቦት፣ የክዋኔው አተረጓጎም የሚከናወንበት መመሪያ፣ በየደረጃው የሚከናወኑ ድርጊቶችና ተግባራት፣ ቅደም ተከተል

ስለ ክዋኔ እና ስለ አውድ ተኮር ጥናት ምንነትና ዝምድና ከላይ የቀረበውን ያህል ከተባለ በአውድ ውስጥ ስለሚጠናው አንድ የክዋኔ ዓይነት ስለሆነው ክብረ በዓል ምንነት መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ ክዋኔን እና ክብረ በዓልን ነጣጥሎ ማየት እንደማይቻል ሁሉ ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው ማለትም አይደለም፡፡ ምክንያቱም ክዋኔ ማለት ማንኛውም በሰው ልጅ የሚከናወኑ ድርጊቶችን ሁሉ የሚያጠቃልል ሲሆን ክብረ በዓል ግን የተመረጡ የሰው ልጅ ስሜቶችን፣ ሃሳቦችን፣ እምነቶችን ምክንያት በማድረግ የሚቀርቡ ክንውኖችን የያዘ በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ውስጥ የሚጠና ነው፡፡ በመሆኑም ክዋኔ የሰውን ህይወት በሰፊው የሚያሳይ ሲሆን ክብረ በዓል ደግሞ የተወሰኑ የህይወት መልኮችን የሚገልጽ በመሆኑ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### 2.1.3 የክብረ በዓል ምንነት

የክብረ በዓልን ወይም የክበራን ምንነት የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል፡፡ ክብረ በዓል ማለት ሃይማኖታዊ ድርጊቶች የተሸከሟቸውን ጉዳዮች የመግለፅ ስነ-ስርዓት ሲሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ ወይም ከዘመን ዘመን የሚዘልቅ ስርዓተ ክዋኔ ነው በማለት የገለጹት (አሳንቴ እና ማዛማ፣ 2009፣ 575) ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ክብረ በዓልና ሃይማኖት ፈጽሞ ተነጣጥለው የማይቆሙ መሆናቸውን እና መነሻቸው ወይም ምንጫቸው ሚት እንደሆነ (ራፓፖርት፣ 1999፣ 158) ገልጸዋል፡፡ ይህም ሲባል ማህበረሰቡ እያንዳንዱን ክብረ በዓል ለማክበር የሚሰጠው ሃይማኖታዊ ምክንያት አለው፡፡ በየሃይማኖቱ ያሉ ቅዱሳን ተዓምር የፈጸሙበትን ቀንና የፈጸመውን መልዓክ ለማስታወስና ለማክበር ሲሉ የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ በመሆኑም ክብረ በዓል ማለት ሚት በድርጊት የሚገለጽበት ነው የሚል አቋም አለው፡፡

በርካታ ክብረ በዓሎች በድርጊት ስለሚገለጹ ማህበረሰቡ በቀላሉ የሚረዳቸውን ጉዳዮች ያገኝባቸዋል፡፡ ሁሉም ክበራዎች የሚቀርቡበት የራሳቸው የሆነ አውድ ይፈልጋሉ፡፡ አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ከሚያከናውናቸው ሰፊ ስርዓተ ክዋኔዎች ውስጥ በርካታ ስነ-ስርዓቶች ተጨምረው ይቀርባሉ (ቤል፣ 1997፣ 172)፡፡ ማህበረሰበቡ በህይወት ሲኖር የሚያልፍባቸውን ልዩ ልዩ ደረጃዎች ለማክበር እንዲሁም ለፈጠረውና እንዲኖር ላደረገው አምላክ ምስጋና ለማቅረብ ወይም ለመማጸን ሲል ክብረ በዓላትን በተለያዩ ክንውኖች ያከብራል፡፡ ባጠቃላይ ክብረ በዓላት ደስታን፣ ሀዘንን፣ ጭንቀትን፣ ብሶትንና ሌሎች ስነ-

ልቦናዊ ስሜቶችን በመግለጽ እረፍት ለማግኘት ይከናወናሉ፡፡ በመሆኑም ሰው እስካለ ድረስ ክብረ በዓል አለ፡፡ ተሳታፊዎች ወይም ታዳሚዎች በኑሯቸው የሚጠቀሙባቸውንና የሚመሩባቸውን እሴቶችና ተምሳሌቶች መግለጫ አድርገው ይጠቀሙባቸዋል (ቤል፣ 1997፣ 171)፡፡

አሁን ላይ ያሉ የስነ-ሰብና የባህል ተመራማሪዎች ትኩረታቸውን የክብረ በዓልን ምንነት መግለጽና መተርጎም ላይ አድርገዋል፡፡ እንደ ምክንያት የሚያነሱትም በርካታ አዳዲስ ንድፈ ሀሳቦች ምንጫቸው ማህበረሰቡ የሚያብራቸው ክብረ በዓላት ናቸው የሚል ነው፡፡ ንድፈ ሀሳቡን ለመረዳት ክበራውን የሚያከናውኑ ሰዎች ለስነ-ስርዓቱና ለማህበራዊ ደንቡ ያላቸው አመለካከት እንዲሁም ከዋኜው የሚፈልጋቸው ህጎች ሁሉ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች እንደሆኑ የጠቆሙት (ኮርሚክ እና ኋይት፣ 2011፡1105) ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ (አሳንቴ እና ማዛማ፣ 2009፣ 575) የአንድ ማህበረሰብ ክብረ በዓል ማህበረሰቡ ህይወቱን፣ ኑሮውን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የግድ አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር የተሳታፊዎችን ስሜታዊና ስነ-ልቦናዊ ጥንካሬ የሚያዳብር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡[8] ማህበረሰቡ ክብረ በዓላትን የሚያከብረው በዕለቱ ወይም በስነ-ስርዓቱ የሚታሰበው መንፈስ አንዳች ነገር ያደርግልኛል ወይም አድርጎልኛል ብሎ ሲያስብና ሲያምን ነው፡፡ ይህም በትርብ በማያየው አምላኩ እንዲተማመን ከማድረጉም በላይ ህልውናውን ጠብቆ እንዲኖር ያስችለዋል፤ ከትውልድ ወደ ትውልድም ጸንቶ እንዲዘልቅ ይረዳዋል፡፡

የአንድን ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ እምነት፣ የሚያስደስተውንና የሚያሳዝነውን ነገር ለመለየትና ስሜቱን የሚገልጽበትን መንገድ ለመረዳት ብሎም ማንነታቸውን ለማወቅ በህይወት ዘመናቸው የሚያከብሯቸውን ክብረ በዓሎች ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ በማን፣ መቼ፣ ለምንና እንዴት እንደሚከበሩ በማጥናት ማንነቱንና የሚኖርበትን አለም መረዳት ይቻላል፡፡

[8] "Rituals are vital. When the life and safety of a community are threatened, rituals can psychologically and emotionally strengthen the community's member by creating a sense of order."(Asante and Mazama, 2009፣ 575)

### 2.1.4 የክብረ በዓል ባህሪያት

ስለ ክብረ በዓል ባህሪያት (ሳልሞን፣ 2004፣ 321) በተቀመረ ቋንቋ ወይም ድርጊት የሚቀርብ፣ የሚደጋገምና የማይለዋወጥ መዋቅር ያለው የፎክሎር ቅርጽ ነው በማለት ከገለጹ በኋላ እያንዳንዱ ክብረ በዓል በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደውን ቅርጽ፣ ስርዓትና ደንብ ሳይለውጥ እየተደጋገመ ለዘመናት መዝለቅ የሚችል እንደሆነም ጨምረው አስረድተዋል፡፡ በመቀጠልም ሰዎች በተናጠል ወይም በቡድን በመሆን ተምሳሌታዊ እንቅስቃሴዎቻቸውን የሚገልጹበት በመሆኑ የክዋኔን ባህሪያት እንደሚጋራ እና እነሱም የሚከተሉት መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

1. መዋቅራዊነት፡-መዋቅራዊነት ክብረ በዓሉ የአከባበር ሂደት ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ የሚያልፍባቸውን ደንቦች ያመለክታል፡፡ ክብረ በዓሎች እንደሚከናወኑበት ምክንያትና አላማ በተለያየ መንገድ ቢፈጸሙም የሚከተሏቸውና የሚመሩባቸው ደንቦች አሏቸው፡፡ በክዋኔው የሚቀርቡ ንግግሮች፣ ዜማዎች፣ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች የሚተገበሩት ማህበረሰቡ ባወጣቸውና በሚመራባቸው ህጎች አማካኝነት መሆኑን ያመለክታል፡፡
2. ቅደም ተከተላዊነት፡- በክብረ በዓሉ የሚፈጸሙ ጉዳዮች የሚቀርቡት በቅደም ተከተል ነው፡፡ መጀመሪያ የሚባለው በቅድሚያ መባል አለበት፣ ቀጥሎ የሚደረገውም በጊዜው፣ መጨረሻ የሚፈጸመውም እንዲሁ መጨረሻ መቅረብ አለበት፡፡ በመዋቅሩ የተቀመጡት ደንቦችና ስርዓቶች በሙሉ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንደሚቀርቡ ያሳያል፡፡
3. ተደጋጋሚነት፡- የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ከበራ ተደጋጋሚነት በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የጊዜ ድግግሞሽን የሚያመለክት ሲሆን በርካታ ስርዓተ ክዋኔዎች በሳምንት፣ በወር ወይም በአመት ተደጋግመው ይከናወናሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የጉዳዩን ተደጋጋሚነት ይጠቁማል፡፡ በዋናነት ለአንድ ሰፊ ጉዳይ በሚፈጸም ከበራ ውስጥ የሚቀርቡ ጉዳዮች ሁልጊዜም ተደጋግመው ይፈጸማሉ፡፡
4. ታዳሚ፡- ክብረ በዓል በተፈጥሮው ታዳሚ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም አድማጭ፣ ተመልካች ወይም የኔ ብሎ የሚከታተል ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ያስፈልጋል፡፡

በአብዛኛው የሚከወነው ጉዳይ የራሱ የማህበረሰቡ በመሆኑ ያለ ታዳሚ ህልውና የሌለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

5. ውጤት፡- ሰዎች ሁሉንም ክብረ በዓሎች የሚፈጽሟቸው አንዳች ውጤት ላይ ለመድረስ ነው፡፡ ሆኖም ግን ብዙዎቹ የሚከበሩት አንድ ሰው ወይም ማህበረሰብ ራሱን ለማክበር፣ ከጭንቀት ለመገላገልና ስነ ልቦናዊ እርካታን ለማግኘት ሲል በመሆኑ ውጤቱ ላይቆጠርና ላይጨበጥ ይችላል፡፡

6. ቅዱሳዊነት፡- በሁሉም ማህበረሰብ የሚከናወኑ ክብረ በዓላት ግለሰቡን ወይም ቡድኑን ከኔጋቲቭ ወደ ፖዘቲቭ እንዲሁም ከሚገኙበት ደረጃ ወደተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግሩ ናቸው፡፡

የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮችን ምክንያት በማድረግ የሚከበሩ በዓላት ማህበረሰቡ ርኩስ ብሎ ከሚገፋቸው ተግባራት ያነጻሉ፡፡ ከከበራው በኋላ ሰዎች በነጻነት ወደማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ፣ ማህበረሰቡ ወደሚፈልገው ጥሩ ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡ ለምሳሌ፡- አንዲት እናት በወለደች በአስረኛው ቀን የምትጠመቀው፣ ህጻኑ ክርስትና የሚነሳው፣ ሰዎች በሰርግ የሚያገቡት፣ እርጅና ሲመጣ የሚቆርቡት፣ የሚመነኩሱት ወደ ጥሩ ደረጃ ሽ ቸለመሸጋገርና ቅድስና ለማግኘት ሲሉ ነው፡፡

## 2.1.5 የልደት፣ ሰርግና ለቅሶ ከበራ ሽግግር ደረጃዎች

እንደ ዠኔፕ ገለጻ ሁሉም የህይወት ዘመን ዑደቶችን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ከበራዎች በሶስት ተከታታይ ደረጃዎች ያልፋሉ፡፡ እነዚህ ደረጃዎች መነጠል፣ መሸጋገር እና አዲስ ማንነት ማግኘት ይባላሉ፡፡ ከዠኔፕ ሀሳብ በመነሳት የደረጃዎች ምንነትና ባህሪ በሚከተለው መንገድ ተቀምጧል፡፡

### 2.1.5.1 መነጠል[9]

መነጠል በህይወት ሽግግር ሂደት መጀመሪያ የሚከሰት ሲሆን አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ከነበረበት የአኗኗር ስልት፣ ሚና፣ ማህበራዊ ደረጃ እና ማንነት መውጣት ወይም መለየት ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ያለበትን ደረጃ ከሚያመለክቱ ሚና፣ ማንነት እና ማህበራዊ ደረጃ

[9]Separation/Pre Liminal

ውጭ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ወደ ሌላ ማንነት ለመሸጋገር ጉዞ የሚጀመርበት ደረጃ በመሆኑ ነው፡፡ የማህበረሰቡ አባል የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን የመነጠሉን ስነ-ስርዓት የሚፈጽምበት መንገድ ከባህል ባህል ይለያያል፡፡

በብዙ ባህሎች እዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች ሀገራቸውን በመልቀቅ፣ ልዩ ልዩ ቅጣቶችን በመቀበል፣ ረጅም ጉዞ በመጓዝ፣ የአለባበስ ስልታቸውን በመቀየር፣ ጸጉራቸውን በመቆረጥ፣ የነበራቸውን ስም በማጣት ሊያሳልፉት ይችላሉ፡፡ ሰዎች በመነጠል ደረጃ ላይ እያሉ በሚፈጽሟቸው ክዋኔዎች የራሳቸውን፣ የቡድናቸውን፣ ብሎም የማህበራቸውን ማንነት፣ አስተሳሰብ እንዲሁም ርዕዮተ ዓለም ይረዳሉ፡፡ ባጠቃላይ ማህበራቸው የተዋቀረበትን ባህልና ራሳቸውን ያያሉ (ሳልሞን፣ 2004፣ 311)፡፡

የመነጠል ጽንሰ ሀሳብ የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ሽግግር ደረጃ ላይ ያለው ገጽታ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ለምሳሌ፡- ልደትን ብንመለከት አንድ ህጻን ከእናቱ ማህጸን ሲወለድና ወደ ማህበረሰቡ ሲቀላቀል የነበረበትን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ይተዋል፡፡ ስለሆነም ከሚያውቀውና ከለመደው አለም ሙሉ በሙሉ ይነጠላል፡፡

በሰርግ ስነ-ስርዓት ሰዎች ከብቸኝነት ወደ ባለትዳርነት ለመሸጋገር ከነበሩበት የቀደመ ህይወት ተነጥለው ሌላ ህይወት ይገባሉ፡፡ እንዲሁም ሰዎች እድሜአቸው እየገፋ ሲሄድ የሚፈጽሟቸውና የሚከሰቱባቸው እንደ ቁርባን፣ ምንኩስና፣ ምናኔ፣ ሞት እና ሀዘን የመነጠል ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ የሚጠቃለሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡

### 2.1.5.2 ሽግግር[10]

በህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር አከባበር ሂደት ውስጥ ከመነጠል ቀጥሎ የሚመጣው ሽግግር ይባላል፡፡ ይህም በፊት የነበረው ማንነት ቀርቶ ሌላ አዲስ ማንነት ለማግኘት የሚደረገውን ዝግጅት ያመለክታል፡፡ ስርዓተ ክዋኔ የሚፈጸምለት ግለሰብ ወይም ቡድን እዚህ ደረጃ ላይ ሲሆን ከነበረው ማንነትም ሆነ ወደፊት ከሚሆነው መካከል ላይ ስለሚሆን በአብዛኛው ግራ የመጋባት ስሜት ይታይባቸዋል፡፡ ቪክተር ተርነር "ሽግግር" እንደሌሎቹ ደረጃዎች (መነጠልና አዲስ ማንነት ማግኘት) መዋቅሩን በግልጽ ማሳየት አስቸጋሪ ነው

[10] Transition/Liminal

በማለት ይጠግታል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በሽግግር ጊዜ በፊት ከነበሩትም ሆነ ወደፊት ከሚሆኑት ማንነት ውጪ በመሆናቸው እንደ በይነ-መዋቅር[11] ወይም በመነጠልና አዲስ ማንነት በማግኘት መካከል የሚከሰት ሁነት ነው (ተርነር፡ 1977፡ 95)፡፡

የሰው ልጅ ለውጦች የሚከሰቱባቸው ሁነቶች በአጭር ጊዜ የሚፈጸሙ ሳይሆኑ ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ናቸው፡፡ ሰዎች ከመነጠል ቀጥለው የሽግግር ደረጃ ላይ ሲደርሱ በፊት ከነበሩበትና ወደፊት ከሚሆኑት ማንነት ውጪ ይሆናሉ፡፡ ተሳታፊዎች በዚህ ደረጃ ከምግብና ከመጠጥ ሊታቀቡ፣ የአነጋገር ለዛ ሊቀይሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ሌላ አዲስ ማንነት ለማግኘት የሚደረግ ዝግጅት ሽግግር ይባላል፡፡

### 2.1.5.3 አዲስ ማንነት ማግኘት[12]

ይህ ደረጃ የመጨረሻው የሽግግር ደረጃ ሲሆን የተነጠሉት ሰዎች አዲስ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ይዘው ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀሉበት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ይህንን ደረጃ በብዛት ልዩ ስነ-ስርዓት በማዘጋጀት ያከብረዋል፡፡ ሰዎች እዚህ ደረጃ ላይ ካልደረሱ በስተቀር ከበራ አይካሄድም፡፡ በከበራው ስነ-ስርዓት ጊዜ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ አዲስ ስያሜ፣ አዲስ ማንነት፣ አዲስ የአለባበስ ስልት፣ አዲስ ማህበራዊ ሚና ይዞ ወደ ማህበረሰቡ ይመለሳል፡፡ ልዩ ልዩ ስጦታዎችም ሊበረከቱላቸው ይችላል፡፡ የከበራው ስነ-ስርዓት ሲፈጸም ግለሰቦች፣ የተለያዩ ቤተሰቦች እንዲሁም የማህበረሰቡ አባል በሙሉ ሊገኙ ይችላል (ሳልሞን፣ 2004፣ 312)፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ክፍል የህይወት ዘመን ዑደት ደረጃ ሽግግሮች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ይዳሰሳሉ፡፡ የጥናቶች ጠንካራ ጎን፣ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ የታዩ ክፍተቶችና ይህ ጥናት የሚሞላቸው ጉዳዮች ይተነተናሉ፡፡

የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ላይ ያተኮረና ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ጥናት ማግኘት ባልችልም ተቀራራቢ የሆኑ ሁለት በኢትዮጵያ ስነ

[11] በይነ-መዋቅራዊ፡-"Enterstructural Situation" ወይም "Betwixt and Between" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ለመተርጎም የሞከርኩበት ሲሆን መነጠል፣ ሽግግር እና አዲስ ማንነት ማግኘት ከሚባሉት ሶስት የደረጃ መዋቅሮች የሽግግር ደረጃን ያመለክታል፡፡ በሁለቱ ገልጽ መዋቅሮች መካከል የሚመጣ ወሳኝ ደረጃ ነው፡፡
[12] Encorporation/Post Liminal

ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተሰሩ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ፣ ሶስት በስነ-ሰብና ስነ-ማህበረሰብ ትምህርት ክፍሎች የተሰሩ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡

የመጀመሪያው አየለ ሊሬ በ1986 ዓ.ም ለአፕላይድ ሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል ቢ.ኤ ዲግሪ ለማሟላት የተሰራ ሲሆን በሀድያ የህይወት ዘመን ሽግግር[13] ላይ የተካሄደ ምርምር ነው፡፡ ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች የከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን አላማ እና የጥናቱን ዘዴ የያዘ ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉትን አላማዎች የያዘ ነው፡፡ በሃድያ ጎሳ የሚተገበሩ ባህላዊ ልምዶችን ለማስተዋወቅ፣ የሃድያን ባህል ለመጠበቅ፣ በሃድያ ባህል የሚዘወተሩ ጎጅ ልማዶች ዙሪያ እርምጃ ለመውሰድ እና በዚህ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ ሌሎች ምሁራን ፍንጭ ለመስጠት የሚሉ ናቸው፡፡

አየለ እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ክፍት ቃለ መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ በነዚህ ዘዴዎች አማካኝነት የሰበሰባቸውን መረጃዎች በገላጭ የመተንተኛ ስልት ተጠቅሞ እንደተነተነ ጠቁሟል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ከልደት እስከ ሞት ያሉ የሰው ልጅ የደረጃ ሽግግሮችን ከክብረ በዓላቸው ጋር ተንትኖ ያስቀመጠበት ክፍል ነው፡፡ የልደት ስነ-ስርዓት በሀድያ፣ የህጻን አቀባበልና የጾታ ምርጫ፣ የድህረ ወሊድ ስነ-ስርዓት እና የስም ማውጣት ስነ-ስርዓት በሚሉ ርዕሶች ተከፋፍሎ ተተንትኗል፡፡

በምዕራፍ ሶስት የጉርምስና ስነ-ስርዓቶችና የደረጃ ሽግግር በሚል ርዕስ ስር በሃድያ ባህል ከጉርምስና ጋር ተያይዘው የሚከናወኑ ሪቺዋሎች ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ አራት የሰዎች የአዋቂነት ደረጃ ሲሆን በዚህ ክፍል የቀለበትና[14] የሰርግ ስነ-ስርዓት ልማድ በሃድያ ባህል በሚል ርዕስ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች ተብራርተዋል፡፡ እንዲሁም እዚህ ደረጃ የደረሱ ሰዎች ማህበራዊ ደረጃ እና ሚና ምን እንደሆነ ያሳየበት ክፍል ነው፡፡ በምዕራፍ አምስት የሽምግልና እና የሞት ስነ-ስርዓቶችን ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ሞት ያሉ ሂደቶች ቀርበውበታል፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍ ዘመናዊ ተቋማት በባህላዊ ክዋኔዎች ላይ ያስከተሏቸው ተጽዕኖዎች በሚል ርዕስ ዘመናዊ ስርዓተ ትምህርት፣ ሀይማኖታዊ ተቋማት፣ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት፣ የአዳዲስ ማህበራት መስፋፋት፣ የልዩ ልዩ ማህበራዊ፣

[13] የጥናቱ ርዕስ፡-"The Rites of Passage Among Hadya Ethnic Group" የሚል ነው፡፡
[14] Betrothal

ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ ተቋማት በርካታ ባህሎች እንዲለወጡ የየራሳቸውን አሻራ አሳርፈዋል፣ በማለት ጥናቱን አጠናቋል፡፡

የአየለ ጥናት እንደ መጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ጥሩ የሚያስብሉ በርካታ ነጥቦችን አንስቷል፡፡ ሆኖም ይህንን ጥናት እንደ ፎክሎር ተመራማሪ ከተጠቀሱት አላማዎች መካከል የሃድያን ባህል ለመጠበቅ የሚለውና በባህሉ በሚተገበሩ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሚሉት ተገቢ ሆነው አላገኘኋቸውም፡፡ ምክንያቱም ባህል በባህሪው ተለዋዋጭ በመሆኑ ቢጠናም ባይጠናም መለወጡ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ይህ አላማ የተሰነዘረው የባህልን ባህሪ ካለመረዳት ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ አላማ የማህበረሰቡን ባህል በማውጣት ተንትኖ ማሳየት እንጅ ባህሉን ጥሩ ነው ወይም ጥሩ አይደለም ብሎ መፈረጅ አይደለም፡፡ ስለዚህ በዚህ መንገድ ማየቱ ተገቢነት የሌለው ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

በሁለተኛነት የሚጠቀሰው ጥናት የአልማዝ ኤጀርሶ ሲሆን በአፕላይድ ሶሲዮሎጂ ትምህርት ክፍል በ1986 ዓ.ም ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የተሰራ ነው፡፡ የምርምሩ ትኩረት በኦሮሞ ማህበረሰብ የህይወት ሽግግር[15] ላይ ነው፡፡ ይህ ጥናት በሶስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው፡፡ በዋናነት ልደት፣ ሰርግና ሞት በሚሉ ርዕሶች የቀረበ ሲሆን በስራቸው ተያያዥ የሆኑ ንዑስ ርዕሶችን አካቶ በዝርዝር ያቀረበችበት ጥናት ነው፡፡

ይህ ጥናት የተጠቀሰው አካባቢ ማህበረሰብ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮችን ለመረዳት፣ የማህበረሰቡን ባህል ጠብቆ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ፣ ከጊዜ መለወጥ ጋር ተያይዘው የመጡ የባህል ለውጦችን ለማሳየት፣ እንዲሁም በተጠኝውና በሌላው ማህበረሰብ መካከል ያለውን የባህል ተመሳስሎና ልዩነት ለማሳየት እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ አልማዝ መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመችባቸው ዘዴዎች ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ በካልኣይ የመረጃ ምንጭነት ደግሞ ተያያዥነት ያላቸው መጽሐፍትንና መጣጥፎችን እንደሆነ ገልጻለች፡፡

ሶስተኛው ትኩረት የተካሄደበት ጥናት በ1991 ዓ.ም በአለማየሁ በላይ የተጠናው ሲሆን ያተኮረው በሲዳማ ማህበረሰብ የህይወት ሽግግር[16] ላይ ነው፡፡ የተሰራውም ለሶሲዮሎጂ እና

[15]የጥናቱ ርዕስ "The Rites of Passage of Oromo People in Seyyo District of Qellem" የሚል ነው፡፡
[16]የጥናቱ ርዕስ "The Rites of Passge in the Sidama society" የሚል ነው፡፡

ሃሳቦችን በማንሳት ወሊድና ገለብ በተለያዩ አካባቢዎች ያላቸውን ገጽታ በማሳየት በኩል የተሻለ ቢሆንም ጠባብ መሆኑና በአንድ ንድፈ ሀሳብ ተደግፎ አለመጠናቱ ድክመት ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ዋናው ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን ዘዴ በዋናነት መጠቀም ከፎክሎር አውዳዊነትም ከሚጠናው ጉዳይ አንጻር አይመከርም፡፡ በእርግጥ ልደትና ሞት በታቀደው ቀንና ሰዓት የማይፈጸሙና የማይቀሩ የህይወት ዘመን ውዶቶች ቢሆኑም በነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የማህበረሰቡን እውቀት ለመረዳት ተመራጩ ዘዴ ከዚህ ይልቅ ቃለ መጠይቅን በመጠቀም ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ያስችላል፡፡

የመጨረሻው ቅኝት የተደረገበት ጥናት በየኔአሳብ የሰራህ በ2004 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የተሰራ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ "የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ፎክሎራዊ እይታ በፍኖተ ሰላም አካባቢ" ይሰኛል፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው አላማ በፈኖተ ሰላም አካባቢ የሚገኙ የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ምን እንደሚመስል ማሳየት የሚል ነው፡፡ እንዲሁም የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎችን ጨምሮ ይዟል፡፡ በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ተደጋግመው የሚከሰቱ የህይወት መገለጫዎች ምን ምን እንደሆኑ መጠቆም፣ የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቆይታቸው የሚያልፉባቸውን ደረጃዎች ማሳየት፣ የቆሎ ተማሪዎች ስለ ማህበረሰቡ፣ ቀሪው ማህበረሰብ ስለ እነሱ ያለውን አለመለካከት መግለጽ፣ የቆሎ ተማሪዎች በገጸ ባህሪነት የሚሳሉባቸው ተረቶች ይዘታቸው ምን ምን እንደሆንና ከህይወታቸው ጋር ያለውን ማመልከት የሚሉ ናቸው፡፡

ዝርዝር አላማዎች ወደ ጥያቄ ተቀይረው የምርምር ጥያቄዎች ሁነው ቀርበዋል፡፡ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ነው፡፡ እንዲሁም በገላጭና በትርጓሜ መልክ እንዳቀረበ ገልጿል፡፡ ጥናቱ ፎክሎራዊ በመሆኑ እነዚህን አላማዎች ከፎክሎር የጥናት መስክ አንጻር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የጥናቱ አላማ የቆሎ ተማሪዎችን ህይወት በፎክሎር እይን ማየት ቢሆንም ከዋናው አላማ ጀምሮ ከአንዱ በስተቀር ዝርዝር አላማዎችም ተገቢነት የሌላቸው ሁነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ምክንያቱም ትኩረታቸው ፎክሎር ሳይሆን የትምህርት ደረጃቸው ምን እንደሚመስል፣ የህይወት መገለጫቸውን መጠቆም፣ ማህበረሰቡ ለነሱ ያለው አመለካከት ምን እንደሆነ ማሳየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ፎክሎራዊ እይታ ብሎ ከመጠቅለል ይልቅ ከተጠኝዎች

ህይወት ጋር የሚሄዱ ዘውጎችን በመምረጥ ጥናቱን ቢያካሂድ የተሻለ ግኝት ላይ መድረስ ይችል ነበር፡፡

የዚህ ጥናት ሌላ ድክመት ሆኖ ያገኘሁት የክለሳ ድርሳናት ክፍል ነው፡፡ ክለሳ ድርሳናት የአንድን ጥናት ትኩረት በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ምን እንደሚመስል የሚያሳይና ወደ ትንተናው የሚመራ መሆን ሲገባው ይህ ግን የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች ከማስቀመጥ ያለፈ ምንም አይነት የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ እና ጽንሰ ሀሳባዊ ምንነት አላስቀመጠም፡፡ በመሆኑም እንደ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ምርምር ብዙ ነገሮች የሚጎድሉት ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

ባጠቃላይ የእኔ ጥናት ከላይ ቅኝት ከተደረገባቸው ጥናቶች በሚከተሉት ነጥቦች ይለያል፡፡ የህይወት ሽግግሮችን ሪቿዋል ከማሳየትም ባሻገር በሪቿዋሉ አፈጻጸም ላይ የሚመጡ ስነ-ቃላዊ አገላለጾች ይዘት በመተንተንና በመተርጎም የማህበረሰቡን እውቀት የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲሁም የሪቿዋሎችን አፈጻጸም ከክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንጻር እና ከሪቿዋል ጽንሰ ሀሳቦች አንጻር አውዳዊ ትንታኔ ማድረግ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የተሻለ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3 የፍኖተ ሰላም አካባቢ ዳራዊ መግለጫ

በፎክሎር ጥናት ምርምር የተካሄደበትን አካባቢና ማህበረሰብ አጠቃላይ ገጽታ ማስተዋወቅ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም የክብረ በዓላትን አከባበር ለመረዳት የማህበረሰቡን እምነት፣ ባህል መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የፍኖተ ሰላም አካባቢን መልካዓ ምድራዊ አቀማመጥና የህዝብ ብዛት፣ ሃይማኖት፣ መተዳደሪያ፣ በአካባቢው የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች እንደሁም የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባህል ምን እንደሚመስል መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የቀረቡበት ምክንያት ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ማለትም ከአካባቢው የህይወት ሽግግር ደረጃዎች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ስላላቸው ነው፡፡

ፍኖተ ሰላም ከተማ ከአዲስ አበባ በ387 ኪ.ሜ ከባህር ዳር ደግሞ 180 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ፍኖተ ሰላም በከተማነት ከመቆርቆሯ በፊት አሁን ያለችበት ቦታ “ጎንጅን” ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡ በከተማነት ከተቆረቆረች በኋላ ደግሞ “ወጀት” በሚል ስያሜ ስትጠራ ኖራለች፡፡ ቀጥሎም በከተማዋ የሚገኘውን ላህ ወንዝ ስም በመጨመር “ላህ ወጀት” በመባል ስትጠራ ቆይታለች፡፡ ከዚያም በ1933 ዓ.ም በጣሊያን ወረራ ወቅት ተዳግዊ ኃይለ ሥላሴ እና አርበኞቻቸው ከሱዳን ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ላህ ወጀት በተባለችው ቦታ አርፈው ስለነበር እና ቦታውም ሰላም ስለነበር “ፍኖተ ሰላም” ብለው እንደሰየሙት ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ትርጉሙም የሰላም መንገድ እንደማለት ነው፡፡

ፍኖተ ሰላም ከተማ ለብዙ ዓመታት በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል አንዱ የሆነው የጃቢ ጠህናን ወረዳ አስተዳደር በመሆን ስታገለግል ብትቆይም ከ1996 ዓ.ም ወዲህ ግን ለአስተዳደር ያመች ዘንድ በሶስት የከተማና በሁለት የገጠር ቀበሌዎች ተከፋፍላ በከተማ አስተዳደርነት እያገለገለች ትገኛለች፡፡ ሌሎች 37 ያህል ቀበሌዎች ደግሞ በጃቢ ጠህናን ወረዳ ስር ይተዳደራሉ፡፡ ክፍፍሉም የተካሄደው ለአስተዳደር ያመች ዘንድ እንጂ የተለየ ባህልም ሆነ የአኗኗር ስልት ወይም መልከዓምድራዊ አቀማመጥም ኖሮ እንዳልሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች እና የወረዳው የአስተዳደር ሰራተኞች ይናገራሉ፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት ፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደርና የጃቢ ጠህናን ወረዳ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ የፍኖተ ሰላም አካባቢ መልካዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡ የፍኖተ ሰላም ከተማ አስተዳደር በሁሉም አቅጣጫ የጃቢ ጠህናን ወረዳ ቀበሌዎች ያዋስኗታል፡፡ የጃቢ ጠህናን ወረዳ ደግሞ አምስት አጎራባች ወረዳዎች ያዋስኗታል፡፡ በስተሰሜን ሰከላ ወረዳ፣ በስተደቡብ ደንበጫ ወረዳ፣ በስተምስራቅ ደጋ ዳሞት ወረዳ እና በስተምዕራብ ቡሬ ወረዳዎች ያዋስኗታል፡፡

ከወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽህፈት ቤት በተገኘ መረጃ መሰረት 65% የሚሆነው የአካባቢው የመሬት አቀማመጥ ሜዳማ፣ 15% የሚሆነው ተራራማ፣ 15% የሚሆነው ወጣገባማ ሲሆን ቀሪው 5% ደግሞ ገደላማ የበዛበት ነው፡፡ የአካባቢው የአየር ንብረትም 88% የሚሆነው ወይና ደጋ ሲሆን 12% ያህሉ ደግሞ ቆላማ የአየር ንብረት አለው፡፡ ከወረዳው ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በ2002 ዓ.ም በተደረገው የቤትና የህዝብ ቆጠራ መሰረት የአካባቢው አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 317877 እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ በአካባቢው ከሚኖረው ህዝብ መካከል 99% የሚሆነው የአማራ ብሄር ተወላጅ ሲሆን የመግባቢያም ሆነ የስራ ቋንቋም አማርኛ ነው፡፡

የአካባቢውን ህዝብ ሃይማኖት ስንመለከት 99% የሚሆነው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ነው፡፡ ቀሪው 1% ያህሉ የእስልምና፣ የፕሮቴስታንት እና የካቶሊክ እምነት ተከታይ ነው፡፡ በወረዳዎች ከሚገኙ ከ67 በላይ ጎጦች (ንዑስ የገጠር ቀበሌዎች) መካከል አንድ ጎጥ ብቻ የእስልምና ሃይማኖት ነው፡፡ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታይ የሆኑትም በብዛት በከተማ እንደሚገኙ ከወረዳው ቤተ ክህነት የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡ ወደ አስራ ስምንት የሚደርሱ ቤተ ክርስቲያኖች መምህር ተመድቦላቸው በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡

በአካባቢው ከሚኖረው ህዝብ መካከል 94% ያህሉ ህዝብ ኑሮ የተመሰረተው በግብርና ላይ ሲሆን በተጓዳኝ እንስሳት በማርባትና ንብ በማነብ ይተዳደራል፡፡ አስተራረሱም ባህላዊ አስተራረስ የተከተለ ነው፡፡ 6% የሚሆነው ደግሞ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተቀጣሪ በመሆንና በንግድ ስራ የሚተዳደር ነው፡፡ በአካባቢው እንደ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ አተርና ባቄላ የመሳሰሉት በብዛት ይመረታሉ፡፡ አካባቢው በአትክልትና ፍራፍሬ እና በሸንኮራ አገዳ ምርትም ተለይቶ ይታወቃል፡፡ በአካባቢው ከሚዘወተሩ ዋና ዋና ምግቦች መካከል ከበቆሎና ከጤፍ የሚዘጋጅ እንጀራ፣ ከአተርና ከባቄላ የሚዘጋጅ ሽሮ ወጥ እና ከገብስና፣ ከበቆሎና ከጌሾ የሚዘጋጅ ጠላ ይጠቀሳሉ፡፡

የወረዳዎች ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤቶች ታሪካዊ ቦታዎች በማለት ካስቀመጧቸው መካከል በጣሊያን ወረራ እንደተሰራ የሚነገርለት የጆርጌ ድልድይ፣ በጣሊያን ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያውያን አርበኞች መሽገውበት እንደነበር የሚነገርለት የዘውዴ ዋሻ፣ ከ200 አመት በላይ እንዳስቆጠረ የሚነገርለት ቀጥ ብሎ ከወጣ ተራራ አናት ላይ የሚገኘው የድንግራ ማሪያም ቤተ ክርስቲያን፣ በርካታ ልማታዊ ተግባራትን በማከናወን የሚታወቀው የአባ ጨው ገዳም፣ መኩድ ወታደራዊ ማሰልጠኛ፣ የጎቻ የተፈጥሮ ደን፣ ገራይ ግድብ፣ የላህ ወንዝ፣ የቀረር ቁስቋም ማርያም ገዳም የመሳሰሉት ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች እንደሚገኙ ተጠቁሟል፡፡

የአካባቢው ህዝብ በደስታም ይሁን በሀዘን ተረዳድቶና ተደጋግፎ የመኖር ባህል አለው፡፡ የተለያዩ የመገናኛና የመሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመፍጠር ተደጋግፎ ይኖራል፡፡ ማህበር፣ ጽጌ፣ ሰንበቴ፣ እቁብ፣ እድር እና የዘመድ ማህበር የመሳሰሉት ማህበረሰቡ የጋራ ኑሮውን ለማጎልበት የሚጠቀምባቸው ናቸው፡፡ በሀዘን ጊዜ የሟች እድርተኛና ወዳጅ ዘመድ ከቀብር እስከ ሳልስት ድረስ ከሀዘንተኞች አይለዩም፡፡ ቁርባኑንም ማህበርተኞች ተረዳድተው ያወጣሉ፡፡ በሰርግ ጊዜም አቶልቋይ[17] በመያዝ አስራጊውን በወጪም ሆነ በጉልበት ያግዛሉ፡፡ በተጨማሪም በማንኛውም ስራ ወቅት በጋራ የመስራት ባህል አላቸው፡፡

---

[17]አቶልቋይ- በአካባቢው አንድ ሰው ልጁን ደግሶ ሲድር ወዳጅ ዘመድ እህል ውሃ በመውሰድ በወጭም ሆነ በጉልበት የሚያግዙበት የመረዳጃ ዘዴ ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4 መረጃ ትንተና

የምንኖርባት አለም ጸንታ የቆመችው ከጊዜ ጋር በሚከሰቱ የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ዑደቶች ቅብብል እና ሂደት አማካኝነት ነው፡፡ የሰው ልጅ በአለም ላይ የተፈቀደለትን ያህል ጊዜ ኑሮ እስከሚለይ ድረስ የሚያልፍባቸው ወሳኝ የህይወት አጋጣሚዎች በርካታ ቢሆኑም በዚህ ጥናት የሚተኮርባቸው ልደት፣ ጋብቻና ሞት ናቸው፡፡ ይህ ክፍል ልደትን፣ ጋብቻንና ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚከበሩ ክብረ በዓላት በፍኖተ ሰላም አካባቢ እንዴት እንደሚከወኑ፣ የማህበረሰቡ አመለካከት ምን እንደሆነ እና አመለካከቱን በስነ-ቃል ክዋኔው አማካይነት እንዴት እንደሚገልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

### 4.1. የልደትና ክርስትና ስርዓት ክዋኔ

"ልደት" የሚለውን ቃል ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ውልደት፣ መውለድ፣ መወለድ፣ አወላለድ በማለት አስቀምጠውታል (ገጽ፣ 391)፡፡ ከዚህ ፍቺ በመነሳት ልደት የሚለው ቃል ከእርግዝና እስከ ክርስትና ድረስ ያለውን ሂደት እንዲወክል የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡

የልደት ክብረ በዓል የአንድን ህፃን ወደዚች አለም መምጣት ምክንያት በማድረግ የሚከናወን ሀይማኖታዊ ስነ-ስርዓት ነው፡፡ በብዙ ማህበረሰብ ልደት ከሌሎች ወደ ፊት ከሚደረሱባቸው ዑደቶች ሁሉ የመጀመሪያው ስለሆነ የበለጠ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ ልደትን ምክንያት በማድረግ እንደየባህሉ የተለያዩ ክብረ በዓሎች ይፈጸማሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ባልና ሚስቱ ለፍሬ ስለበቁ ነው (ግሪም፣ 1943፣16)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ በመነሳት የፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ልደትን ምክንያት በማድረግ በወሊድ ጊዜ ከሚያጋጥሙ ተፈጥሯዊ ሂደቶች ጋር ተያይዘው በቅደም ተከተል የሚተገበሩ በርካታ ባህላዊ ክዋኔዎች አሉ፡፡ የልደትን ሂደት ቅድመ ልደት፣ የወሊድ ጊዜ እና ድህረ ልደት የሚፈጸሙ ባህላዊ ክዋኔዎች በማለት በሶስት ደረጃዎች ከፍሎ ማየት የተሻለ ነው፡፡ የእርግዝና ጊዜ፣ የወሊድ ጊዜ እና ከወሊድ በኋላ እስከ ክርስትና ድረስ የሚከወኑ ድርጊቶች፣ ፋይዳ እና ፍቺ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

አንዲት እናት ነፍሰ ጡር መሆኗ ከተረጋገጠ በኋላ የእንቅስቃሴ፣ የአለባበስ፣ የአመጋገብ ለውጥ ታደርጋለች፡፡ የሚያምራትን ትበላለች፣ ትጠጣለች፡፡ ሰውነቷን ከሚጉዱ ከባድ ስራዎች መታቀብ አለባት፡፡ በእንጻሩ ሰውነቷን የሚገነቡ ምግቦችን መመገብ የለባትም፡፡ ከላይ የቀረቡት በእርግዝና ጊዜ የሚደረጉ ተግባራት ለህጻኑና ለወላጂ ጤንነት ሲባል እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

ነፍሰ ጡር እናት በእርግዝና ወቅት ያማራትን መብላት አለባት፣ የሽተታትም ምግብ ቀምር ያለበት ቦታ ተፈልጎ ትበላለች፡፡ ይህም ለተረገዘው ህጻን ጤንነት ሲባል ነው፡፡ የሸተታትንና ያማራትን ካልበላች ምልክቱ የህጻኑ ገላ ጥቁር ሁኖ ይወጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ምግቡ ወይም መጠጡ ባይገኝ እንኳ ፊት ለፊት የማይታይ የሰውነት ክፍሏ ላይ ቆንጠጥ ማድረግ አለባት፡፡[18] እናቶች የእርግዝና ጊዜያቸው እየተቃረበ ሲመጣ እናት ወይም የቅርብ ዘመድ ይጠብቃታል፡፡ ወልደው የማያውቁ ከሆነ እንዲህ ዓይነት ነገር ይገጥምሻል፣ እንዲህ ትሆኛለሽ እያለ ያለውን ሁኔታ የሚነግር የቅርብ ሰው ሰው ያስፈልጋታል፡፡

እናቶች በጭንነት ሶስት ጊዜ ያምጣሉ፡፡ የእንሽርት ውሃ ሲፈስ፣ ልጁ ከማህጸን ሲወጣ እና የእንግዴ ልጅ እንዲወርድ ያምጣሉ፡፡ በመውለድ ሂደት እያሉ ካህናት እንደ ድርሳነ ሩፋኤል፣ መልካ ሩፋኤል[19] በእለት ውሃ እየደገሙ ያጠምቋታል፣ እንድትጠጣ ያደርጓታል፣ ከወለደች በኋላም በትራሷ ይደረግላታል፡፡ በተጓዳኝ በአጋጣሚው የተገኘ ማህበረሰብ ትኩስ እንጀራ በመጋገር፣ ቡና በማፍላት፣ የተቀቀለ ተልባ እንድትጠጣ በማድረግ እመ ብርሃን[20] እንድትለመናቸው እና ምጧ እንዲቀልላት ሲባል የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወንዶች ቀበቷቸውን፣ ሴቶች ደግሞ መቀነታቸውን በመፍታት "እግዚኦ! እመ ብርሃን ተለመኝን!" እያሉ ከለመኑ የወላድ አምላክ እመ ብርሃን ከተፍ ትላለች፣ ወላዷም

[18]በቀን 8/8/2005 ዓ.ም ከቀኑ በ10፡30-12፡00 ሰዓት ከወይዘሮ ድንቃየሁ አለሙ ቀረር ቁስቋም በሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው የተደረገ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ እኒህ ሴት እድሜያቸው 52 አመት ሲሆን በአካባቢው ነፍሰ ጡር እናቶችን በማዋለድ ያታወቃሉ፡፡
[19]መልከ ሩፋኤል፡የሩፋኤልን መልክ የያዘ ሲሆን በወሊድ ጊዜ የማገላገል ሚና ከአምላክ ተሰጥቶታል፡፡ እንደ የልምድ ሀኪም የሚታይ ነው፡፡
[20]እመ ብርሃን፡የብርሃን እናት ማለት ሲሆን በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት አማኞች ዘንድ ብርሃን ማለት ክርስቶስ ነው፡፡በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ነፍሰ ጡር እናቶችን ታዋልዳለች (ታገላግላለች) ተብሎ ይታመናል፡፡ ለማርያም ያላቸውን ክብር ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ቃል እንደሆነ ከቃለ መጠይቁ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ትገላገላለች፡፡ ድንገት የእንግዴ ልጁ የቀረ እንደሆነ ደብተራዎች[21] ጉድጓድ ይቆፈርና የተለያዩ እጽዋቶች ሞቅ ባለ ውሃ ተቀቅለው ጉድጓዱ ውስጥ በመጨመር እንድትቀመጥበትና በማህጸኗ እንዲገባ እና እንዲወርድላት ያደርጋሉ፡፡

ሶስተኛው የወሊድ ደረጃ ልጅ ከእናቱ ማህጸን የሚለይበት ቅጽበት እና ከዚያ በኋላ የሚከናወኑ ክዋኔዎችን ያጠቃልላል፡፡ አዋላጇ[22] ህጻኑን በንጹህ ጨርቅ ከተቀበለች በኋላ እትብቱን ለክታ በተገቢ ቦታው ላይ ትቆርጣለች፡፡ የእንግዴ ልጅ ከወረደና ከተቀበረ በኋላ ወላዷ እና ህጻኑ ታጥበው ቅቤ ይቀባሉ፡፡ ወላዷ ቅቤ በምትቀባበት ጊዜ እናቶች ተሰብስበው እልል ይላሉ፡፡ እልልታው ለወንድና ለሴት ባይለይም የደስታቸው መጠን ግን የተለያየ ነው፡፡ በአብዛኛው ወንድ ልጅ ደም ይመልሳል[23]፣ ስም ያስጠራል፣ አደባባይ ይውላል፣ ለቤተሰቡ መመኪያ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ወንድ የተወለደ እንደሆነ በተለይ አባቱ ከፍ ያለ ደስታ ይሰማዋል፡፡ እንዲሁም እንደወንዱ ባይሆንም በቤተሰቡ ሴት ልጅ ከሌለ እና የሴትን ወርቅነት[24] የተረዱ የተለየ ደስታ ይሰማቸዋል፡፡ ደስታው እንደ ቤተሰቡ ቢወሰንም በብዛት ወንድ ሲወለድ ግን ቤተሰቡም ሆነ ማህበረሰቡ ይደሰታል፡፡

---

[21] ደብተራ፡ በአካባቢው የሚታወቁ ባህላዊ ህክምና የሚያውቁ ሰዎች በብዛት ደብተራዎች ናቸው፡፡ መድሃኒቱን የሚቀምሙትም ከተለያዩ እጽዋቶች ነው፡፡ የእንግዴ ልጅ የቀረ እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ለበርካታ በሽታዎች ፈውስ ያስገኛሉ፡፡

[22] አዋላጅ፡ በአካባቢው በብዛት የማዋለድ ድርሻ ያላቸው ሴቶች ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ወንዶችም ያዋልዳሉ፡፡ ወንዶች ከሆኑ የወላጇ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ገመናዋን ለመሸፈን ሲባል ነው፡፡

[23] ደም መላሽ፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በአንዳንድ አለመግባባቶች ምክንያት አንድ ሰው የሌላ ሰውን ነፍስ ሊያጠፋ ይችላል፡፡ በአካባቢው ባህል መሰረት የሰው ደም በከንቱ ፈስሶ አይቀርም፣ በቤተሰቡ ይመለሳለታል፡፡ ገዳዩ በሌላ አጋጣሚ ቢሞት እንኳን የገዳይ አባት፣ ወንድም፣ እኅት… በሚች ቤተሰብ ይገደላል፡፡ ሁኔታው ከልተመቻቸ ከረዥም አመታት በኋላ እንደገና ሊቀጥል ይችላል፡፡ ደም የሚመለሰው ሁሉጊዜም በወንድ (ህጻን ሊሆንም ይችላል) ነው፡፡ ሴትና መነኩሴ ፈጽሞ አይገደልም፡፡ ፈሪ ያሰኛል፡፡ በባህሉ ሰው መግደል ባይደገፍም ደም መመለስ ግን ግድ ነው፡፡ ካለበለዚያ በማህበረሰቡ ዘንድ ይናቃል፡፡ ደሙን የመለሰ እንደሆነ ግን ይደነቃል፣ ጀግና ይሰኛል፣ ደስታም ይሆናል፡፡ የሚገደል ዘመድ አዝማድ ከሌለው እንኳ በውሻው፣ በከብቶቹ መመለስ አለበት የሚል ብሂል አለ፡፡

[24] አንድ ፈላስፋ አንድ ሰው ወንድ ልጁን በጫንቃው (በትከሻው)፣ ሴት ልጁን ደግሞ በእግሯ እያስኳዛት ሲሄድ ያየዋል፡፡ ፈላስፋውም አንተ ሰው "ወርቅ በጭቃ ነብር በጫንቃ ይዘሃል" አለው፡፡ ይባላል በማለት የነገሩኝ መሪጌታ ስሜነህ ናቸው፡፡ መልዓከ ጥበብ መሪጌታ ስሜነህ አበበ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የምዕራብ ጎጃም ዞን ስብከተ ወንጌል ትምህርት ክፍል ሃላፊ ናቸው፡፡ ከሀላፊነታቸው ባሻገር ስለ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ስለ አካባቢው ባህል ጠለቅ ያለ እውቀት እንዳላቸውና እሳቸውን ብጠይቅ የተሻለ መረጃ እንደማገኝ የሚያውቋቸው ሰዎች ጠቁመውኛል፡፡ መሪጌታ ስሜነህ የሚኖሩት ፍኖተ ሰላም ከተማ ውስጥ ሲሆን ባለትዳርና የ62 አመት ዕድሜ ባለፀጋ ናቸው፡፡ ቃለ መጠይቁ የተካሄደው ሀሙስ ሚያዝያ 9/2005 ዓ.ም ከቀኑ 8፡53- 10፡20 ደቂቃ በመስሪያ ቤታቸው በመገኘት ነው፡፡

ኀንኳን ማሪያም ማረችሽ እየተባለች ትሳማለች፡፡ ለህጻኑም የአንቃር[25] ማንሻ ቅቤ እንዲውጥ ያውጡታል፡፡ እናቱም ጡት ታጠባዋለች፡፡ ከዚያም የማሪያም መሸኛ ገንፎ ተገንፍቶ ሁሉም ሰው ይበላል፡፡ በአንጻሩ ወላዶች ብዙ ካማጡ ወይም ብዙ ደም ከፈሰሳቸው እንደሰመመን ይወስዳቸዋል፤ ራሳቸውን ይስታሉ፡፡ ይህንን ሁነት ማህበረሰቡ ስራቂ[26] ክፉ መንፈስ እንደሆነ ያምናል፡፡ ወላዷን ከዚህ ክፉ መንፈስ ለመታደግ ጠገራ ብር ያስነክሷታል፤ ወንዝ ያሻግሯታል፤ በአጠገቧ ብረት ምጣድ ያንኳኳሉ፤ ጥይት ይተኩሳሉ፡፡ እነዚህ ክንውኖች ከሰመመን ይመልሷቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በአካባቢው ጠገራ ብር ከክፉ መንፈስ ይጠብቃል፤ ወንዝ በማሻገር ክፉ መንፈስን ማባረር ይቻላል፤ ክፉ መንፈስ የብረት ድምጽ አይወድም ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲሁም ስራቂ በወላዶች ደም ገብቶ ይይዛቸዋል የሚል አመለካከት ስላላቸው እንዲህ አይነት ክንውኖችን ይፈጽማሉ፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት የሚከወኑበት የራሳቸው ምክንያት አላቸው፡፡ እትብት ከመቆረጣቸው በፊት የሚለኩበት ምክንያት እናቷ ወይም ህጻኑ እንዳይጎዳ እኩል እንዲሆን ሲባል ነው፡፡ እኩል ካልሆን ብዙ ደም እንዲፈሳት ያደርጋል፡፡ የሚቋጠርበት ምክንያት ወላዷ ብዙ ደም እንዳይፈሳት ከማድረጉም ባሻገር የእንግዴ ልጅ እንዲወርድም ያግዛል፡፡ የእንግዴ ልጁ የሚቀበርበት ምክንያት የሰውነት ቁራጭ ነውና የትም አይጣልም፤ "በሰማይ ቤት ያስጠይቃል" የሚል እምነት ስላላቸው ነው፡፡

ወላዷ ትቤ የምትቀባበት ምክንያት በእርግዝና እና በምጥ ጊዜ ብዙ ሃይል ስላወጣች ጭንቅላቷ ክፍት ነው ተብሎ ስለሚታመንና የሻከረ ሰውነቷን ለማለስለስ ዓይነተኛ መድሃኒት ነው፡፡ ወደ ቀድሞ ጥናካሬዋ ትመለስ ዘንድ በተደጋጋሚ መቀባት አለባት፡፡ የተመረጡ ምግቦችንም እንደ ገንፎ፣ አጥሚት እና የመሳሰሉትን መመገብ አለባት፡፡ "እራስ የእጇን ትልስ" እንደሚባለው ሲወልዱ የጠየቀቻቸው ሰዎች ሁሉ ወተቱን፣ ቅቤውን፣ አጥሚቱን፣ ገንፎውን፣ ጭብጦውን እየያዙ ይጠይቋታል፡፡

---

[25]አንቃር፡- ህጻኑ ከእናቱ ማህጸን እንደወጣ ከታጠበ በኋላ ጡት ከመጥባቱ በፊት ቅመም ያልገባው ንጹህ ቅቤ እንዲውጥ ይደረጋል፡፡ ይህም ህጻኑ ጡት እንዲጠባ የሚያዘጋጅ ባህላዊ ክዋኔ ነው፡፡

[26]ስራቂ፡- አንዳንድ እናቶች ከወለዱ በኋላ ራሳቸውን ይስታሉ፡፡ ህይወትን እስከማጣት ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ መንስኤውም ብዙ ስላማጡ የሚከሰት ድካም ይመስለኛል፡፡ ስራቂ የተባለበት ምክንያት ወላዷ በሰላም በመገላገሏ ደስታ በሆነበት ጊዜ ህይወትን ሊያሳጣ የሚችል ክስተት በመሆኑ ነው፡፡

አራሷ ከወለደች ቀን ጀምሮ በተከታታይ ለአስር ቀናት በሌላ አካል ትጠበቃለች፡፡ ምክንያቱም በአራስነት ጊዜያቸው ክፉ መንፈስ እንዳይተናኮላቸው ሲባል ነው፡፡ ሰው ከሌለ ድርሳነ ሩፋኤል፣ መልክ ሩፋኤል፣ ጸበል፣ መስቀል፣ ድፍን ቅል እና ጠመንጃ ከነዚህ ሁሉ የተገኘው አንዱ ወይም ሁለቱ በአጠገቧ ይደረግላታል፡፡ አራስ ሴት ሙሽራ ማለት ናት በመሆኑም ጠገራ፣ ድሪ ጠልሰምና ሌሎች ጌጦቿን ታደርጋለች፣ አዳዲስ ልብስም ትለብሳለች፡፡ ድፍን ቅል የተመረጠበት ምክንያት መራራና ድፍን በመሆኑ ምክንያት ምንም ዓይነት ክፉ መንፈስ አያርፍበትም ብለው ማመናቸው ነው፡፡ ከብረት የተሰሩ መሳሪያዎች የተመረጡበት ምክንያት ደግሞ ርኩስ መንፈስ ብረት ባለበት አካባቢ አይጠጋም የሚል እምነት እንዳላቸው በቡድን ውይይቱ[27] ጊዜ ተረድቻለሁ፡፡

ወላዷ በተገላገለች በአስረኛው ቀን በካህን ትጠመቃለች፡፡ እስከዚህ ቀን ድረስ የሚጠበቁበት ምክንያት ድካም እንዳይሰማቸው፣ ረኩስ መንፈስ እንዳይጠጋቸው እና ክብር ለመስጠት ሲባል ነው፡፡ በማህበረሰቡ ባህል እና እምነት መሰረት የወለዱ እናቶች ካልተጠመቁና ልጃቸውን ክርስትና ካላስነሱ ወደ ቅዱስ ቦታ መግባት አይፈቀድላቸውም፡፡ ወላዷ ወደ ቤተክርስቲያን ካለመሄድም በተጨማሪ ጾም አትጾምም፡፡ በዚህ ጊዜ አህዛብ ናቸው፣ ከሃይማኖት ውጭ ይሆናሉ፣ ቢጾሙ እንኳን አይቆጠርላቸውም፣ ተብሎ ስለሚታሰብ ክርስቲያንነታቸውን ትተው ይቆያሉ፡፡ በመሆኑም በጾም እንዳይበሉ የተከለከሉ ምግቦችን እንደ ወተት፣ ስጋ፣ እንቁላል እየበሉ ይቆያሉ፡፡

ወላዷ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን የምትሄደው ልጇን ክርስትና ለማስነሳት ነው፡፡ በክርስትናው ቀን አዷና ያዋለዷት ሰዎች ሁሉ ጸበል ይረጫሉ፡፡ ወደ መቅደሱም መግባት ይችላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እስከ አስር ተከታታይ ቀናት የተለያዩ ክዋኔዎች እየተካሄዱ ይቀጥላሉ፡፡ ህጻኑ ወንድ ከሆነ በስምንተኛው ቀን የሚፈጸመውን ስርዓት ግርዘት ጨምሮ በአስረኛው ቀን የሚፈጸመው ጥምቀት ህጻኑን እና እናቱን ወደ ቅዱስነት ደረጃ የሚያሸጋግሩ ናቸው፡፡

[27]የቡድን ውይይቱ የተካሄደው እለተ እርብ ግንቦት 03/2005 ዓ.ም ከጥዋቱ 2፡30- 4፡03 ድረስ ፍኖተ ሰላም በሚገኘው ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ነው፡፡የቡድኑ ተሳታፊዎች ቄስ ሚናስ ሀሩይ፣ አቶ በቀለ ቸሩ፣ መሪጌታ ስማኔ ገብረ እየሱስ፣ እማሆይ እጅግምታ ሀይሉ እና አቶ ለገሰ እምሩ ይባላሉ፡፡ እድሜአቸው 82፣ 86፣ 49፣ 69፣ 72 (እንደስማቸው ቅደም ተከተል) ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ባደረጉት የቡድን ውይይት የተገኘ መረጃ ነው፡፡

መልካ ተበብ መሪጌታ ስሜነህ አበበ እንደነገሩኝ እነዚህ ቀኖች የተመረጡበት ምክንያት ቀዳማዊ ምኒልክ ከእስራኤል ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ አብረዋቸው የገቡ 318 ሊቃውንቶች ህገ ኦሪትን፣ ከሄኖክ እስከ ሰሎሞን የተጻፉ መጽሐፍተ ብሉያትን ይዘዋቸው በመምጣታቸው ምክንያት የኦሪታውያንን ባህል እንዳለ ወደ ኢትዮጵያ ብሎም ወደ ክርስትና ሃይማኖት ገብተው እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡

ቤተሰቦቿ በቅርብ ከሌሉ በሰላም መገላገሏን እንደሰሙ እናት፣ አባት፣ እህት፣ ወንድም፣ አጎት፣ አክስት ባጠቃላይ የቅርብ ዘመዶቿ ጠላ፣ ወተት፣ ቅቤ፣ እርጎ፣ ጭብጦ[28] እና የገንፎ እህል እየያዙ ለረጅም ጊዜ ይጠይቋታል፡፡ ሊጠይቋት የሚመጡ ሰዎች ሁሉ "እንኳን ማሪያም ማረችሽ" እያሉ እንደሚገቡ ሁሉ ሲወጡ ወይም ሲሰናበቱ ደግሞ "ማሪያም በሽልም ታውጣሽ"፣ "ለመቀነትሽ ታብቃሽ"፣ "ልጅሽን ታሳድግልሽ"፣ "ጭንሽን ታሙቅልሽ" እያሉ ይሄዳሉ፡፡ እነዚህ አባባሎች እንደ ሙሽራ ይመርቡሽ፣ ጠንክሪ፣ ዘጠኝ ወር በማህጸንሽ አርግዘሽ አምጠሽ የወለድሽውን የእብራክሽን ክፋይ ታሳድግልሽ የሚሉ አገላለጾች ለማሪያም የተሰጡ ሀላፊነቶች ናቸው፡፡ "ጭንሽን ታሙቅልሽ" የሚለው አገላለጽ አንድም ልጅ በማቀፍ የሚገኝ ሙቀት ነው፤ ሌላም በእርግዝና እና በአራስነት ምክንያት ከባሏ ተለይታ ስለቆየች ከባሏ ጋር በመተኛት የሚገኝ ሙቀት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለእመቤታችን የቃል ኪዳን አገሯ ስለሆነች፣ በስደቷ ጊዜም በጣና ሀይቅ አካባቢ ሶስት ወር ከአስር ቀን ቆይታለች ተብሎ ስለሚታመን ህዝቡ በተለይ ሴቶች ይወዷታል፤ በማለት የነገሩኝ መሪጌታ ስሜነህ አበበ ናቸው፡፡ ከመውደዳቸው የተነሳ በችግራቸው ሁሉ እሙቤቴ አማልጅኝ እያሉ ይለምናሉ፡፡ ከዚህ የተለየ ሴቶችን እንድታዋልድ የተሰጣት ቃልኪዳን የለም፣ በማለት የነገሩኝ መሪጌታ ስሜነህ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን የተሰጣት ቃልኪዳን ባይኖርም ማህበረሰቡ ከእርግዝና እስከ ልደት ያለውን ህይወቱን የምትጠብቅለት ማርያም ናት፡፡ አንዲት እናት በእርግዝና ጊዜዋ ከፉ ነገር ከፈጸመች "በማርያም እጅ ተይዛ ይሆን ታድርግ" ተብላ ትገሰጻለች፡፡ የልደትን ጉዳይ ለማርያም የሚሰጡበት ምክንያት እየሱስ ክርስቶስን በወለደች ጊዜ እርግዝናን እርግዛ፣ የምጡን ስሜት የምታውቅ ያየች እሷ በመሆኗ ለወሊድ ቅርበት ያላት እሷ ናት በማለት ነው፡፡ በመሆኑም በወሊድ ጊዜ የምትረዳቸው፣ የምታድናቸው፣ የምታግዛቸው፣ እመቤታችን ናት ብለው ያምናሉ፡፡

[28] ጭብጦ፡፡ ከጤፍ ዱቄት የሚዘጋጅ ቂጣ በቅቤ ተፈርፍሮ እየተጨበጠ የሚበላ ምግብ ሲሆን በአካባቢው በወቅት አራስ እናቶችን ለመጠየቅ ይዘጋጃል፡፡

ልደትን በተመለከተ የሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባራት ሁሉ እንድትለመናቸውና ምህረት እንድልክላቸው በማሰብ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ ህጻኑ ወንድ ከሆነ በአርባ፣ ሴት ከሆነች ደግሞ በሰማኒያ ቀናቸው ክርስትና ይነሳሉ፡፡ እነዚህ የተለያዩ ቀኖች ለምን እንደተመረጡ የሀይማኖት አባቶች መልስ አላቸው፡፡

> ክርስትና ማለት 'ክረስተና' ከሚል ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም ቀጠረ ማለት ነው፡፡ መነሻው ወደ አዳምና ሄዋን ታሪክ ይወስዳል፡፡ ማለትም አዳም ተፈጥሮ በቀራኒዮ ለአርባ ቀናት ከቆየ በኋላ በመላእክት ታጅቦ ወደ ገነት መግባቱን ምሳሌ በማድረግ ነው፡፡ የሴቶችንም ስንመለከት ሄዋን ተፈጥራ እስከ ሰማኒያ ቀን ድረስ በቀራኒዮ ከቆየች በኋላ ነው ወደ ገነት የገባችው፡፡ ከዚህ በመነሳት ወንዶች በተወለዱ በአርባ ቀን ሴቶች ደግሞ በሰማኒያ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ሀብተ ወልድ፣ ስመ ክርስትና፣ እሴተ ልቦና ያገኛሉ፣ በማየ ገቦ ይጠመቃሉ፣ ሲጋና ደሙንም ይቀበላሉ፣ በመዝገበ ጥምቀት፣ በመዝገበ ክርስትና፣ በመዝገበ ህያዋን ተመዝግበው ቁጥራቸው ከክርስቲያን ይሆናል፡፡[29]

ከዚህም በተጨማሪ ከክርስትና ጋር ተያይዞ ለህጻኑ ማተብ ይታሰርለታል፡፡ ምሳሌነቱም ያዕቆብ ዛልወረዳይ (ዘኢልወረዳኢ) የተባለ ሰው በአረማውያን መንደር ገብቶ ሲያስተምር አሳምኖ፣ አጥምቆ፣ አቁርቦ ወደሌላ አካባቢ ሲሄድ የተጠመቁት፣ ያመኑት፣ ስጋና ደሙን የተቀበሉት ከሌሎች የእግዚአብሄር ቤተሰቦች ካልሆኑት ጋር ያገኛቸዋል፡፡ ይህንን ለመለየት ሲል ነጭ፣ ቀይና ጥቁር ክር አንድ ላይ አድርጎ አሰረላቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የአካባቢው ሊቃውንት ለአዲስ አማንያን (ክርስትና ለሚነሱ ህጻናት) ያንን አይነት ማተብ ያደርጉላቸዋል፡፡ ማተብ ሃይማኖታዊ ማንነትን ከማመልከት ባሻገር በርካታ ባህላዊ ትእምርቶችን የያዘ ነው፡፡ ቃል አክባሪነትን፣ ሀቀኝነትን፣ ታማኝነት፣ አደራ ተቀባይነት የተሰኙ መልካም እሴቶች መገለጫ ነው፡፡

በብዙ ባህሎች ለልጆች ስም የሚወጣላቸው ራሱን የቻለ የስም አወጣጥ ስርዓት ተካሂዶ ነው፡፡ ስም ህጻኑ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖረው ማንነት የሚጀምርበት ደረጃ ነው፡፡ ህጻኑም ከሌላው የሚለየው ስም ሲወጣለትና በስሙ መጠራት ሲጀምር ነው፡፡ ልደትና ስም የሰዎች ግላዊና ማህበራዊ ማንነት የሚጀምርበት በመሆኑ የተለያዩ ስርዓተ ክዋኔዎች ይፈጸማሉ፡፡ ብዙ ስሞች በትርጉም የተሞሉ እንዲሁም መንፈሳዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን የመግለጽ ፋይዳ አላቸው፣ እንደ ቅዱስም ተደርገው ይወሰዳሉ (ግሪም፣ 1943፡16)፡፡

---

[29] ከመልጌከ ዋበብ መሪጌታ ስሜነህ ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ነው፡፡

ክርስትና ህጻናትን ክርስቲያን ከማድረግም ባሻገር በእለቱ የሚወጣላቸው ስም ጾታቸውን፣ ሃይማኖታቸውን ይገልጻል፡፡ ሴትና ወንድ በአንድ ቀን ክርስትና ቢነሱ እንኳን የሚወጣላቸው ስም የተለያየ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በእለተ ማርያም ክርስትና የተነሱ ወንድ እና ሴት ህጻናት ወንዱ ወልደ ማርያም ሲባል ሴቷ ወለተ ማርያም የሚል ስም ይወጣላቸዋል፡፡ ግተብ ማስሬቸው፣ መጠመቃቸው እና ስጋውንና ደሙን መውሰዳቸው ክርስቲያን መሆናቸውን የሚያመለክት ሲሆን በሚወጣላቸው ስም ደግሞ ጾታቸውን ይገልጻል፡፡ ወላጁ ክርስቲያንነቷ የሚታደስበት ህጻኑ ደግሞ ክርስቲያን የሚሆንበት እለት ስለሆነ ትልቅ ዋጋ ይሰጠዋል፡፡ እንደየቤቱ አቅም ድግስ ተደግሶ ወዳጅ ዘመድ ይጠራል፡፡

## በልደትና ክርስትና ስነ-ስርዓት ማሳረጊያ የሚቀርቡ ምርቃቶች

ምርቃት አንድ ክብረ በዓል ተከብሮ ሲጠናቀቅ በእድሜ ጠገብ ሰዎች የሚቀርብ የስነ-ቃል ዓይነት ነው፡፡ እንዲሁም በአብዛኛው የህብረተሰብ የእለት ከእለት ህይወት ውስጥ ማእከላዊ ቦታ ያለው ከእምነት ጋር የተሳሰረ ቅርጽ ነው፡፡ በቅርጹ ዝርው በመሆኑ አቀራረቡም በንግግር መልክ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መራቂዎች የሚመርቁበት ቅደምተከተል አለው፡፡ በመጀመሪያ መነኩሴዎች፣ ከዚያ ሽማግሌዎች ከመረቁ በኋላ ቄስ በጸሎት ያጠቃልላል፡፡ ምርቃት ሰዎች አምላካቸውን የሚያመሰግኑበት፣ የሚፈልጉትን የሚጠይቁበት፣ ማንነታቸውን የሚገልጹበት፣ የሚመሩበትን ርዕዮተ አለም የሚያስተላልፉበት፣ ለማህበረሰቡ ብሎም ለሀገራቸው ያላቸውን መልካም ምኞት የሚገልጹበት ቅርጽ ሲሆን እንደየአጋጣሚው መለያየት የተለያየ ይዘት ያላቸው ምርቃቶች ያቀርባሉ፡፡ ምርቃቶች በብዛት በምሳሌያዊ ንግግሮች፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚተኮራባቸው ጽንሰ ሀሳቦችን በያዙ ቃላት፣ በተረት የተዋቀሩ ናቸው፡፡ የልደትና ክርስትና ከበራ መጠናቀቂያ ላይ ከሚቀርቡ ምርቃቶች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

### ምርቃት 1. ለአቅመ አዳም (ለአቅመ ሄዋን) ያድርሰው (ያድርሳት)፣

ማህበረሰቡ ልጁን ክርስትና ሲያስነሳ ከሚባሉ ምርቃቶች መካከል የመጀመሪያው ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን መድረስ ልጆችን ወደ ሌላ ደረጃ የሚያሸጋግር የእድሜ ደረጃ ነው፡፡ ልጆች እዚህ ደረጃ ላይ ካልደረሱ ወደሚቀጥለው ደረጃ መሸጋገር አይችሉም፡፡ በመሆኑም በምርቃታቸው ውስጥ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ይገኛል፡፡

ምርቃት 2. በሰርጉ (በሰርጓ) እንብላ፣

ሰርግ የልጆችን ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን መድረስ ተከትሎ የሚመጣ የህይወት ሽግግር ነው፡፡ ሰርግ የማህበረሰቡ የመጨረሻ የደስታ መግለጫ ስነ-ስርዓት ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ተደሰትሁ ብሎ የሚያስበውም ልጁን ደግሶ ወዳጅ ዘመድ ጠርቶ ያበላ ቀን ነው፡፡ ልጁ አድጎ ቤተሰቦቹ እሱን በመዳር በህይወታቸው የመጨረሻውን ደስታ እንዲያዩ ያላቸውን መልካም ምኞት በምርቃታቸው አማካኝነት ይገልጻሉ፡፡

ምርቃት 3. ሃይማኖቱ የጸና ምግባሩ የቀና ይሁን፣

ይህ ምርቃት ምንም እንኳን በተባእት ጾታ ስለቀረበ ለወንድ ብቻ ነው ማለት አይደለም፡፡ ሴቷም በሃይማኖቷ የጸናች ምግባሯ የቀና እንድትሆን ይፈለጋል፡፡ በመሆኑም ትንታኔው ሁለቱንም ጾታዎች መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ሃይማኖትና ምግባር ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው መልካም እሴቶች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ሰው በሃይማኖቱ ጠንካራ፣ በምግባሩ ትጉ ሊሆን ይገባል፡፡ ሃይማኖትና ምግባር ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት፣ እንዲሁም ከማህበረሰቡ ጋር ተስማምቶ ለመኖር መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም ህጻኑ አድጎ፣ በሃይማኖቱ ትእዛዝ የሚኖር፣ ስለሃይማኖቱ እስከ ሞት የሚታገል፣ ሃይማኖቱን የሚሰብክ እንዲሁም በመልካም ስነ-ምግባር የታነጸ እንዲሆን ከመፈለጋቸው የተነሳ የሚመርቁት ነው፡፡

ምርቃት 4. ወንዝ እሚያሳፍር አገር እሚያስከብር ይሁን፣

ምርቃቱ በተረበበት አውድ አገር ማለት አንድም መኖሪያ ቀበሌንና ወረዳን ወይም ኢትዮጵያን እንደማለት ነው፡፡ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ብዙ ቀበሌዎች የተከፋፈሉት በወንዞች አማካኝነት ነው፡፡ ብዙ ቀበሌዎችም የየራሳቸው ወንዝ አላቸው፡፡ ማህበረሰቡም ወደና ፈትዶ ካልሰጠ በስተቀር ወንዙን አያስደፍርም፡፡ የኛ ነው ብለው የሚያስቡት ወንዝ በሌላ ቀበሌ ከተጠለፈ እስከ ነፍስ ማጥፋት የሚደርስ ጸብ ይፈጠራል፡፡ ምክንያቱም ወንዝ ማለት አገር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ልጁ ጀግና መሆን እንዳለበት፣ አገርን የሚያስከብር፣ የማያስደፍር እንዲሆን ያላቸውን ፍላጎት የሚገልጹበት ነው፡፡ በዚህም አገር መደፈር እንደሌለባትና ማህበረሰቡ ጀግና መሆን እንዳለበት ለማመልከት የሚጠቀሙበት ምርቃት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ጀግና የተወደደ፣ የተከበረ፣ የተፈራ ነው፡፡ በመሆኑም ጀግንነትን በምርቃታቸው ብቻ ሳይሆን በሌሎች የስነ-ቃል ዘርፎች ይሰብካሉ፡፡

ምርቃት 5. ለጠላቱ እሚመክት ለወዳጁ እሚፈተፍት ይሁን፣

ሁሉም ሰው የተለያየ ባህሪ ስላለውና በግል መኖር ከባድ ስለሆነ ኑሮውን በጋራ በሚመራበት ጊዜ አንዳንድ አለመግባባቶች ወይም መግባባቶች ይፈጠራሉ፡፡ አለመግባባቶች ወደ ጠላትነት የሚያመሩ ሲሆን መግባባቶች ደግሞ ወዳጅነትን ያመጣሉ፡፡ ማህበረሰቡ እያንዳንዱ ሰው የእነዚህ ሁለት ተቃራኒ ባህርያት ባለቤት ሊሆን ይገባል ብሎ ያምናል፡፡ እነዚህ ባህሪያት በሁለት ተቃራኒ አጋጣሚዎች የሚገለጹ ናቸው፡፡ አንድ ሰው ሁልጊዜ የዋህ ወይም ሁልጊዜ ክፉ መሆን የለበትም፡፡ ይልቁንም ለጠላቱ ሁልጊዜም የማይደፈር፣ የማይሸነፍ፣ የማይንበረከክ መሆን ሲገባው በአንጻሩ ለወዳጁ ደግሞ ደግ፣ የሚያበላ፣ የሚያጠጣ፣ መሆን እንደሚገባው ለማመልከት የተጠቀሙበት ምርቃት ነው፡፡

ጠላትነት ከግለሰቦች አልፎ በቡድኖች ወይም በሀገር መካከል ሊከሰት ይችላል፡፡ ከሌሎች በወትቱ ትኩረት ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች ማለትም እንደ ትምህርት፣ ንግድና ሌሎች የስራ ፈጠራ ክሂሎች ይልቅ ጀግንነትና ደግነት በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህ በምሳሌነት የቀረቡት ምርቃቶች በሚመረቁበት ጊዜ ከደካሞችና ከሀሙምተኞች በስተቀር ሁሉም ታዳሚ ቆሞ "አሜን!" በማለት የይሁንልን ይደረግልን ተማጽኖ እጃቸውን በመዘርጋትና ከንፈራቸውን በመምጠጥ ተማጽኖ ያደርጋሉ፡፡

## 4.2 የሰርግ ስርዓት ክዋኔ

የሰርግ ስነ-ስርዓት ከሰው ልጅ የህይወት ዘመን ዑደቶች መካከል ከልደት ቀጥሎ የሚመጣ ሲሆን ወንዶች ለአቅመ አዳም ሴቶች ደግሞ ለአቅመ ሄዋን መድረሳቸውን ተከትሎ የሚፈጸም ነው፡፡

ከሰው ልጅ የህይወት ዘመን ዑደቶች መካከል በብዙ ማህበረሰቦች በስፋት የሚከናወን እንዲሁም ሰዎች ከነበሩበት ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚሸጋገሩት በሰርግ አማካኝነት ነው፡፡ ሰርግ የተጋቢዎቹ ጋብቻ የሚታወቅበትና የሚረጋገጥበት ስነ-ስርዓት ሲሆን ክዋኔውም ህዝባዊ ወይም ሃይማኖታዊ ሊሆን ይችላል፡፡

የሰርግ ስነ-ስርዓት ሙሽሮቹ ለትዳር ከተመራረጡበት ወይም ከተፋቀሩበት ጊዜ ጀምሮ ልጅ እስከሚወልዱ ድረስ የሚፈጸመውን ክዋኔ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ የሁለቱ የተጋባቦት ሁኔታ፣ አለባበስ፣ ጌጣጌጥ፣ የጸጉር አሰራር እና ሌሎች ሰብዕናቸውን የሚገልጹ ነገሮች ሁሉ

ባልና ሚስቱን ወደ አንድ ለማምጣት የሚደረጉ ስርዓተ ክዋኔዎች ናቸው፡፡ በብዙ ባህሎች የሰርግ ክዋኔ የሚፈጸመው በዘፈን፣ በዳንስ፣ በጸሎት፣ በምርቃን፣ በእልልታ አማካኝነት ነው (ሂል እና ዳኔልስ፣ 2008፣ 279)፡፡

መሪጌታ ስሜነህ አበበ እንደነገሩኝ ሰዎች በአለም ላይ ሲኖሩ ጋብቻ ዘርን ተክቶ ለማለፍ፣ ከዘሙት ለመራቅና ለመረዳዳት ሲባል ይፈጽማሉ፡፡ ሰርግ የራሱ የሆኑ ሂደቶች ያሉት ረጅም ጊዜ የሚወስድ ስነ-ስርዓት ነው፡፡ የሰርግ ክዋኔ ሶስት ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ ይፈጸማል፡፡ የመጀመሪያው የተጋቢ ቤተሰቦች የውል ስምምነት የሚይዙበትን ቀን ምክንያት በማድረግ፣ ሁለተኛው የሰርጉ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው ቀናት እና የመጨረሻው ከሰርጉ በኋላ የሚፈጸመው የመልስ ስነ-ስርዓት ነው፡፡

ከሰርጉ ቀን በፊት የወንድ ቤተሰቦች በማህበራዊ ደረጃ፣ በሃይማኖት፣ በመደብ ይመጥነኛል ብለው ያሰቡትን ቤተሰብ ልጅህን ለልጄ በማለት ሽማግሌ ይልካሉ፡፡ ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ቢጋቡ ለመዛመድ ሲፈልጉ ብዙ ነገሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባሉ፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ባህል መሰረት ለዘር፣ ለሃይማኖት፣ ለመደብ ትልቅ ቦታ ይሰጣል፡፡ ጨዋ፣ ቡዳ (ሸማኔ፣ ፋቂ፣ ቀጥቃጭ) የሚሰኙ የማህበራዊ ደረጃ መገለጫዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ከመስማማታቸው በፊት መደቡ የነማን እንደሆነ ይጠየቃል፤ ይጣራል፡፡ ጨዋ የጨዋን ልጅ እንጅ ከሌላ የማህበረሰብ መደብ አይጋባም፡፡ ባለማወቅ እንኳን ቢፈጸም ትዳሩ እንዲፈርስ ይደረጋል፡፡ ካልፈረሰ ከቤተሰብ፣ ከወዳጅ ዘመድ ብሎም ከማህበረሰቡ ይገለላሉ፡፡ ሰው ያለደረጃው እንዳይጋባ ከሚያነሷቸው ምክንያቶች መካከል ዋናው ቀድመው ያረቁ ቤተሰቦቻችን አጥንት ይሙሀል፤ ከፈጣሪም ያጣላል፡፡ የሚል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጋብቻ በሀብት ተመጣጣኝ በሆኑ ሰዎች መካከል ይፈጸማል፡፡ ማለትም በሃብታምና ድሃ፣ በሹማምንት ዘሮችና ተራ በሆነው ማህበረሰብ መካከል ፈጽሞ እንኳን ባይሆን በብዛት አይፈጸምም፡፡

ማህበረሰቡ ጋብቻን እንደ አንድ ዝምድና መፍጠሪያ ዘዴ አድርጎ ይጠቀምበታል፡፡ ማለትም ሰዎች ይጠቅመኛል ወይም ለክፉ ቀን ይሆነኛል ብለው ከሚያስቡት ሰው ጋር ዝምድና ለመፍጠር የሚጠቀሙበት አጋጣሚ ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች ከግምት ውስጥ አስገብተው ከተጨራረሱ በኋላ በተመጣጣኝ ድግስ በፊርማ የተደገፈ ትምምን ያካሂዳሉ፣ ውልም ይይዛሉ፡፡

በሰርግ ስነ-ስርዓት በዋናነት ከሚከወኑ ስርዓቶች ዋናው ሰርጉ የሚፈጸምባቸው ቀኖች ናቸው፡፡ በአካባቢው ባህላዊ ሰርግ የሚከወነው በብዛት በሁለት ተከታታይ ቀናት ነው፡፡ የመጀመሪያው ወንዱ ሙሽራ ወደ ሴቷ ቤት ሄዶ የሚያድርበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሙሽራዋን ይዞ የሚመለስበት ቀን ነው፡፡ ሙሽራው ከቤቱ ከመውጣቱ በፊት፣ ከሙሽሪት ቤት ሲገባ፣ ሙሽሪትን ይዞ ሲወጣ፣ ተመልሶ ሲገባ፣ እንደኛውን ወደ ቤቱ ይዟት ሲሄድ የሚፈጸሙ በርካታ ባህላዊ ክዋኔዎችና አገላለጾች አሉ፡፡ ሁኔታውን በቅደም ተከተል መመልከት ተገቢ ነው፡፡

በምርጫ ጊዮርጊስ ቀበሌ በተካሄደ ሰርግ ላይ ተገኝቼ ባደረግሁት ምልከታ ሙሽራው ከመውጣቱ በፊት የተዘጋጀለትን የተለየ ምግብና መጠጥ ከሚዜዎቹ ጋር አብረው በሉ፤ የተዘጋጀላቸውንም ጠላ ጠጡ፡፡ ከዚያም "በቸር ተመለሱ፣ ይቅናችሁ፣ መልካም ነገር ይጠብቃችሁ" ተብለው ተመርቀው፤ ዘፍነው ወጡ፡፡ የሙሽራው ስር (ዋና) ሚዜ ሙሽራውን በትክሻው ያዘውና፣ ሙሽራው ጽዋ ሙሉ ድፍድፍ ተሰጥቶት ያዘና ሌሎች አጃቢዎች ሆ እያሉ የቆመ ሙቀጫ ከዞረ በኋላ አነጣጥሮ የቆመው ሙቀጫ ውስጥ ጨመረው፡፡ ይህም ወደ ሙሽሪት ቤት ለመሄድ የመጨረሻው ድርጊት ነው፡፡[30]

አንድ ስርዓተ ክዋኔ በሚፈጸምበት ባህላዊ አውድ የጉዳዩ ተግባርና ተምሳሌት የሚገለጽበት ስለሆነ የገለሰቡን፣ የቤተሰቡን ብሎም የማህበረሰቡን ማንነትና ርዕዮተ አለም የማስተዋወቅ ፋይዳ አለው፡፡ በመሆኑም የሙቀጫው፣ የጽዋውና የድፍድፉ እንዲሁም ሙሽራው የሚያከናውንበት ምክንያት መመርመርና መተርጎም ያስፈልጋል፡፡

ሙሽራው በሰርጉ ቀንም የማያውቀውን አዲስ ነገር ለማወቅ ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ሙሽሮች ብቻ በሚስጥር የሚፈጽሙትን ነገር በተለያዩ ወካይ ቁሳቁሶችን ትእምርታዊ በማድረግ በማህበረሰቡ መሃል ያደርጉታል፡፡ ሰርጉን ተከትሎ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚፈጽመውን የግብረ ስጋ ግንኙነት ለማመልከት ሙቀጫ፣ ጽዋ እና ድፍድፍ በመጠቀም ድርጊቱን በትእምርት ያቀርቡታል፡፡ ማህበረሰቡ በግልጽ የማያደርገውን የነገረ ወሲብ ጉዳይ በሁሉም ሰው እንገዳ ባልሆኑ ትእምርታዊ ቁሳቁሶች አማካኝነት ይከውኑዋል፡፡ እያንዳንዳቸው ትእምርቶች ወካይና የሴትና የወንድ የወሲብ አካል ክፍሎች ናቸው፡፡ ሙቀጫው የሴትን

[30] በምርጫ ዮራወር ቀበሌ የሚኖሩ አቶ ቻሌ ማሞ የተባሉ አባወራ ወንድ ልጃቸውን ለመዳር ባዘጋጁት የሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ በመገኘት የተደረገ ምልከታ ነው፡፡ ምልከታው የተካሄደው ማክሰኞ ሚያዝያ 27/2005 ዓ.ም ከቀኑ 7፡30 እስከ 8፡20 ሙሽራው ሲወጣ የተደረገ የመሸኛ ፕሮግራም ላይ ነው፡፡

ብልት የሚወክል ሲሆን ጽዋው ደግሞ የወንድን ብልት እንዲሁም ድፍድፉ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወቅት ከወንድ ብልት የሚወጣውን አባለዘር ወክሎ የቀረበ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ትእምርታዊ ክንውን ሙሽሮች የሚፈጽሙትን ወሲብ ያመላክታል፡፡

ነገረ ወሲብ ትውልድ ወይም ዘር እንዲቀጥል የግድ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ትልቁ አጋጣሚ ሰርግ ነው፡፡ ወሲብን ሁሉም እንስሳት እንዲሁም ህይወት ያላቸው ፍጥረታት ሁሉ ይፈጽሙታል፡፡ የሰው ልጅ ግን እንደየባህሉና እንደየአጋጣሚው ጉዳዩን ትእምርታዊ በማድረግ ይገልጸዋል፡፡ የሰርግ ስነ-ስርዓት ወሲብ የሚጀመርበት ከመሆኑም ባሻገር ከሰርጉ በኋላም እየተተገበረ የሚዘልቅበት አለም እንደሆነ ለማስተዋወቅ ተምሳሌታዊ አድርገው ይገልጹታል፡፡ በትእምርት የቀረበው ነገረ ወሲብ የሚገልጸው ሁነቡን ብቻ ሳይሆን ሂደቱን ጭምር ነው፡፡ ማለትም ድፍድፉ የወንዱን አባለዘር እንደሚያመለክት ከላይ ተገልጿል፡፡ ይህም በትክክል ወደ ሴቷ ብልት መግባት እንዳለበት ሁሉ ሙሽራውም ጽዋውን በጥንቃቄ ሙቀጫው ውስጥ መጨመር አለበት፡፡ ምናልባት ካልጨመረው ወይም ከነተው በማህበረሰቡ ዘንድ ይናቃል፡፡ ይህ አጋጣሚ በሁለት መንገድ ያስተቻል፡፡ አንድም ሙሽራው ክብረ ንጽህና የመውሰድ አቅም የለውም ተብሎ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታሰባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሚስቱ ክብረ ንጽህና የላትም የሚል ጥርጣሬ በሙሽራው፣ በቤተሰቦቹ እንዲሁም በጓደኞቹ ላይ ያድርባቸዋል፡፡



ፎቶ ገራፍ 1 ሙሽራው ከቆናው ሚዜ ትከሻ ላይ ሆኖ ድፍድፍ የተሞላ ጽዋ ሙቀጫ

ውስጥ ሲጨምር የሚያሳይ ምስል

ጥያቄ፡- በልጅነት ሽበት፣ በጉብዝና ጥቁረት፣ በእርጅና ቅላት ምንድን ነው?

መልስ፡- በርበሬ

ጥያቄ፡- የበሬ ዕቃ ስንት ነው? ስማቸውንም ንገሩን?

መልስ፡- ሶስት ናቸው እነሱም ከብረት፣ ከእንጨትና ከቆዳ የሚሰሩ ናቸው፡፡

ጥያቄ፡- ልጃችንን ስንሰጣችሁ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳይደርስባት በካህን እና በምትወዷት እህታችሁ ተገዙ?

መልስ፡- በመካከላቸው ጠብ ቢፈጠር ቢቻል አስታርቃለሁ ባይቻል መጥቼ እናገራለሁ፡፡ በባሏ በደል እንዳይደርስባት አደርጋለሁ፡፡ ይህን ባላደርግ ነፍሴ ትውረድ በቁስ አላፀ፣ እሁቴን ትርንጉን ይሁንብኝ በማለት በንስሃ አባታቸው ተገዙ፡፡ ከዚህ በኋላ ሙሽራዋን አሳዳሪው አስረከባቸው፡፡[34]



ፎቶግራፍ 2 የወንድ ሙሽራ ሚዜዎች ሽማግሌ ፊት ቀርበው ሲጠየቁ የሚያሳይ ምስል

የጥያቄ እና መልስ ሂደት ትክክለኛ መልስ ካልመለሱ ተራ በተራ ሶስቱም ሚዜዎች ይጠየቃሉ፡፡ ጥያቄዎችን በመመለሳቸው በሽማግሌ ዘንድ ታማኝነት ይኖራቸዋል፡፡ ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ የቀለዱ፣ የዋሹ እንደሆነ ሙሽራዋን እስከ መከልከል ሊደርሱ ያችላሉ፡፡ ይህም ለሙሽራዋ ቤተሰብ ምን ትሆን ይሆን እያሉ ከማሰብ በመጠኑም ቢሆን ያርቁሏ፡፡ ምናልባት ሴቷ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ከሆነች አቅሟ እከሚፈቅድ አስገድዶ እንዳይደፍራት ገደድ ይይዛሉ፡፡ ይህም ለሴቷ ጨንነት ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ምክንያቱም

[34] ከሀርር ኪዳነምህረት ከአቶ አማኑ ቤት በተካሄደ ሰርግ ላይ ባደረግሁት ምልከታ የተገኘ መረጃ

የሙሽራው ስር ሚዜ እና ሁለተኛ ሚዜ የገቡት ቃል እና ግይድ ስላለ ተገዳ እንዳትደፈር፣ በደል እንዳይደርስባት የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት፡፡

ከዚህ በኋላ አሳዳሪው ለሙሽራዋ የሚያስፈልጋትን አልባሳት ቆጥሮ አስረከበ፡፡ በመጨረሻም ሙሽራዋ የመጡላትን ልብሶች ለብሳ በአሳዳሪው ታዝላ ወጣች፡፡ ከተዘጋጀላት ዳውጃ ላይ ተቀምጣ ከቆየች በኋላ እንደገና ታዝላ በቅሎው ላይ ተቀመጠች፡፡ በዚህ ጊዜ ወንዶች ሃይሎጋ ሸበ! ሴቶች ደግሞ የተለያየ መልእክት ያላቸው ግጥሞችን እየደረደሩና በእንጊታቸው እየዘፈኑ ሸኟቸው፡፡



ፎቶግራፍ 3 አሳዳሪው ከሚዜዎች የተረከባቸውን አልባሳት በሽማግሌ ፊት ቆጥሮ

ሲያስረክብ የሚያሳይ ምስል

የወንድ ሙሽራ ቤተሰቦች ሲደርሱ ሞቅ ባለ ዘፈን፣ በእልልታ እና በሆታ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ተደርጎላቸው ሙሽሮች ወደተዘጋጀላቸው ጫጉላ ገቡ፡፡ ዋና ዋና ሚዜዎች የሙሽራውን እናት ጠሯቸውና የአንድ ልጇን ስም ጠርታ "ከልጄ አለያትም" በማለት ቃል እንድትገባ አደረጓት፡፡ ይህም ሙሽራዋ ቤት ውስጥ ስትኖር በደል እንዳይደርስባት ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም እናት ልጇ እንድትጎዳ ስለማትፈልግ ከልጇ

አለያትም በማለት ቃል ስለገባች እንዲያውም በእንክባካቤ ይይዟታል፡፡ ይህም ሌላው ሙሽራዋ እንዳትበደልና ባይተዋርነት እንዳይሰማት የማድረጊያ ዘዴ ነው፡፡ በአካባቢው ቃል መግባት ከሰርግ እጋጣሚ ባሻገር ለማህበረሰቡ ህልውና ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ የሙሽሪት ቤተሰቦች ለጃቸው ለማያውቋቸው ሰዎች አምነው የሚሰጡት ቃል ስለገቡ እንጅ ሌላ የሚታይም ሆነ የሚጨበጥ ማረጋገጫ የላቸውም፡፡

በሌላ በኩል ሙሽራው እና ሙሽሪት ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ከሆኑ ሙሽራው ክብረ ንጽህና እንዲወስድ በጓደኞቹ ይመከራል፡፡ ይህንንም ሚዜዎች ያስፈጽሙታል፡፡ ስር ሚዜ ሙሽሮች የሚተኙበትን ምንጣፍ አነጣጥፎ ነገሩን እንዴት ማድረግ እንዳለበት ነገሮ ይወጣል፡፡ ሁለተኛ ሚዜ ደግሞ ከአካባቢው ሳይርቅ ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራል፡፡ ውሻ ጠባቂ የሚባለው ከሩቅ ሆኖ ሌላ ሰው እንዳይረብሽ የሚጠብቅ ነው፡፡[38]

የሰርግ ስነ ስርዓት የሚጠናቀቅበት የመጨረሻው ክንውን መልስ የሚባለው ነው፡፡ መልስ ከሰርግ ቀን ጀምሮ በአምስተኛው ቀን ወይም በአስረኛው ቀን የሚከበር ሲሆን የሙሽሮች የጫጉላ ቆይታ የሚያበቃበት ቀን ነው፡፡ እስከ መልስ ቀን ድረስ ሙሽሮቹ ወደ ቤት አይገቡም፣ ፊጽሞ ብቻቸውንም አይሆኑም፤ እራስ ሴት እንደምትጠበቅ ሁሉ ሙሽሮምች እርኩስ መንፈስ እንዳይቀርባቸው ጠባቂ ሰው ያስፈልጋቸዋል፤ በሚል እምነት እንደሆነ ከቡድን ውይይቱ ተረድቻለሁ፡፡

ሙሽሮች አስር ቀን በጫጉላ ሲቆዩ ጠባቂ ሰው ያስፈልጋቸዋል፡፡ በአስረኛው ወይም በአምስተኛው ቀን እንደእዲስ ድግስ ተደግሶ ዘመድ ወዳጅ ተጠርቶ ከተበላና ከተጠጣ በኋላ ተመርቀው ወደ ማህበሩ የሚቀላቀሉበት ስነ-ስርዓት ነው፡፡ የመልስ ቀን ሙሽሮች ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ከመሄዳቸው በፊት ለብቻቸው ተመርቀው ይሸኛሉ፡፡ በዚህ እለት የሚዘፈኑ ቃል ግጥሞችና ምርቃቶች ይዘት የተለየ ነው፡፡ መላመድን፣ ለፍሬ መብቃትን፣ የማህበረሰቡን ባህል የሚጠብቁ ልጆች እንዲወልዱ ይመኙላቸዋል፡፡

---

[38]አቶ ሙሉ ደታደሰ የምርጫ ጊዮርጊስ ቀበሌ ነዋሪ ሲሆኑ ባለትዳር፣ የሁለት ልጆች አባት እና የ64 አመት እድሜ ባለፀጋ ናቸው፡፡ በወጣትነታቸው ዘመን ለብዙ ሰው ሚዜ እንደነበሩ አጫውተውኛል፡፡ በእለተ ማክሰኞ፣ ሚያዝያ 15/2005 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00-10፡23 ድረስ በመኖሪያ ቤታቸው በመገኘት በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ነው፡፡

የሰርጉ ስነ-ስርዓት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከተለያዩ ድርጊቶች ጎን ለጎን የተለያዩ ክዋኔዎች በወንዶችም ሆነ በሴቶች ይቀርባሉ፡፡

## 4.2.1 የሰርግ ክብረ በዓል ላይ የሚከወኑ ቃል ግጥሞች

ግጥም 1. እንዳላይሁ፣

ዳመናው ሳለ በላይሁ፡፡

ይህ ግጥም ከወንድም ሆነ ከሴት ሙሽራ ቤት የሙሽሮችና መውጣት እና መግባት ምክንያት በማድረግ በሴቶች የተዘፈነ ቃል ግጥም ነው፡፡ የሙሽሮች ክብር ምን ያህል እንደሆነ የሚጠቁም ግጥም ነው፡፡ ሰዎች የሚያውቁትና ያሳደጉት ልጅ ሙሽራ በመሆኑ ምክንያት እንዳይታይ የሚያደርገው የሆነ ሀይል ያድርበታል ብለው ያምናሉ፡፡ ሙሽራ መሆን ትልቅ ዋጋ ያስጠዋል፡፡ በመሆኑም ይጠበቃሉ፤ የተለየ ክብርና ደረጃ ይሰጣቸዋል፡፡ በሙሽርነት ጊዜያቸው በፊት የነበራቸውን ማንነት ትተው ሌላ አዲስ ማንነት ይይዛሉ፡፡

በአካባቢው ዳመና፣ ጸሀይ፣ ዝናብ፣ የፈጣሪ ስራዎች ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ በደመና ምንም ነገር በግልጽ እንደማይታይ ሁሉ ሙሽሮችም የሰርጋቸው ቀን ማንም ሰው እንደፈለገ አያያቸውም፡፡ እንደልብ አለመታየታቸውን ለማመልከት እንዲህ አይነት ግጥሞችን ይገጥማሉ፡፡

ግጥም 2. ካባ ልበስ ምንድነው ልበስ ምንድነው፣

ሞትና ሰርግ አንድ ነው ልበስ ምንድነው፡፡

ይህ ቃል ግጥም ሙሽራው ሲወጣ ሴቶች እየተቀባበሉ የዘፈኑት ነው፡፡ አንዲት ሴት ብቻዋን ካዜመችው በኋላ ሌሎች እሷን ተቀብለው ያዜማሉ፡፡ የተወሰኑት መሀል ላይ ሆነው እስክስታ ያወርዳሉ፡፡ በዚህ ግጥም ካባ መልበስ፣ ሞትና ሰርግ አንድ ነው የሚሉትን ቃላትና ሀረጋት ፍቺ በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው በአካባቢው ባህል መሰረት በለቅሶ ጊዜ ሀዘንተኞች፣ በሰርግ ጊዜ ደግሞ ሙሽሮች ካባ በመልበሳቸው ያንን ተመሳስሎ ለማመልከት የተጠቀመበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሁለቱም የወዳጅዘመድ መሰባሰቢያና መገናኛ መሆናቸውም እንደምክንያት ይታያል፡፡

ከዚህ ባሻገር ሞትና ሰርግ ሁለት ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ስሜቶች የሚስተናገዱባቸው የህይወት ሁነቶች ናቸው፡፡ ሰርግ በዋናነት ትውልድን ወደፊት ለማስቀጥል ሲባል የሚፈጸም በመሆኑ በደስታ፣ በእልልታ፣ በዘፈን፣ ይከናወናል፡፡ በተቃራኒው ሞት ደግሞ ህይወት የሚያበቃበት ቅጽበት በመሆኑ ስርዓቱ ከዋኔው የሚፈጸመው በከፍተኛ ሀዘንና ለቅሶ ነው፡፡ በቃል ግጥሞቻቸው ግን ሞትና ሰርግ አንድ ነው እያሉ የሁለቱን ተመሳሳይነት ይገልጻሉ፡፡

ይህ የሚያመለክተው ማህበረሰቡ ለሰርግና ለሞት ያለው አመለካከት ተመሳሳይ መሆኑን ነው፡፡ በአካባቢው ባህል መሰረት ሞትና ሰርግ ትኩረት የሚደረግባቸው የህይወት ዑደቶች ናቸው፡፡ ሰዎች በህይወት ዘመናቸው የመጨረሻ ደስታቸውን የሚያዩት ልጃቸውን ሲድሩ ነው፡፡ ትላቅ ግምት በመስጠታቸው ያለ የሌለ ሀብትና ንብረት ወጥቶ ተደግሶ ወዳጅ ዘመድ ይጠራል፡፡ የተጠሩ ሰዎች ከቀሩ በመካከላቸው ቂም ይፈጠራል፡፡ ምክንያቱም ልጅን ከመዳር፣ የበለጠ ደስታ የለም ተብሎ ስለሚታመን ወዳጅ ዘመድ የደስታ ተካፋይ መሆን አለበት የሚል አመለካከት አላቸው፡፡

ማህበረሰቡ በሰርግ ደስታውን እንደሚጋራ ሁሉ በሞት ጊዜም ሀዘኑን ይካፈላል፡፡ ቀብር ላይ በመገኘት፣ ለቀስተኛውን በማስተናገድ፣ ሀዘንተኞችን በማጽናናት፣ የሟችን ተዝካር በማውጣት ሀዘንን ይጋራሉ፡፡ ሰርግ ላይ የማይገኝ ወዳጅ ዘመድ እንደማይወደድ ሁሉ ለቅሶ ላይ ያልተገኘ ሰውም እንዲሁ ለመጨረሻ ጊዜ ከዝምድና ይገለላል፡፡ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት እንኳን የእጥንት ክፋይ የስጋ ቁራጭ የሆነ ሰው ይቅርና ሟችን የማያውቀው የአካባቢው ነዋሪ ለቅሶ ላይ መገኘት አለበት፡፡

ሞት ሟችን ከቤተሰብ፣ ከማህበረሰብ ብሎም ከአለም ለዘላለም የሚነጥል የህይወት ቅጽበት በመሆኑ የሚያስከትለው ሀዘን ልብን ይሰብራል፣ መንፈስን ይጎዳል፡፡ በመሆኑም የአካባቢው ሰው ተገኝቶ ሊያለቅስ፣ ሊያዝን ይገባል፡፡ ለአካባቢው ማህበረሰብ ሞትና ሰርግ እኩል ዋጋ አላቸው፡፡ ከዚህም የተነሳ ከበራቸው ሲከፈድ ተመሳሳይ ነገሮች ይስተዋላሉ፡፡ ካባ መልበስ ሁለቱም ላይ የሚስተዋል ጉዳይ ነው፡፡ በሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ ሙሽሮች ካባ ለብሰው ነው ከቤታቸው የሚወጡት እንዲሁም በለቅሶ ጊዜ ሀዘንተኞች ከቀብር ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ተከታታይ ቀን ድረስ ካባ ይለብሳሉ፡፡

ሰርግ ላይ ሙሽሮች የሚለብሱት ካባ ነገስታት ከሚለብሱት ጋር የሚገናኝ በመሆኑ ጥሩ ነገርን ወክሎ ይቀርባል፡፡ ትርጓሜውም ክብር፣ ልዩነት፣ እነሱን ከሌላው ማህበረሰብ ለመለየት ነው፡፡ ሙሽሮች በሰርጋቸው ቀን እንደ ንጉስና ንግስት ይታያሉ፡፡ በለቅሶ ጊዜ የሚለብሱት ካባ ሀዘንተኞች የጉስቁልና፣ የጨለምተኝነት፣ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ እንዳሉ ያመለክታል፡፡ የካባው ዓይነቱ፣ አለባበሱ ተመሳሳይ ሆኖ የሚቀርብበት አጋጣሚ ግን ትርጉሙን ሙሉ በሙሉ ሲለውጠው ይስተዋላል፡፡ ይህም የአንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ ፍቺ የሚወሰነው በሚቀርብበት አውድ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ግጥም 3. ሙሽር አበባ፣

አይዞህ ልብህ አይባባ፡፡

ይህ ቃል ግጥም ከሴትም ሆነ ከወንድ ሙሽራ ቤት የሚባል ነው፡፡ ሙሽራው ሲወጣ እና ሴቷ ሙሽሪት ከቤተሰቦቿ ስትሰናበት ማለትም ሙሽሮች ስወስዷት ተዘፈነ ዘፈን ነው፡፡ እዚህ ላይ ለምን አበባ እንደተባሉ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ አበባ የእጽዋት የመራቢያ ክፍል ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ግጥም ሙሽራው አበባ ሆኖ ተገልጿል፡፡ እጽዋት ለመራባት ዝግጁ ሲሆን አበባ ያብባል፡፡ አበባው በጊዜ የወንዴ ዘር ካገኘ ለፍሬ ሲበቃ ካላገኘ ግን ይረግፋል፡፡ ይህንን የእጽዋት ባህሪ ማህበረሰቡ ወደ ራሱ በማምጣት በተምሳሌትነት ይጠቀምበታል፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሰርግ የሙሽሮች አበባ የሚታይበት ቀን ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ እዚህ ላይ አበባ የወከለውን ነገር መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ ሙሽራው የሙሽሪትን ክብረ ንጽህና ሲወስድ የሚፈሰውን ደም ለመጠቆም የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ የአበባ ፍቺ ይህ እንደሆነ የወር አበባ የሚለውን ሀረግ ማየት ይቻላል፡፡ ሙሽሮችም በሰርጋቸው ቀን እንደ አበባ ቀልብ የሚስቡበት፣ የሚዋቡበት፣ በደስታ የሚፈነድቁበት እለት በመሆኑ በግጥሞቻቸው ሁሉ "አበባ" የሚል ቃል ይጠቀማሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በተለይ ሴት ልጆቻቸውን የሚድሩ ወይም የዳሩ ሰዎች "የልጄን አበባ አየሁ" በማለት ይናገራሉ፡፡ በምርቃንም የልጆቻችሁን አበባ፣ ፍሬ ለማየት ያብቃችሁ እየተባለ ይመረቃል፡፡ ስለሆነም እዚህ ቃል ግጥም ውስጥ አበባ የሚለው ቃል የሴቷን ክብረ ንጽህና ወክሎ የቀረበ ነው፡፡ አበባ የፍቅር ስጦታ መሆን፣ ፍቅርን ለመግለጽ የሚሰጥ መሆኑ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ በዚሁ ቃል ግጥም ውስጥ "ልብህ አይባባ" የሚለው ሀረግ ሙሽሮች እንዳች ልብ የሚያባባ፣

የሚያስጨንቅ እንግዳ ነገር የሚያዩበት እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ይህም ሲባል ሙሽሮች በሰርጋቸው ቀን ከዚህ በፊት አይተውት ወደማያውቁት ሌላ አለም የሚሸጋገሩበት ነው፡፡

የሰርግ ቀን ባልና ሚስቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈጽሙበት ነው፡፡ ይህም ከተለያዩ ነገሮች አንጻር የወንዱንም ሆነ የሴቷን ልብ ያስጨንቃል፡፡ በወንዱ በኩል ምናልባት ካልሆነለት በጓደኞቹም ሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ይናቃል፣ መሳቂያ መሳለቂያም ይሆናል፡፡ ይህ ነገር ገና መሞሸር ሲጀምር ያስጨንቀዋል፡፡ በሴቷ በኩል ደግሞ የመጀመሪያዋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሊሰማት የሚችለውን ስሜት እያሰበች ትጨነቃለች፣ ታስባለች፡፡ በመሆኑም ታዳሚው ሙሽሮቹ መጨነቅ እንደሌለባቸው፣ ነገሩን በድፍረት ማድረግ እንዳለባቸው አይዞህ! ወይም አይዞሽ! እያሉ በግጥሞቻቸው ይዘፍኑላቸዋል፡፡

ግጥም 6. ሎሚ ጣልባት በደረቷ፣

የጨዋ ልጅ ናት መሰረቷ፡፡

ይህ ቃል ግጥም በዋናነት ከሴት ሙሽራ ቤት በሴቶች አማካኝነት የሚከወን ሲሆን ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ለመተንተንና ለመተርጎም ግጥሙ የቀረበባቸውን ቃላትና ሀረጋት መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ "ሎሚ ጣልባት" የተባለው ለምንድን ነው፣ በደረቷ የተባለውስ ለምንድን ነው፣ ሎሚ መጣልና የጨዋ ልጅ መሆን ምን ያገናኘዋል፣ የሚሉትን ጥያቄዎች በመያዝ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ሎሚ የፍቅር መገለጫ ነው፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች ወንዶች ፍቅራቸውን ለመግለጽ ሎሚ በመወርወር የሚመቷቸውም ደረታቸውን ጡታቸው አካባቢ ነው፡፡ ይህም ምኞትንና ፍላጎትን ያሳያል፡፡

ሎሚ ለጨዋ ዘር እንጂ በማህበረሰቡ አጠራር "ለማንም" አይጣልም፡፡ በድሮ ጊዜ ሎሚ የሚጣልላቸው ለነገስታት ልጆች ብቻ ነበር፡፡ በዚህ ቃል ግጥም ሎሚ በርካታ ውክልናዎች አሉት፡፡ በአካባቢው ባህል መሰረት ወንድ ለሴት የሚጥለው ጥሎሽ እንደቤተሰቡ የኑሮ ደረጃ ይለያያል፡፡ ሀብት ያለው ወርቅ፣ ብር ከዚህም በላይ ማቅረብ ሲችል የሌለው ደግሞ ቢያንስ ሙሉ ልብስ የማልበስ ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑም ሎሚ ከወንድ ለሴት ሙሽራ የሚበረከት ማንኛውም ስጦታ ነው፡፡ በግጥማቸው ለሙሽራዋ አንድም ጥሩ ጥሎሽ እንዲጣልላት ሌላም "የጌታ ልጅ ናት መሰረቷ" በማለት ማንነታቸውን ይገልጹበታል፡፡

ሙሽራዋ የጨዋ ልጅ ናት በማለት ነን ለነን እኛ የጨዋ ዘር ጨዋ ነን የሚል መልእክት እያስተላለፉ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ግጥም 7. እያ ንሳ ንሳ፣
እንዳታበላት ዳጉሳ፡፡

ይህ ቃል ግጥም ሙሽራዋ ስትሰናበት በሴቶች የሚከወን ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ዳጉሳ ዝቅተኛ ሀብት ያለው ሰው የሚመገበው የእህል አይነት ነው፡፡ "እንዳታበላት ዳጉሳ" የሚለው ሀረግ በቀጥታ ከዳጉሳ የተዘጋጀ እንጀራ እንዳያስበሏት የሚያስጠነቅቁበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እነሱ የሚበሉት ጤፍ እንጀራ ሙሽራዋም የለመደችው ያንን ነው፡፡ በሙሽርነት ጊዜዋ ዳጉሳ እንዳትበላ በማለት የእነሱን ግላዊና ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ሲያደርጉ የተቃራኒያቸውን ደግሞ ዝቅ ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም በቃል ግጥሞቻቸው አማካኝነት በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ደረጃ ይገልጻሉ፡፡

ግጥም 8. የሙሽሪት እናት በላይ ይቀመጡ፣
የሙሽሪት አባት በላይ ይቀመጡ፣
አሳድገዋታል እየቆነጠጡ፡፡

ይህ ግጥም የመልስ ቀን በወንድ ሙሽራ ሚዜዎች የሚከወን ለሙሽሪት እናትና አባት ክብር የሚዘፈን ነው፡፡ የዘፈኑ መልእክት ልጅን እየቀጡ ማሳደግ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ ልጆች ሲያድጉ ካልተቆነጠጡ ባለጌ ቤተሰብ አሰዳቢ ይሆናሉ ተብሎ ያታሰባል፡፡ በመሆኑም በተቻለ መጠን ልጅን ቀጥቶ ለማሳደግ ይሞከራል፡፡ ሙሽራው የሙሽሪትን ክብረ ንጽህና ከወሰደ የእሷ ቤተሰቦች ደረጃ ከፍ ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ ለሙሽራው ቤተሰቦች 'ብር አምባር ሰበረልዎ ጀግናው ልጅዎ' እየተባለ ሲዘፈን ለሴቷ ቤተሰቦች ደግሞ ከላይ የቀረበው ዘፈን ይዘፈንላቸዋል፡፡

በማህበረሰቡ ባህል መሰረት የአቀማመጥ ቅደምተከተል የራሱ የሆነ ተዋረድ አለው፣ በተገኘው ቦታ ሁሉ ከመቀመጥ በፊት እድሜን፣ ጾታን፣ ማህበራዊ ደረጃን ለይቶ በተገቢውና በሚመጥናቸው ቦታ መቀመጥ አለባቸው፡፡ መነኩሴ፣ ሽማግሌ፣ ቄስ ከላይ የሚቀመጡ ሲሆን ባልቴት፣ ጎልማሳ፣ ወጣት፣ እያለ እስከ ህጻናት ድረስ የሚመጥን ቦታቸው ላይ መቀመጥ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ቦታ አንዱ የእያንዳንዱን ሰው ማህበራዊ ደረጃ

የማመልከት አቅም አለው፡፡ የማህበረሰቡ የሙሽራዋ እናትና አባት ልጃቸው በክብር ስለተገኘች እነሱም ክብር ይገባቸዋል፤ ከላይ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህ የሚያመለክተው በማህበረሰቡ ውስጥ ክብረ ንጽህና የሙሽራዋን ደረጃ ከማሳደጉም በላይ የቤተሰቦቿም የአስተዳደግ ብቃት የሚያመለክት በመሆኑ በሰው ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚያሰጥ መሆኑን ነው፡፡

### 4.2.2 የሰርግ ስነ-ስርዓት ማሳረጊያ ምርቃቶች

መልስ የሰርግ ስነ ስርዓት የሚጠናቀቅበት ክዋኔ ነው፡፡ ከሰርጉ እለት በኋላ የሚጉላ ቆይታቸውን ጨርሰው ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀሉበት ስርዓት ነው፡፡ በመልስ ስነ-ስርዓት ሙሽራውም ሚስት ስላገኘ፣ ከነክብረ ንጽህናዋ ስላገኛት ለቤተሰቦቿ ያለውን ክብር ለመግለጽ በግ አርዶ ያስረክባል፡፡

በመልስ ስነ-ስርዓት የሚቀርቡ ምርቃቶች በክርስትና ጊዜ ከሚቀርቡት በይዘት የተለዩ ናቸው፡፡ ምርቃቶች ሰርጉን ተንተርሰው የሚመጡ በመሆናቸው የሰርግ አውድ በሌለበት ቢከወኑ ምንም ዋጋ የሌላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ባልና ሚስቱ ከሰርጉ እስከ ግላጩ ቀን ባለው ጊዜ በመንፈስም ሆነ በስጋ ተዋህደዋል ተብሎ ስለሚታመን ምርቃቶች በሙሉ ወደሚወልዱት ልጅ ያነጣጥራል፡፡ በዚህ ጊዜ ከሚቀርቡ ምርቃኖች መካከል የሚከተሉትን በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ምርቃት 1. ወንድ ወልዳችሁ ለፈረስ፤ ሴት ወልዳችሁ ለበርኖስ አድርሱ፤

በዚህ ምርቃት ውስጥ ሙሽሮች አይናቸውን ባይናቸው ከማየትም ባሻገር ወንድ ከወለዱ ፈረሰኛ እንዲሆን፣ ሴት ከወለዱ በጥሞ ለበርኖስ እንዲሆኑላቸው መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ፈረሰኛ ማለት ጦረኛ፣ አገር የሚያስከብር፣ ጀግና ማለት ነው፡፡ ጀግና ወንድ በማህበረሰቡ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ ለቤተሰብ፣ ለዘመድ ብሎም ለሀገር ኩራት ነው፡፡ ስለሆነም ሙሽሮች የሚወልዱት ልጅ ጀግና እንዲሆን ካላቸው ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ከማንጓላ እንደወጡ በምርቃን ይነገራቸዋል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ወንድ ልጅ ጠላት በመጣ ጊዜ ጦሩን ሰብቆ ጋሻውን አንግቦ፣ ቤቱ ንብረቱ ሳይል መውጣት አለበት፡፡ ለታዳሚው (ተሳታፊው) ለጠላት የማይንበረከክ ጀግና እንዲሆን መልእክት ማስተላለፊያ ዘዴ አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡

ሴት ወልዳችሁ ለበርኖስ' የሚለውን ሀረግ ስንመለከት ይህ ምርቃን በቀረበበት አውድ ውስጥ በርኖስ ማለት የሴት ወይዘሮ ማለት ነው፡፡ የሚወልዷት ልጅ ቤተሰቦቿን የምታስከብር፣ የንገስታት፣ የቀኝ አዝማች፣ የግራ አዝማችና የመኳንንት ባለቤት፣ እመቤት፣ ወይዘሮ እንድትሆንላቸው ምኞታቸውን የሚገልጹበት ነው፡፡ ባጠቃላይ በዚህ ምርቃት ማህበረሰቡ ስርዓተ ጾታ፣ ጀግንነት፣ ሴትነት፣ ወንድነት የሚሉ ሀሳቦች ምን ያህል ዋጋ እንዳላቸው ያሳያል፡፡

ማህበረሰቡ በምርቃቱ ውስጥ ወንድ ምን መሆን እንዳለበት፣ ሴት ምን መሆን እንደሚገባት እንዲሁም በባህሉ መሰረት ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ ያሳያል፡፡ በማህበረሰቡ አመለካከት የጀግንነት መገለጫ ጦረኛነት እንደሆነ፣ ሴትነት ማለት ደግሞ የነገስታት ሚስት፣ እመቤት መሆን፣ እንደሆነ፣ ወንድነት ማለት ደግሞ አልደፈር ባይነት፣ የሀገር ኩራት ማለት እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ምርቃት 2. አስራ አምስት ወልዱ፣ አምስቱ ለፈረስ፣ አምስቱ ለመቅደስ፣ አምስቱ ለበርኖስ ይሁኑ፡፡

በዚህ ምርቃት "ለፈረስ"፣ "ለመቅደስ" እና "ለበርኖስ" የሚሉት ቃላት የተሸከሟቸው ሀሳቦች በማህበረሰቡ ዘንድ የሚተከርባቸውና እኩል ዋጋ የሚሰጣቸው መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ፈረሰኛ ማለት ጦረኛ፣ አርበኛ፣ ሀገር በእሱ እንዲከበር፣ ወንዛቸው እንዳይደፈር ተፈልጎ ነው፡፡ ለበርኖስ ማለት ደግሞ ሙሽራ የሚሆኑ፣ በርኖስ እሚለብሱ እና ወይዘሮ እንዲሆኑ ተፈልጎ ሲሆን ለመቅደስ ማለት ደግሞ ለሃይማኖታቸው አገልጋይ ተምረው ቄስ እሚሆኑ፣ እሚያጠምቁ ይሁኑ ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ብዙ ሁኑ በአደባባዩ፣ በመቅደሱ የእናንተ ልጆች ይታዩ ለማለት ነው፡፡ እንዲሁም ሁሉም አምስት አምስት መሆናቸው ሁሉም እኩል ዋጋ እንደተሰጣቸው አንዱ ማሳያ ነው፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአካባቢው ማህበረሰብ ማንነት መገለጫዎች ጦርነት፣ ሃይማኖትና ሙሽራ መሆን ናቸው ማለት የአካባቢው ማህበረሰብ ለሃይማኖት፣ ለሀገር እና ለሴት ያለውን እኩል ዋጋ ለማሳየት የተጠቀመበት ስልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የማህበረሰቡ ህልውና የተመሰረተው በእነዚህ ሶስት ነገሮች ነው ብሎ ያምናል፡፡ እነዚህን ሁነቶች ከምርቃቶች በተጨማሪ በቃል ግጥሞቻቸው እና በሌሎች ባህላዊ አገላለጾቻቸው ደጋግመው ሲገልጹ ይስተዋላሉ፡፡

### ምርቃት 3. አጥር ቀስቋሽ ነገር አመላላሽ አያድርግሽ፣

ይህ ምርቃት በዋናነት ለሴት ሙሽራ የሚመርቁት ነው፡፡ ምርቃቱም ሙሽራዋ በማህበረሰቡ ዘንድ የተጠሉ ተግባራትን እንዳትፈጽም የሚያደርግ ነው፡፡ ማለትም "አጥር ቀስቋሽ" እና "ነገር አመላላሽ" አንዲት ሴት መሆን የሌለባት የተወገዙ ባህሪዎች ናቸው፡፡ አጥር ቀስቋሽ ማለት ሰዎች ምርታቸውን ከብት እንዳይበላባቸው በእንጨት አጥር ይከልላሉ፡፡ ለማገዶ የሚሆን እንጨት ያጡ ሴቶች ከዚያ አጥር ሰርቀው በመውሰድ ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ምርቃት ሌብነትን ለመቃወም የተጠቀሙበት ነው፡፡

ነገር አመላላሽ ማለት ወሬኛ ማለት ነው፡፡ በሴት የመጣ ወሬ አይበርድም፣ እስከ ነፍስ መጥፋት ያደርሳል፡፡ በተጨባጭ በሴቶች በሚወራ ወሬ ምክንያት ብዙ ነፍስ ጠፍቷል፣ በዚህ ምክንያት ብዙ ቤተሰብ ከመኖሪያ ቦታው ተፈናቅሏል፡፡ በመሆኑም ሴት ፈጽሞ ወሬኛ መሆን የለባትም የሚል አመለካከት አላቸው፡፡ ሴት ወሬኛ መሆን የለባትም በሚለው እንስማማ እና ከሴት የመጣ ወሬ እስከ ግድያ የሚደርሰው ለምን እንደሆነ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ሴት ምንም የማታውቅ፣ ወንድ ደግሞ አዋቂ፣ አላፊ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገር ግን ከወንዶች ይልቅ ሴቶች የሚያወሩትን ግን ችላ ብሎ ለማለፍ የሚያስችል አቅም የላቸውም፡፡ ይህ የሚያሳየው የሴቶችን አላዋቂነት፣ አይሰሜነት ሳይሆን ከባድ ነገሮችን የማስፈጸም አቅም እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በማህበረሰቡ ህልውና ላይም ቀውስ ያስከትላል፡፡ በመሆኑም ሴቶች የተሰማቸውን እንዳይናገሩ የሚያስገነዝቡበት እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

### ምርቃት 4. በወንድ ልጅ ተበከሪ፣

ይህ ምርቃትም በአብዛኛው ለሴት ሙሽራ የሚመረቅ ሲሆን መጀመሪያ ወንድ ውለጅ እንደማለት ነው፡፡ ከላይ እንዳስረዳሁት ወንድ የሚለው ቃል ጾታን ከማመልከት ያለፈ ትርጉም አለው፡፡ ወንድ የሚለው ቃል ጀግንነት የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ይጠራል፡፡ ስለዚህ ወንድ በመጀመሪያ አባቱን ያስጠራል፣ ደም ይመልሳል፣ ቤተሰቦቹን እና አገሩን ያስከብራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በመሆኑም አንዲት እናት ለመጀመሪያ ጊዜ ወንድ ስትወልድ የተለየ ስነ-ስርዓት ባይከሄድም የደስታቸው መጠን ግን እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ ማህበረሰቡም ለራሱ ካለው ክብር የተነሳ የሚወለደው ልጅ አንዳች ጀብዱ ሰርቶ ስማችንን ብሎም አገራችንን ያስጠራናል ብሎ ከማሰቡ የተነሳ በምርቃቱ ውስጥ ይጠቀምበታል፡፡

ምርቃን 5. የምትወልዱት ልጅ መንፈሳዊ ቢሆን እንደ እንጦስ እንደ መቃርስ፤ ስጋዊ ቢሆን እንደ ቆስጠንጢኖስ እንደ አኖሬዎስ ይሁን፤

እንጦስ እና መቃርስ የግብጽ መነኩሳቶች ሲሆኑ በንጽህና በቅድስና የታወቁ ናቸው፡፡ ቆስጠንጢኖስ እና አኖሬዎስ በሮም የነበሩ ታላላቅ ነገስታት ናቸው በህይወት ዘመናቸው ሃይማኖታቸው የጸና ምግባራቸው የቀና ታላላቅ ነገስታት ስለሆኑ እንደነሱ እንዲሆን ተፈልጎ ነው፡፡

ይህ ምርቃት በቀጥታ ከማህበረሰቡ እምነት ጋር ይገናኛል፡፡ ሰው በህይወት ሲኖር አንድም እንደ እንጦስና እንደ መቃርስ ፍጹም መንፈሳዊ ወይም እንደ ቆስጠንጢኖስ እንደ አኖሬዎስ ሲጋዊ ሆኖ እግዚአብሄርን የሚያስደስት ምግባርና ተግባር ሊኖረው እንደሚገባ ለማመልከት ነው፡፡ ይህም ሃይማኖታዊ ታሪኮችን እየጠቀሱ አሁን ያለውና ወደፊት የሚኖረው ትውልድ ሃይማኖቱን እንዲያጠነክር፣ በኑሮው ጎበዝ እንዲሆን የመንገሪያ ስልት ነው፡፡

ማህበረሰቡ ሁለት የተለያዩ አለማትን የሚገናዘብበት የሚለካበት ሚዛን አለው፡፡ የመንፈሳዊ ህይወት ስኬት ምንኩስና ሲሆን የአለማዊ ህይወት ስኬት ደግሞ ንግስና ነው፡፡ ይህ ልጅ ከሁለቱ የህይወት መንገድ አንዱን የመከተል ሙሉ መብት ቢኖረውም መሆን ያለበት ነገር አለው፡፡ አንድም እስከ ምንኩስና የሚደርስ መንፈሳዊነት ወይም ንጉስ እስከመሆን የሚደርስ ስኬት ጫፍ ላይ መድረስ አለበት፡፡

ባጠቃላይ የሰርግ ክብረ በዓል ማሳረጊያ ላይ የሚመረቁ ምርቃኖች ትኩረት ከሙሽሮች ይልቅ ወደሚወለደው ልጅ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡ ምርቃኖች የተዋቀሩባቸው ቃላትና ሀረጋት የተሸከሟቸው ጽንሰ ሀሳቦች ማህበረሰቡ እየኖረ ያለበትን ርዕዮተ አለም ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ማለትም ሴትና ወንድ በማህበረሰቡ ባህል ምን ቦታ እንዳላቸው፣ ለማህበረሰቡ ህልውና ሃይማኖት፣ ሀገር፣ ሚስት፣ ጀግንነት ትልቅ ዋጋ እንዳላቸው፣ እንደ ስርቆት፣ ወሬ በማህበረሰቡ ዘንድ የማይወደዱ ምግባሮች እንደሆኑ፣ ከምርቃኖች ትንታኔ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ማህበረሰቡም በምርቃን የሚወደዱ እሴቶችን ያበረታታል- የሚጠሉትን ደግሞ ይነቅፋል፡፡

## 4.3 የለቅሶ ስርዓት ከዋኔ

ከሰው ልጅ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ሁደቶች መካከል የመጨረሻው ሁነት ሞት ነው፡፡ ሞት በአካባቢው ባህልና እምነት መሰረት ሰው አለም ላይ ሲኖር ለሰራው ማንኛውም ተግባር ፍርዱን የሚያገኝበት ሌላ ዘላለማዊ አለም ነው፡፡ ሞት ሁልጊዜም ያለና የሚጠበቅ ቢሆንም በትክክል መቼ ሊከሰት እንደሚችሉ ባለመታወቁ የሟች ነፍስ በጠፋበት በማንኛውም ቦታና ጊዜ የሀዘን መግለጫ ስነ-ስርዓት ይከናወናል፡፡ ስነ-ስርዓቱም የሟቹን ዘላለማዊ ስንብት የሚገልጽ ስለሆነ ከዋኔው ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል (ሂል እና ዳኔልስ፣ 2008፣ 380)፡፡

ሰው በአለም ላይ ሲኖር ኑሮውን ለማሸነፍ፣ ፍላጎቱን ለማሟላት እንዲሁም ህይወቱን በጥሩ ሁኔታ ለመምራት የተለያዩ ሰናይና እኩይ ተግባሮችን ይፈጽማል፡፡ እድሜው እየገፋ ሲሄድ ገደኑ አላይም የማለት፣ ጆሮው አልሰማም የማለት፣ እግሩና እጁ አልታዘዝም የማለት፣ የመድከም፣ የማንገበስ፣ የመዘንጋት ባህሪ ይታይበታል፡፡ እድሚያቸው እየገፋ ሲሄድ በእምነታቸው መሰረት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ ይጠብቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሰው ይጸጸታል፣ ይመለሳል፣ ይቆርባል፣ ይሰግዳል፣ አድባራት ገዳማትን ይሳለማል፡፡ የበደለውን ይቅር በለኝ እያለ ይታረቃል፡፡ ይህ ማለት እንግዲህ ወደ መቃብር የሚደረግ ጉዞ ነው፡፡ አለም ላይ ለመኖር ከመጓጓት ይልቅ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ይታይበታል፡፡ ያሳለፈው ጊዜ ይቆረቁረውና ወደ መንፈሳዊ ህይወት ይመለሳል፡፡[36]

ከላይ የቀረበው ሀሳብ እንደሚያስረዳው የሰው ሞት የሚጀምረው ገና በህይወት እያለ መሆኑን ነው፡፡ ማለትም ማህበረሰቡ ከሞት በኋላ ለሚኖርበት አለም ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት የቅድመ ሞት ተግባራት በማህበረሰቡ አስተሳሰብ መሰረት ከአምላክ ዘንድ ምህረት ያስገኛሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ገነትን ወይም መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ የሚያበቁ ናቸው፡፡ ቀሪ ጊዜያቸውንም መልካም ስራዎችን እያከናወኑ ይቆያሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች አለም ለምኔ በማለት ቤተሰባቸው፣ ዘመዳቸውን፣ አገራቸውን፣ ቤት ንብረታቸውን ትተው ወደ ገዳማት ይሰደዳሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ተግባራትን ስለፈጸሙ ስነ ልቦናዊ እረፍት ያገኛሉ፡፡ አንድ ቀን ህይወታቸው ሲያልፍ ሲጠብቁት ወደ ነበረው አለም ሄዱ ተብሎ ይታመናል፡፡ ከለቅሶ ስነ-ስርዓቱ ጎን ለጎን የሚከናወኑ ጉዳዮችን

---

[36]አቶ ዘለቀ መንግስቱ ናዝሬት ጊዮርጊስ የሚኖሩ ሲሆን በሚያዝያ 17 ቀን በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ነው፡፡

በመመርኮዝ የቅድመ ሞት እና ድህረ ሞት ስርዓተ ክዋኔዎች በማለት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡ አንድ ሰው ነፍስ እና ስጋው ሲለያይ ሟች የሚታይበት ምልክቶች አሉ፡፡ አቶ ሙሉ የሚከተለውን ሀሳብ ነግረውኛል፡፡

> አንድ ሰው ህይወቱ ሊያበቃ ሲል ሰውነቱን አፈር ያለብሰዋል፡ ዓይኑ ይለወጣል፡ እጅ እግሩ ይዝላል፡ ፊቱ ይጎደጉዳል፡ በመጨረሻም ዓይን ምድር ይጥላል፡፡ በዚህ ጊዜ ህይወቱ አበቃ ማለት ነው፡፡ ከዚያ ይሞሀል፡ ሰው ይሰበሰባል፡ ራቅ ያለ ቦታ ላሉ ወዳጅ ዘመድ ይላካል፡ አስከሬኑም ይታጠባል፡ ጸጉሩ ይላጫል፡ ሰውነቱ ይስተካከላል፡ ይገነዛል፡ ይከፈናል፡ ከዚያም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄድና መቀበር ያለበት ቦታ ይቀበራል፡፡[37]

የሰው ልጅ በዚህ መልክ የኖረባትን አለም ይሰናበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ቤተሰብ፡ ወዳጅ ዘመድ የሟችን መልካምነት እያሰበ አብሮት የኖረው ሰው ሲለየው ሀዘኑን በለቅሶ ይገልጻል፡፡ ሟች በጣም እድሜው ከገፋ ሌላ ሰው ያስከትላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ማህበረሰቡ አስከሬን ከመውጣቱ በፊት ቤቱን ይቀዱና ሞት በዚያ ይወጣል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህም ሞትን ረቂት አድርጎ ከማሰብ ተጨባጭ አድርገው በማሰባቸው መውጫ ቀዳዳ እስከማበጀት ይደርሳሉ፡፡ እንዲህ የሚያደርጉት ሞት ሰው በሚወጣበት በር ከወጣ ሊገድላቸው እንደሚችል ማሰባቸው እና ለሞት ያላቸውን ፍራቻ እንዲሁም ራሳቸውን ለመጠበቅ ካላቸው ፍላጎት የመነጨ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ስርዓተ ግንዘት እንደየሰው ማንነት ማለትም ጾታ፡ እድሜ፡ ማህበራዊ ደረጃ፡ የተለያየ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ መርጌታ ስሜነህ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ "የተለያየ የአገናነዝ ስርዓት አለ፡፡ ሁሉም ሰው የሚገነዘው ሰባት ላይ ቢሆንም የሊቃውንትና የቀሳውስት፡ የዲያቆናት፡ የጨዋ፡ የሴቶች፡ የህጻናት የተለያየ ነው፡፡ ፍታቱና ጸሎቱም ይለያል፡፡"[38]

የለቅሶ ክዋኔ እንደ ሟች ማንነት፡ ማህበራዊ ደረጃ፡ ጾታ እና እድሜ የተለያየ ነው፡፡ ቄስ፡ ወታደር፡ ወንድ፡ ሴት፡ ህጻን፡ አዋቂ በሚሞቱበት ጊዜ የሚፈጸመው ስርዓተ ክዋኔ እንደየባህሉና እንደየማህበራዊ ደረጃቸው የተለያየ የአለቃቀስ ስርዓትና ደንብ አላቸው፡፡ የሟች ቤተሰብ፡ ጓደኛ፡ ዘመድ ወዳጅ ሁሉም የራሳቸው የሆነ የአለቃቀስ ስልት አላቸው፡፡ በዚህም የእያንዳንዱ አልቃሽ ማንነት ይታወቃል (ግሪምስ፡ 1943፡ 218)፡፡

---

[37] ወ/ሮ ሄደን አስመሮም ፍርን ቀበሌ ነዋሪ ሲሆኑ ፍኖተ ሰላም ከተማ በሚገኘው መድሃኒያለም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሚያዝያ 13 ቀን በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ነው፡፡

[38] ከመርጌታ ስሜነህ አበበ ጋር ባደረግሁት ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ነው፡፡

የለቅሶ ከዋኙ ላይ ተገኝቼ እንደተመለከትኩት አስከሬኑ ማልቀሻ ቦታ ላይ ሆኖ ሴቶችና ወንዶች እየዞሩት ያለቅሳሉ፡፡ ለቅሶ ላይ ከተገኘው ማህበረሰብ መካከል ሙሾ ማውረድ የሚችል ሁሉ በየተራ እየተቀባበለ ሟቹን የሚያወድሱ እና የሚያመሰግኑ ሰብእና የሚገልጹ ጉዳዮችን በግጥምና በዜማ እያዋሃዱ ያስለቅሳሉ፡፡ የሟች የቅርብ ቤተሰብ ነጠላና መቀነት በወገባቸው አስረው ልብሱን እየወዘወዙ ያለቅሳሉ፡፡ በተለይ የቅርብ ዘመዶች አለባበስ ከሌላው የተለየ ነው፡፡ ሴቶች ነጠላቸውን ለሶስት አጥፈው፣ ወይም ነጠላቸውን ከኋላቸው ከእንገታቸው እስከ ታች ተሚሳቸው ጫፍ ድረስ ለብሰው ወገባቸው ላይ ከነጠላው በላይ በመቀነታቸው ያስሩታል፡፡ እንዲሁም ከዚህ በፊት የሞቱ ዘመዳቸውን ልብስ፣ ጌጣጌጥ በማልቀሻነት ይጠቀሙበታል፡፡ ወጣት ወንዶች ለእራት የታጠፈ ጋቢ ሲለብሱ፣ በእድሜ የገፉት ደግሞ ከላዩ ላይ ካፖርት ደርበዋል፣ ጭራ ይዘዋል፡፡[39]

በሌላ ዑደን ቄሶች ስርዓተ ቀብሩ እስኪፈጸም የሟችን የመጽሐፍ ስም ወይም የክርስትና ስም እየጠሩ ለብቻቸው በመሆን የፍታት ስነ-ስርዓት ያከናውናሉ፡፡ የተመረጡ ቄሶች አስከሬኑን ወስደው በስ ዙሪያ በመሆን እጣን እያጠኑ፣ መጽሐፍ እያነበቡ ቆይተው፣ ደመቅ ያለ ሽብሻቦ አደረጉ፣ በመጨረሻም ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ ለቅሶውና ፍታቱ ተጠናቆ በመጨረሻም በሃይማኖት አባቶች የሟች የህይወት ታሪክ ተነበበ፣ መንግስተ ሰማያት ያግባልን ተብሎ ተጸልዮ፣ ተመርቆ፣ ሀዘንተኞች እንዲጽናኑ ምክር ተሰጥቶ ስርዓተ ቀብሩ ካህን በሚቀበርበት ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምስራቅ በኩል ተፈጸመ፡፡

---

[39]ቄስ አዝመራ ደሲታ የተባሉ የ92 አመት እድሜ ባለጸጋ የነበሩ ሰው ባረፉበት ቀን በለቅሶ ስነ-ስርዓቱ ላይ በመገኘት የተደረገ ምልከታ ሲሆን ምልከታው የተካሄደው አርብ ቀን ሚያዝያ 11/2005 ዓ.ም በፍኖተ ሰላም ከተማ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው፡፡



ፎቶ ግራፍ 5 ቄሶች በእስከሬኑ ዙሪያ ሆነው የፍታት ስነ-ስርዓት ሲያካሂዱ የሚያሳይ ምስል

አልቃሹም ወደ ሀዘኑ ቤት በመሄድ እድርተኛው ያዘጋጀውን እህል ውሃ ተቃምሶ መንተኞችን "እግዚአብሄር ያጽናችሁ" እያለ ወደየቤቱ ይሄዳል፣ የቅርብ ዘመድ የሆነው ቢያንስ እስከ ሶስት ቀን ይሰነብታል፡፡ በተከታታይ ከሶስት እስከ ሰባት ቀናት ጠዋት ጠዋት ወደ ቀብሩ በመሄድ ይለቀሳል፡፡ በመሆኑም ከተቻለ እስከ ሰባት ካልሆነም እስከ ሰልስት ድረስ እየተመላለሱ አብሮነታቸውን ይገልጻሉ፡፡

ቄሶች ሟች አመት እስከሚሆነው ድረስ በተለያዩ ቀናት መታሰቢያቸውን ያደርጉላቸዋል፡፡ የሟች ቤተሰብም ድግስ በመደገስ ያከብርላቸዋል፡፡ ከመሪጌታ ስሜነህ አበበ ጋር ባደረግሁት ቃለ መጠይቅ ፍታትና ተዝካር በማህበረሰቡ እምነት ውስጥ ምን ቦታ እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሀያዋን በአጸደ ስጋ ለሙታን፣ ሙታን በአጸደ ነፍስ ሀያዋን ሊጸልዩ እንደሚገባ ታምናለች፡፡ በዚህ መሰረት ለሟች ከዕለት እስከ አመት መታሰቢያቸውን ታደርጋለች፡፡ ቤተ እስራኤላውያንም ለነ ሙሴ፣ ለነ አሮን፣ ለነ ያዕቆብ እስከ አርባ ቀን ድረስ መታሰቢያ አድርገውላቸዋል፡፡ ይህንን በመከተል ሙታንን በማህሌት፣ በጸሎት፣ በስርዓተ ቅዳሴ ስመ ዝክራቸውን መታሰቢያቸውን በማድረግ ትዘክራቸዋለች፡፡ "በአጸደ ነፍስ ከነአብረሃም፣ ከነ ያዕቆብ፣ ከነ ይስሃቅ አጠገብ አሳርፍልን"

እያሉ ይጸልያሉ፡፡ ይህም በቤተ ክርስቲያኒቱ በቅብብሎሽ የመጣ ትውፊት፣ ባህል፣ ቀኖና ነው[40]፡፡

ተዝካር ሟችን ምክንያት በማድረግ የሚከናወን ሃይማኖታዊ መሰረት ያላቸው ክብረ በዓላት የሚፈጸምባቸው የተመረጡ ቀኖች ናቸው፡፡ እነሱም ሳልስት፣ ሰባት፣ አስራ ሁለት፣ ሰላሳ፣ አርባ፣ ስልሳ፣ ሰማኒያ፣ መንፈቅ፣ ዓመት ሲሆኑ በእምነቱ የነበሩ ሊቃውንት ተስማምተው ያስቀመጧቸው እንደሆኑ ከቡድን ውይይቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአካባቢው ባህል መሰረት አርባ ትልቅ ግምት ይሰጠዋል፡፡ በመሆኑም ሀብት ያለው በሬ፣ ላም፣ የሌለው ደግሞ በግ አርዶ መታሰቢያውን ለሚያደርጉ ቄሶችና ለተጠራው ወዳጅ ዘመድ ያበላል፡፡ የእርድ ስነ-ስርዓቱም የሚከናወነው መቃብሩ ላይ ነው፡፡

ይህ የሚሆንበት ምክንያት የሟችን ነፍስ ለማስደሰት ሲባል እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በእነዚህ ቀናት ከሚደገሰው ድግስ የሟች ነፍስ ከጓደኞቿ ጋር መጥታ ትበላለች፣ ትጠጣለች ደስም ይላታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ለዚህም ሲባል ሰዎች ያለ የሌለ አቅማቸውን ተጠቅመው ተዝካር ይደግሳሉ፡፡ ለሟችም ለመጨረሻ ጊዜ ይለቀስለታል፡፡ ማህበረሰቡ ይህን በመፈጸም ለሟች ማድረግ ያልቻለውን በስሙ በመደገስ ከሚሰማው የጸጸት ስሜት ለመውጣት ይጠቀምበታል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በብዛት ተዝካር የሚደገሰው ከሞት በኋላ ነው፡፡ ነገር ግን የአካባቢው ማህበረሰብ ለተዝካር ካለው ትልቅ ቦታ የመነጨ ሰው በህይወት እያለ፣ በአለም እየኖረ የቁም ተዝካር ይከበርለታል፡፡ ከመርጌታ ስሜነህ አበበ እንደነገሩኝ የቁም ተዝካር የሚከበረው ሰዎች በአቅራቢያቸው ልጅና የሚተማመኑበት ወዳጅ ዘመድ ከሌላቸው ከሞት በኋላ የሚከበርላቸውን መሸኛ እና መታሰቢያ የሚያደርግላቸው ወገን ስለሌላቸው በቁመናቸው በአካባቢያቸው ለሚኖሩ መምህራንና ሊቃውንት በማማከር የሚፈጽሙት ነው፡፡ በመሆንም በህይወት እያሉ በክርስትና ስማቸው ይቀደስላቸዋል፣ ፍታት ይፈታላቸዋል፣ ይጸለይላቸዋል፣ በስማቸው ለነዳያን ይመጸወታል፣ ስመ ተዝካራቸውም ይወጣላቸዋል፡፡ በዚህም ሰዎች ዘላለማዊ በሆነው አለም ቤት እንደሰሩ ይቆጥሩታል፡፡ ሲሞቱም ወደዚያ እንደሚገቡ በማመን ከሚያሳስቧቸውና ከሚያስጨንቋቸው ጉዳዮች የሚያመልጡባቸው ክበራዎች ናቸው፡፡

---

[40] መርጌታ ስሜነህ ከነገሩኝ መረጃ የተወሰደ ነው፡፡

### 4.3.1 በለቅሶ ስነ-ስርዓት የሚከወኑ ቃል ግጥሞች

በለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በወየ ባዮች አማካኝነት የሚቀርቡት ግጥሞች እንደ ሟች ጾታ፣ እድሜ፣ ማህበራዊ ደረጃ የተለያዩ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት የሚተኮርባቸው የ92 አመት እድሜ ባለጸጋ የነበሩት ቄስ አዝመራ ደስታ የተባሉ ሰው የቀብር ስርዓት ላይ በመገኘት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ እኚህ ሰው በህይወት ሲኖሩ ለተቸገረ ሲሰጡ፣ ለተራበ ሲያበሉ፣ ለተጠማ ሲያጠጡ የኖሩ መሆናቸውን የሚያውቋቸው ሰዎች ነግረውኛል፤ የህይወት ታሪካቸው ሲነበብ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ የሚከወኑ ቃል ግጥሞችም ይህንን ሀሳብ የሚያጠነክሩ ናቸው፡፡ በእለቱ ከቀረቡ በርካታ ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ግጥም 1. የሰው ሁላ ቤቱ ሻጣው ይመዘዛል፣
እሬ ይህ ካህንስ ምሰሶው ይጓዛል፡፡

ይህ ቃል ግጥም የተዋቀረባቸው ቃሎችና ስንኞች ስለ ሟች ማንነት የሚያወሩ ናቸው፡፡ በዋናነት "ሻጣ" እና "ምሰሶ" የሚሉት ቃላት ትንሽነትና ትልቅነት የሚሉ ሀሳቦች ማደሪያ ሆነዋል፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ቤት ለመስራት (በተለይ ጎጆ ቤት) ምሰሶ ቤቱ እንዲቆም የሚያደርግ እንደ መሰረት ሊታይ የሚችል ቤቱ ቤት እንዲሆን ትልቁን ድርሻ የሚወስድ ነው፡፡ ሻጣ ማለት ደግሞ ምሰሶውን ከማራው እና ከግድግዳው ጋር በሚያያየዙ እንጨቶች መካከል እየተሳነ ማራው ሳር እንዲይዝ፣ ግድግዳው ደግሞ ምርግ እንዲይዝ የሚያደርጉ ቀጫጭን እንጨቶች ናቸው፡፡ ይህ አይነት ቤት ምሰሶው ከወደቀ ወይም ከተሰበረ ቤቱ ሙሉ በሙሉ የሚፈርስ ሲሆን ከበርካታ ሻጣዎች አንዱ ቢመዘዝ ግን ምንም አይሆንም፡፡ ይህ ማለት ግን ምንም የሚፈጥረው ጉዳት አይኖርም ለማለት አይደለም፡፡ የምሰሶውን ያህል ባይሆንም ለቤቱ መፍረስ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ይህንን መነሻ በማድረግ ማህበረሰቡ ለህልውናው ቁልፍ የሆኑ ትልልቅ ሰዎች፣ የቤተሰብ አባዎራዎች፣ ለማህበራቸው አስፈላጊ የሆኑ ሰዎችን በምሰሶ፣ እንዲሁም ሰው በመሆናቸውና በማህበሩ ውስጥ መኖራቸው ብቻ ጠቃሚ ተደርገው የሚታሰቡ ተራ የማህበሩ አባላትና ለመግለጽ ሻጣ የሚለውን ቃል በመጠቀም ሟች ከተራው ማህበረሰብ የተለዩ መሆናቸውን የገለጹበት ነው፡፡ ግጥሙ የሟችን ሰብእና መሰረት አድርጎ የቀረበ በመሆኑ ለእሳቸው ጾታ፣ ባህሪ፣ ማህበራዊ ደረጃ እንዲመጥን እና እንዲገልጽ አድርገው ያቀረቡት ነው፡፡ ነገር ግን

በሌላ አጋጣሚ የተለየ ይዘትና ቅርጽ ተሸሽሎ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ባጠቃላይ ይህ ቃል ግጥም ማህበረሰቡ የሟችን ማንነት በመግለጽ ሂደት ውስጥ ለካህን ያለውን ጥሩ አመለካከት አጽንቶ እንዲቀጥል የማድረግ አቅም አለው፡፡

ግጥም 2. አሰለፍ[41] ናት እንጅ ና ብላ ና ብላ፣

አፈር እንደ እንጀራ ሊበላ ነው ብላ፡፡

ማህበረሰቡ የሞትን ቀጣይነት ‹‹ጥሪ›› በሚባለው አብሮ የመብላት ዘዴ ይገልጸዋል፡፡ ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች እየተጠራሩ አብረው ይበላሉ፤ ይጠጣሉ፡፡ በማህበር፣ በአመት በዓል፣ በክርስትና፣ በሰርግ፣ በተዝካር፣ በቡና ምክንያት ቤተሰቡን፣ ዘመዱን፣ ወዳጁን ይጠራል፡፡ አንድ ሰው ደግሶ ሲጠራ መቅረት ነውር በመሆኑ ሁሉም ሰው ጥሪውን አክብሮ ይሄዳል፡፡ በአካባቢው ባህልና እምነት አንድ ሰው የሚሞተው የቀደሙ ዘመዶች ሲጠሩት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ጥሪው ግን አብሮ ለመብላትና ለመጠጣት ሳይሆን ዘላለማዊ የሆነው ሞት በመሆኑ ተቃራኒ ፍች ይኖረዋል፡፡

ማህበረሰቡ ስለ ሟች የሚያውቀው ነፍስና ስጋው እስከሚለዩባቸው ቅጽበት ድረስ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በእምነታቸው መሰረት በሚሰጡት ትረካ ካልሆነ በስተቀር በትክክል ምን ሊሆን እንደሚችል ማየትም ሆነ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ በመሆኑም አለም ላይ ሲኖር በሚያየው ሁኔት የሞትን ሂደት ይገልጻል፡፡ ማለትም ሰው በአለም ላይ የተትረፈረፈ ሀብት፣ የተደላደለ ኑሮ፣ ብዙ ልብስና ጌጥ ሊኖረው ቢችልም ከሞት በኋላ ግን የሁሉም ሰው ሀብቱ እና ንብረቱ አፈር ነው፡፡ ሞት ሁሉም ሰው ተራ በተራ እየተጠራ የሚሄድበት ሌላ አለም መሆኑን በህይወት ዘመናቸው አብሮ ለመብላት ከሚያደርጉት የጥሪ ክቡርነት ጋር ያዛምዱታል፡፡

ግጥም 3. እንደነ ጊዮርጊስ እንደነ ተክልዬ ታቦት መሆን ትቶ፣

አፈር ሊያለብሱት ነው ሰው ሁኖ ተገኝቶ፡፡

[41] አሰለፍ፡፡ ሙሉ ስማቸው አሰለፍ አዝመራ ሲሆን ከቂስ አዝመራ ደስታ ሞት ሁለት ወር በፊት የሞቱ ሴት ልጃቸው ናቸው፡፡ እናቸው በቅርብ ስለሞቱና ልጃቸውም ስለሆኑ ግጥሙ እንዳለ ቀረበ እንጅ ከዚህ በፊት የሞቱ የሟች ወገኖች እየተጠሩ እየተለቀሰላቸው ነው ስርዓቱ የሚቀጥለው፡፡

በዚህ ቃል ግጥም የሟችን ማንነት ለመግለጽ መልእክቱ የተዋቀረባቸው ማነጻጸሪያዎች በማህበረሰቡ እምነት ዘንድ ትላቅ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ ጊዮርጊስና ተክልዬ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮ ውስጥም የየራሳቸው አመታዊና ወርሃዊ ቀን ተመድቦላቸው ክብር፣ ውዳሴ እና ምስጋና ይደረግላቸዋል፡፡ ጊዮርጊስ ወር በገባ በሃያ ሶስተኛው ቀን፣ ተክለ ሃይማኖትም እንዲሁ ወር በገባ በሃያ አራተኛው ቀን በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ይከበራሉ፡፡ ለምን በአማኒያኑ ዘንድ ትልቅ ቦታ ተሰጣቸው የሚለውን በመርመር በግጥሙ ውስጥ የመጡበትን ፋይዳ መረዳት ይቻላል፡፡

የጊዮርጊስና የተክልዬን አመጣጥ ስንመለከት ሁለቱም እንደማንኛውም ሰው አለም ላይ የኖሩ፣ እንደሰው የሚበሉ፣ የሚጠጡ፣ የሚሰሩ ነበሩ፡፡ "ጊዮርጊስ" ለሃይማኖታቸው ሲሉ የተወገሩ፣ ተጋደሎ የፈጸሙ፣ መራራ ሞትን የሞቱ፣ ሲሆን ከፈጣሪያቸው በተሰጣቸው ጸጋ አማካኝነት ብዙ ገድላትን ሲፈጽሙ፣ በስማቸው ብዙ ህሙማንን የፈወሱ እየፈወሱም ያሉ ናቸው፡፡ በመጨረሻም የሰማዕትን ሀይልና ክብር አገኙ፡፡ "ተክልዬ" ደግሞ ለሃይማኖታቸው ህጋጋት ተገዥ፣ አገልጋይ ስለነበሩ ጻድቅ የመሆን ክብር አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም ለሁለቱም ስማቸውን የጠራ፣ በስማቸው የዘከረ፣ በስማቸው የተጠመቀ ድህነት እንዲያገኝ ቃል ተገብቶላቸዋል፡፡ ታቦት ተቀርጾላቸውም በየወሩና በየአመቱ ይከበራሉ፤ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡[42]

ከዚህ ታሪክ በመነሳት ጊዮርጊስና ተክልዬ በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ለምን እንደማነጻጸሪያ ሆነው ቀረቡ የሚለውን ስንፈትሽ የሟች ማንነት እንዴት እንደተገለጸ መረዳት እንችላለን፡፡ ሟች ለሃይማኖቱ ታማኝ አገልጋይ እንደነበረ ያሳያል፡፡ በመጀመሪያ ለሃይማኖቱ በመቆሙ፣ እንዲሁም ሰው በመሆኑ ከጊዮርጊስና ከተክልዬ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሆኖም እንደነሱ ታቦት አልሆንም እንጅ ለሃይማኖቱ ከነሱ ያላነሰ ሚና የተጫወተ ስለሆነ ታቦት ሊቀረጽለት ይገባል የሚል ሀሳብ አለው፡፡ ማህበረሰቡ የሰውየውን ማንነት በማነጻጸር ሲገልጽ የመረጣቸው ሚካኤልን ወይም ገብርኤልን አይደለም፤ ምክንያቱም እነሱ ሲጀመርም ሰው አይደሉም፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ ግጥሞችን የሚያዋቅራቸው ተጠየቃዊና

---

[42] ቄስ ሚናስ ሁሩይ ምርጫ በራብር ቀበሌ የሚኖሩ ቄስና የአገር ሽማግሌ ናቸው፡፡ በቡድን ውይይቱ ከተሳተፉት ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡

ምክንያታዊ አድርጎ ነው፡፡ ይህም ሟች ምን ያህል ጥሩ ሰው እንደነበሩ ከማሳወቅ በተጨማሪ በታዳሚው ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያግዛል፡፡

ግጥም 4. እስኪ እኛ ዝም በሉ ይጮሃል በአፋፉ፣

እነሆ ልማደኞች ዛሬም ተዘረፉ፡፡

የዚህ ቃል ግጥም ሁለተኛ ስንኝ ሀሳብ በሁለት በኩል ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ሞት ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን አብሮነት የሚያመለክት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሞትን ጨካኝነት ያሳያል፡፡ ሞት በፍኖተሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በአለምአቀፍ ደረጃም ነበረ፣ ያለ እና የሚኖር አንድ የህይወት ዑደት ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ በሟች ቤተሰቦች በመወከል ይገልጹታል፡፡ ግጥሙ በቀረበበት አውድ የሟች ቤተሰቦች ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ሞትን ያስተናገዱ መሆናቸውን ለመግለጽ ቢሆንም ለማንኛውም ማህበረሰብ ክፍል የሚባል ቃል ግጥም ነው፡፡ ሞት የተወሰኑ ሰዎች የሚሞቱት ሳይሆን ለሁሉም የሚደርስ፣ ሁሉም የሚታደለው ጽዋ ነው፡፡

በዚህ ስንኝ ውስጥ ያለው ፡፡ተዘረፉ፡፡ የሚለው ቃል የያዘውን ጽንሰ ሀሳብ ለብቻው በመመርመር ማህበረሰቡ ለሞት ያለውን አመለካከት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ማህበረሰቡ ሞትን የሚገነዘበው ዘራፊን በሚያይበት አይን ነው፡፡ ዘራፊ ማለት አንድ ሰው በሀይልና በጉልበት ተገዶ ያለውን ወይም የያዘውን ለሌላ አካል አሳልፎ የሚሰጥበት ማለት ነው፡፡ ሞትም አንዴ ከመጣ ማንም አያስቀረውም፡፡ ለዚህም ነው ሁሉም ሰው እናቱን፣ አባቱን፣ እህቱን፣ ወንድሙን እያጣ ችሎ የሚኖረው፡፡ ማህበረሰቡም አልቅሶ ከመቅበርና በሀዘን እያረሩ ከመኖር ያለፈ ምንም ዓይነት መፍትሄ የለውም፡፡ ይህንን የሞትን ድፍረትና ጥካት በትርብ ከሚያውቀው ድርጊት ጋር እያነጻጸረ ስሜቱንን ሀሳቡን ይገልጻል፡፡

ግጥም 5. በሮቹ ጥቋቁር ገበሬው ደንቆሮ፣

አይናገርም ወይ ዘር አለቀ ብሎ፡፡

ይህ ቃል ግጥም የማህበረሰቡ በሞት ላይ ያለውን ጥላቻ፣ ምሬትና ብሶት ያዘለ ነው፡፡ ይህንንም መልእክት በግጥሙ እንዴት እንደቀረበ በመፈተሽ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በብዛት የአካባቢው ማህበረሰብ ኑሮ የተመሰረተው በግብርና ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መልእክቱም የተዋቀረው በዚህ ማሳያነት ነው፡፡ አንድ ገበሬ በሮቹ ጥቋቁር ከሆኑ ከርቀት ለመታየት

ያስቸግራሉ፣ ገበሬውም ደንቆሮ ከሆነ ዘር እንዳለቀበት እንኳን መናገር አይችልም፡፡ ሞት ለማህበረሰቡ በጥቂቱ በሬዎች እንደሚያርስ ደንቆሮ ገበሬ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ገበሬው ዘር እልቆበት ሁሉ ማረሱን ግን እንዳላቆመ ግጥሙ ያስረዳል፡፡ ሞትም በማህበረሰቡ ኑሮ ውስጥ የነበረ፣ ያለ እና የሚኖር መሆኑን ያስረዳል፡፡ እስካሁን ቤተሰባችንን፣ ወገናችንን ስትነጥል ቆየህ "እስኪ ይብቃህ" የሚል ተማጽኖ የያዘ ቃል ግጥም ነው፡፡

## 4.3.2 በለቅሶና በተዝካር ስነ-ስርዓት ማሳረጊያ የሚቀርቡ ምርቃቶች

ማህበረሰቡ ለሞት ያለውን አመለካከት የቀብር ስርዓቱ ሊፈጸም አካባቢና ተዝካር በሚደገስባቸው ቀናት ሁሉ በምርቃቱ አማካኝነት ይገልጻል፡፡ በምርቃት ማስተላለፍ የፈለጉትን መልእክትም ምሳሌያዊ ንግግሮች በመጠቀም እያዋሃደ ያቀርበዋል፡፡ ማህበረሰቡ በምርቃቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች እንደ ሀሳብ መግለጫና መልእክት ማስኬጃ ዘዴ ይጠቀምባቸዋል፡፡ በለቅሶ እና ተዝካር የሚቀርቡ ምርቃቶች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ግን የሚከተሉት ናቸው፡፡

ምርቃት 1. **ሞት ለፍ ድንጋይ ገርፎ፣**

ማህበረሰቡ በዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ውስጥ የቀረቡት ሁለት ሀሳቦች ማለትም ሞትና ድንጋይ ተመሳሳይ ይዘት እዲኖራቸው ተደርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ ይህም ማለት ድንጋይን ገርፎ ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ሁሉ በሞት ላይም ሰው ክፉ ስላወራ ሞት ሰውን ከመግደል ወደኋላ እንደማይል ለማመልከት የተጠቀመበት አቀራረብ ነው፡፡ መልእክቱም ማህበረሰቡ ሞት ለሁሉም የማይቀርና ግዴታ መሆኑን አምኖ እንዲቀበል ያደርጋል፡፡

ምርቃት 2. **የሞት በደለኛ አይያዝ በዳኛ፣**

ሰው በህይወት ሲኖር በተለያዩ ምክንያቶች ሌላ ሰው በድሎ ወይም ተበድሎ ለሚመለከተው አካል ጉዳዩን በማቅረብ ሊፈረድለት ወይም ሊፈረድበት ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ሰው እኩል በሆነበት አለም አንዱ በዳይ ሌላው ተበዳይ የሚሆንበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ምክንያት አለማችን በቀውስ የተሞላች እንዳትሆን ሁሉም ሰው በህግ ስር ይተዳደራል፣ ይኖራል፡፡ ይህ ህግ የሚያገለግለው ከልደት እስከ ሞት ባለው የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ነው፡፡

ሞት ግን መሞት የሌለባቸውን ሰዎች መሞት በሌለባቸው ጊዜ ሲገድል አልቅሶ ከመሸኘት ውጭ ለማገም እቤት ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ሞት ለሁሉም ሰው የማይቀር ተፈጥሯዊ ሁነት በመሆኑ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ደግሞ አምኖ ከመቀበል ውጭ አማራጭ ባለመኖሩ ነው፡፡ በመሆኑም የሞትን ሀያልነት ለማስገንዘብ ‹‹አይያዝ በዳኛ›› የሚለውን ሀረግ በማሳያነት የተጠቀመበት ስልት ነው፡፡

ምርቃት 3. **ሞት አይለመድ፣ ጎሽ አይጠመድ፣ ሙርቃ አይታጨድ፣**

ከላይ በቀረቡት ቃል ግጥሞችና ምርቃኖች የሞት ሁነትን ሰው አምኖ ከመቀበል ውጪ ምንም አማራጭ የሌለው መሆኑን የሚያሳዩ እንደሆኑ ጠቁሚ ነበር፡፡ በዚህ ምርቃን ደግሞ ምንንም እንኳን ሞት የነበረ፣ ያለና የሚኖር የህይወት ዑደት ቢሆን በተከሰተ ጊዜ ግን የሚፈጠረው ስሜት ፍጹም አስደንጋጭና አዲስ ነው፡፡ ፈጽሞ ከዚህ ስሜት መውጣት እንደማይቻል ለማመልከት ከሌሎች የማይሆኑ ድርጊቶችን በሚያመለክቱ ሀረጋት ጋር በማስባጠር ቀርቧል፡፡ እነሱም ‹‹ጎሽ አይጠመድ›› እና ‹‹ሙርቃ አይታጨድ›› የሚሉት ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ጎሽ በአካል በሬ ቢመስልም ተጠምዶ እንደማይታረስ፣ እህልም ፍሬ አፍርቶ ካልደረቀ እንደማይታጨድ ሁሉ ሞትም በተከሰተ ቁጥር አዲስ ነው፤ አይለመድም፡፡ ምክንያቱም ከቤተሰቡ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ይኖር፣ ይጫወት፣ ይሰራ የነበረ ሰው ሞቶ በድን ሲሆን ያስደነግጣል፣ ያሳዝናል፣ ያስለቅሳል፡፡ ስለዚህ ይህ ምርቃን ሞት በባህሪው ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ እየኖረ የማይለመድ የህይወት ዑደት መሆኑን ያሳያል፡፡

ምርቃት 4. **ብልህ ሲሞት ልቡን ንጉስ ሲሞት ግንቡን ውረስ፣**

ሞት ለሁሉም ፍጥረታት የማይቀር ሁነት እንደመሆኑ መጠን ሰው በህይወት ዘመኑ ሰርቶ የሚያልፋቸውን ቁም ነገሮች በመውረስ ቀሪው ማህበረሰብ እንዳች ጠቀሜታ እንዲያገኝበት ይፈለጋል፡፡ ስለሆነም ሰው ሟች ለምን ሞተ ሳይሆን ከሟች ህይወት ምን መማር እንዳለበት በመረዳት ‹‹ብልህ ሲሞት ልቡን ንጉስ ሲሞት ግንቡን ውረስ›› የሚል ምርቃት ይመርቃል፡፡

ምክንያቱም ለምን ሞተ በሚለው ዙሪያ ማሰብ ከንቱ ድካም ነው፤ የግድ መሞት ስላለበት ማለት ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ ማህበረሰቡ ከሟች ህይወት ትምህርት ወስዶ ቀሪ ኑሮውን ማስተካከል እንደሚኖርበት ትኩረት የሚደረግበት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ንጉስ ሲሞት ቤተ መንግስቱን፣ ንግስናውን ወርሶ ንጉስ ለመሆን መሞከር እንደሚገባ ሁሉ ማህበረሰቡ

አንድ ሰው ህይወቱ ሲያልፍ የሚከተለውን የኑሮ መመሪያ፣ አስተሳሰብ፣ የስኬት ምንጭ በመረዳት ወደራስ በማምጣትና በመተርጎም መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ለማመልከት የሚጠቀምበት ሀሳብ ነው፡፡

ምርቃት 5. ሲሞት ሲተካ ሲፈጭ ሲቦካ፣

ማህበረሰቡ አለም ጸንታ የኖረችባቸውን የልደትንና ሞትን ዞሮ ገጠምነት ለማመልከትና ሞት ገድ እንደሆነ ለመግለጽ በምርቃኖቻቸው ውስጥ ‹‹ሲሞት ሲተካ ሲፈጭ ሲቦካ›› የሚል ምሳሌያዊ ንግግር ይጠቀማሉ፡፡ አለማችን ሁልጊዜም ልደትና ሞት ይስተናገዱባታል፡፡ አሁን ያለችበት ደረጃ ላይ የደረሰችውም በእነዚህ ሁለት የሰው ልጅ የህይወት ዘመን ውደቶች የማያቋርጥ ሂደት አማካይነት ነው፡፡ ይህንንም ለማሳየት ሌላ ሂደት ያለው ነገር በማንጸሪያነት ይጠቀማሉ፡፡ ማለትም ሰዎች በህይወት እስካሉ ድረስ በህይወት ለመኖር ያላቸውን ያስፈጫሉ፣ ያቦካሉ፣ አብስለውም ይበላሉ፡፡ እንዲሁም የሰው ልጅ ወደ መኖርና ወደ አለመኖር የሚሸጋገረው በልደትና በሞት አማካኝነት መሆኑን የገለጹበት ምርቃን ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ወደደም ጠላም በመወለድ ወደዚች አለም ሲመጣ በሞት ደግሞ ይሰናበታል፡፡ በመሆኑም ልደትና ሞት አንድ ሰው የግድ የሚያልፍባቸው ከመሆናቸውም ባሻገር በዘመኑ አንድ ጊዜ ብቻ የሚከሰቱ የህይወት ውደቶች ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ቃል ግጥሞችና ምርቃቶች እንደ ሟች ጾታ፣ እድሜ፣ ማህበራዊ ደረጃ የተለያየ አቀራረብ አላቸው፡፡ ባጠቃላይ በለቅሶ እና በተዝካር ጊዜ የሚቀርቡ ምርቃኖች ይዘት የሞትን አመጣጥ፣ የሞትን አስከፊነት፣ ለሁሉም የሚደርስ ጽዋ መሆኑን፣ የሞትን ሀያልነት፣ የሞትን አዲስነትና አስደንጋጭነት፣ የሞትንና የልደትን ዞሮ ገጠምነት፣ ህዝቡ ከሟች ትምህርት መውሰድ እንዳለበት የሚገልጹ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

## 4.4 የህይወት ዘመን ውደት ሽግግሮች ክብረ በዓል መዋቅር

ቫን ገነፕ እንደገለጹት የህይወት ዘመን ውደት ሽግግሮች ከበራ መነጠል፣ ሽግግር እና አዲስ ማንነት ማግኘት የሚባሉ ደረጃዎችን ያልፋል፡፡ የሪቹዋሉ መፈጸም ዋና ተግባርም የማህበረሰቡ አባል የሆነውን ግለሰብ ወይም ቡድን ማንነት፣ ሚና፣ ማህበራዊ ደረጃ በመለወጥ ወደ ሌላ አዲስ ማህበራዊ ደረጃ ማሸጋገር ነው፡፡

በህይወት ዘመን ሽግግር ለማድረግ መጀመሪያ የሚከሰት መነጠል ነው፡፡ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ በአካል ወይም በመንፈስ ከራሱ ማንነት ወይም ከማህበረሰቡ መውጣትን የሚያመለክት እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ተጠቁሟል፡፡ እንዲሁም ከመነጠል ቀጥሎ የሚመጣው ደረጃ ሽግግር ይባላል፡፡ ሽግግር በፊት የነበረው ማንነት ቀርቶ ሌላ አዲስ ማንነት ለማግኘት የሚደረግ ዝግጅት ነው፡፡

ከሽግግር ቀጥሎ የሚመጣው የተነጠሉትና የተገለሉት ሰዎች ሌላ አዲስ ማንነት ይዘው ወደ ማህበረሰቡ የሚመለሱበት ነው፡፡ ዋናው ክብረ በዓል የሚፈጸመው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ነው፡፡ በክብረ በዓሉ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ አዲስ ስያሜ፣ አዲስ ማንነት፣ አዲስ አለባበስና አዲስ ማህበራዊ ሚና ይዞ ከማህበረሰቡ ጋር ይቀላቀላል፡፡

በፍኖተ ሰላም አካባቢ ልደትን፣ ሰርግንና ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸሙ ከበራዎች መነጠል፣ ሽግግርና አዲስ ማንነት ማግኘት በተሰኙ የሪቹዋል ደረጃዎች የሚያልፉ ናቸው፡፡ የልደት ከበራ የሚፈጸመው አንድ ህጻን ከእናቱ ማህጸን መውጣትን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ ከበራውን ለመፈጸም የሚደረገውን መነጠል ከወላዷ እና ከሚወለደው ህጻን አንጻር መመልከት ይቻላል፡፡ ህጻኑ በእናት ማህጸን ውስጥ የሚቆይባቸው ጊዜያት ወላዷ መነጠል ደረጃ ላይ የምትሆንበት ጊዜ ነው፡፡ እናቶች በእርግዝና ጊዜያቸው የነበራቸው ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ ብሎም ይጠሩበት የነበረው ስም ይቀርና ሌላ ምድብ ውስጥ ይገባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የሚያስቡት እናት ስለመሆን፣ ልጅ ስለማሳደግና ሌሎች እናትነትን ተከትለው ስለሚመጡ ሁኔታዎች ነው፡፡

የነፍስ ጡር ሴቶች አለባበስ ለእርግዝናቸው የሚመመች፣ እርግዝናቸውን የሚያሳውቅ ይሆናል፡፡ የሚመገቡት ምግብና የአመጋገብ ስልታቸው በፊት ከነበረው ይለያል፡፡ እናቶች በእርግዝና ጊዜያቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የተሰጣቸው ሃላፊነት ካለ እንዲለቁ ወይም በሌላ ሰው እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ይህም የነበሩበትን ማህበራዊ ደረጃ እንደለቀቁ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእርግዝና እያሉ ‹‹ነፍስ ጡር›› በሚል የወል ስም ይታወቃሉ፡፡ ነፍስ ጡር የሚለው ስያሜ ከመጠሪያ ስማቸው በተጨማሪ እንደመገለጫና መታወቂያ በመሆን ያገለግላል፡፡ የሴቶች የእርግዝና ጊዜ የነበራቸውን ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ የሚለቁበት ጊዜ በመሆኑ የመነጠል ደረጃ ላይ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በልደት ከበራ ከእርግዝና ቀጥሎ በወሊድ ቀን የሚከሰተው ምጥ ነው፡፡ ምጥ እናቶች ልጃቸውን ለመገላገል ወይም ህጻኑ ከእናቱ ማህጸን ለመውጣት የሚያደርጉትን መፍጨርጨር የሚያመለክት ሀሳብ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ወላዷ በእርግዝና እና በመውለድ መካከል ላይ ስለሆነች ህመም፣ ስቃይ እና ግራ መጋባት ይታይባታል፡፡ የምጥ ጊዜ እናት የሚያደርገ የሚያዘጋጅ ትጽበት በመሆኑ የሽግግር ጊዜ መውሰድ ይቻላል፡፡

በልደት ጊዜ ዋናው ከበራ የሚፈጸመው ወላዷ ልጇን ከተገላገለች በኋላ ነው፡፡ ነፍሰ ጡር የነበረችው የልጅ እናት፣ አንድ የነበረችው ሁለት ስትሆን የማሪያም መሽኛ ከሚገነፋው ገንፎ ጀምሮ ለአራሷና ለህጻኑ የሚደረጉላቸው እንክብካቤዎች፣ የሚበረከቱላቸው ስጦታዎች የከበራው ክፍል ነው፡፡ ወላዷ በተገላገለች በአስረኛው ቀን በሚፈጸምላት የጥምቀት ስርዓት ወደ ቀጣዩ ደረጃ ትሸጋገራለች፡፡ በዚህ ጊዜ ሴቶች አዲስ አለባበስ፣ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ይዘው ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ፣ የእናትነት ሚና ይይዛሉ፡፡ ህጻኑም በተለያዩ ቀናት በሚፈጸምለት የግርዘት እና የክርስትና ስነ-ስርዓቶች በማኅበረሰቡ ባህልና እምነት መሰረት ወደ ትድስና ከመሸጋገሩም በተጨማሪ ሌላ አዲስ ማንነት ይይዛል፣ ክርስቲያን ይሆናል፡፡

መነጠል፣ ሽግግርና አዲስ ማንነት ማግኘት በሰርግ ከበራ ላይ ይከሰታሉ፡፡ ሙሽሮች ለመጋባት ከተጫጩበት ጊዜ እስከ ሰርጉ ቀን ያለውን ጊዜ የመነጠል ደረጃ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም እዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች በፊት የነበራቸውን ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ይተዋሉ፡፡ ባለትዳር ለመሆን ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ራሳቸውን አስውበውና አለባበሳቸውን ቀይረው ይቆያሉ፡፡ በፊት የነበራቸውን ማንነት ቀስ በቀስ ይተዋሉ፡፡ በመሆኑም ግለሰቦች ከማህበረሰቡና ከቤተሰባቸው ባይነጠሉም ከነበራቸው ማንነትና አስተሳሰብ ስለሚወጡ የመነጠል ደረጃ ላይ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሰርግ ከበራ ደረጃዎች ውስጥ ከመነጠል ቀጥሎ የሚመጣው ሽግግር ሲሆን የሰርግ ስነ ስርዓት የሚከናወንባቸው ቀናትና የጫጉላ ቆይታቸው የሽግግር ደረጃ ላይ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ተግባራት ያከናውናሉ፡፡ በጫጉላ ቤት ቆይታቸው የተለየ ስብእና ይዘው ይቆያሉ፣ አንዳንዶች ማንም ሰው እንዳያያቸው ይሸፈናሉ፣ እንቅስቃሴያቸው የተገደበ ይሆናል፡፡ የሚከናወኑበት ምክንያትም የሙሽሮችን ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ወደሌላ አዲስ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ለማሸጋገር ሲባል ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ሙሽሮች ባለትዳር ለመሆን የሚዘጋጁበት ነው፡፡ ከነበራቸውና ወደፊት ከሚደርሱበት ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ውጭ ናቸው፡፡

በሰርግ ከበራ የመጨረሻው ደረጃ አዲስ ማንነት ማግኘት የሚባለው ሲሆን ሙሽሮች ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ የሚደርሱበት ነው፡፡ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ባህላዊ የሰርግ ስነ-ስርዓት ሙሽሮች ጫጉላ ቤት የሚቆዩት ከአምስት ወይም ከአስር ተከታታይ ቀናት በኋላ ለሚከበረው የመልስ ስነ-ስርዓት አማካኝነት የሚጠበቀውን አዲስ ማንነት ያገኛሉ፡፡ የሰርጉ ስነ-ስርዓቱ የሚፈጸመው እና የሙሽሮች ባለትዳርነት የሚረጋገጠው በዚሁ እለት ነው፡ የግላዊ ስነ-ስርዓት ሙሽሮች ተገልጠው ተመርቀው አዲስ ስያሜ ወጥቶላቸው ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላሉ፡፡

ከሞና ሞና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ውስጥ ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚከናወነው የለቅሶ ሪቹዋል እንደሌሎች ሁሉ ሶስቱን የሽግግር ደረጃዎች ያልፋል፡፡ ማህበረሰቡ ከሞት በፊት የሚያከናውናቸው ተግባራት እንደ ቁርባን፣ ምንኩስና፣ የቁም ተዝካር ያሉት ከንዋኔዎች ሰዎች የመነጠል ደረጃ ላይ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ እነዚህን ደረጃዎች ሲሸጋገሩ ከነበራቸው ማህበራዊ ደረጃና ማንነት እየወጡ ይሄዳሉ፡፡ ከተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ይገለላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የቁም ተዝካር የወጣላቸው ሰዎች ራሳቸውን ከማህበር፣ ከእድር፣ ከእቁብ ያገላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ከማህበረሰቡ ወይም ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው አለም በቃኝ ብለው ወደ ገዳማት፣ አድባራት ይሰደዳሉ፡፡ እነዚህ ተግባሮቻቸው የመነጠል ደረጃ ላይ እንዳሉ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በለቅሶ ስርዓት ከዋኔ ደረጃ ሽግግር ሰዎች ከኖሩባት አለም ወደ ሌላው አለም የሚሸጋገሩበት፣ ህይወት የሚያበቃበት፣ እስትንፋስ የሚያቆምበትን ቅጽበት የሚያመለክት ነው፡፡ በሞት ጊዜ የሽግግር ደረጃ ቅጽበታዊ ስለሆን ለመግለጽ ያስቸግራል፡፡

የመጨረሻው የለቅሶ ስርዓት ከዋኔ ሟች ህይወቱ ካለፈ በኋላ የሚቀጥል ነው፡፡ የአገናነዝ ስርዓቱ፣ የለቅሶ ስርዓቱ፣ በወዬ ባዮች የሚከወኑት ግጥሞች ይዘት፣ የፍታት ስርዓት፣ የቀብር ቦታው መለያየት፣ ተዝካር ላይ የሚቀርበው ድግስ መለያየት ሁሉ ሟች የነበረውንና ከሞተም በኋላ ያለውን ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ አመላካቾች አዲስ ማንነት ላይ መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡

በሞት ስርዓተ ክዋኔ ሟች አዲስ ማንነት የሚያገኘው ይህም ሲባል እንደ ልደትና ሰርግ ከበራ ግለሰቡ አዲስ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ይዞ ወደ ማህበሩ አይቀላቀልም፡፡ ስርዓተ ክዋኔው የሚፈጸምለትም ነፍሱ ሌላ ዘላለማዊ አለም ውስጥ ህያው ሆና ትኖራለች ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ባጠቃላይ በፍኖተ ሰላም አካባቢ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮች ክብረ በዓልና አከባበር መነጠል፣ መሸጋገርና አዲስ ማንነት ማግኘት የሚባሉትን የሽግግር ደረጃዎች ያልፋል፡፡ ስርዓተ ክዋኔዎች የሚፈጸሙትም ሶስቱን ደረጃዎች በሂደት ካለፉ በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግሮች ማለትም በልደት፣ በሰርግና በለቅሶ ከበራዎች ውስጥ እነዚህን የሽግግር ደረጃዎችን ተከትለው እንደሚከናወኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአካባቢው የሚፈጸሙ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን ክብረ በዓል ባህሪ እንጻር መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡ እነሱም መዋቅራዊነት፣ ቅደም ተከተላዊነት፣ ተደጋጋሚነት፣ ታዳሚ፣ ውጤት፣ ቅዱሳዊነት የሚባሉ ባህሪዎች ይታዩባቸዋል፡፡

በፍኖተ ሰላም አካባቢ የልደት፣ ሰርግና ለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች ከላይ የተዘረዘሩት ባህሪያት ይታዩባቸዋል፡፡ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ ማህበረሰቡ ባዋቀራቸው ማህበራዊ ህጎችና ደንቦች አማካይነት ይመራል፣ ይቀርባል፡፡ እንዲሁም የዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ክዋኔ የአቀራረብ ቅደም ተከተል አላቸው፡፡

ክዋኔያቸው ማህበረሰቡ በሚያውቀውና በሚከተለው ቅደምተከተል አማካይነት ይካሄዳል፡፡ ለምሳሌ፡፡ የልደት ስርዓተ ክዋኔ ከወላዷ እርግዝና ጀምሮ ህጻኑ ክርስትና እስከሚነሳ ድረስ ክዋኔዎች የሚያልፉባቸው መዋቅሮችና ቅደምተከተሎች አሉ፡፡ እንዲሁም የሰርግ ከበራ ወላጆች ልጆቻቸውን ለመዳር ካሰቡበት ጊዜ ጀምሮ ባለትዳር ሆነው ወደ ማህበረሰቡ እስከሚቀላቀሉ ድረስ የሚከናወኑ ጉዳዮች የሚያልፉባቸው ቅደምተከተሎች ከመኖራቸውም ባሻገር ማህበረሰቡ የሚከተላቸውና የሚመራባቸው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ሁሉም ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሲከበሩ የሚከናወኑ ድርጊቶች ተደጋጋሚነት ይስተዋልባቸዋል፡፡ ማለትም አንድ እናት ምጥ ስትያዝ የሚከናወኑ ተግባራት ሁሉም እናቶች ሲወልዱ የሚከናወኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም በእናቶች የህይወት ዘመን አንዴ ብቻ የሚከናወኑ ሳይሆን ልጆቻቸውን ወልደው እስከሚጨርሱ ድረስ ተደጋግመው የሚቀጥሉ ናቸው፡፡ በባህላዊ የሰርግ ስነ-ስርዓት የሚከናወኑ ጉዳዮችም

ተደጋጋሚነት ይስተዋልባቸዋል፡፡ እንዲሁም በለቅሶ ስነ-ስርዓት የሚከናወኑ ጉዳዮች በማህበረሰቡ ባህል ውስጥ በድግግሞሽ የመጡ እንጅ በአንድ ጊዜ የተፈጠረ ዱብእዳ የሆኑ ድርጊቶ አይች የለም፡፡

የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ክዋኔዎች ግለሰብን የሚመለከቱ ቢሆኑም የሚከናወኑት ግን በቡድን ወይም በጋራ ነው፡፡ ሪቺዋሎች ሲፈጸሙ የኔ ብሎ የሚከተላቸው፣ የሚሳተፍባቸው፣ የሚያምንባቸው ከማህበረሰቡ ውስጥ የወጣ ታዳሚ (ተሳታፊ) አላቸው፡፡ በፍኖተ ሰላም አካባቢ የሚከናወኑ ዋና ዋና የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ሪቺዋል የሚፈጸመው በጋራ መሆኑ የማህበረሰቡን ማህበራዊነት ያሳያል፡፡

በአካባቢው የሚፈጸሙ የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች ግላዊም ሆነ ማህበራዊ ውጤት ያስገኛሉ፡፡ የልደት ክዋኔ ውጤት ልጅ ማግኘት (አይንን በአይን ማየት) ሲሆን የሰርግ ክዋኔ ውጤት ደግሞ ግለሰቦችን ባለትዳር ማድረግ እንዲሁም የለቅሶ ክዋኔ ሟችን ገነት ማስገባት፣ የሟችን ቤተሰብ ማህበራዊ ደረጃ ማሳደግ ናቸው፡፡ በመሆኑም ያለምክንያትና ውጤት የሚከናወኑ ሪቺዋሎች የሉም የሚል ማጠቃለያ መስጠት ይቻላል፡፡

የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎችን የሚመለከቱ ስርዓተ ክዋኔዎች አንድን ሰው ወደ ጥሩ ነገር (ቅዱስ) የሚሸጋግሩ ናቸው፡፡ አንድ እናት ምጥ ስትያዝ የሚከናወኑ ተግባራት በሰላም እንድትገላገል አስበው መሆኑ፣ ከወለደችም በኋላ መታጠቧ፣ መጠመቋ፣ ህጻኑ መገረዙ፣ ክርስትና፣ ሰርግ፣ ቁረባን፣ ምንኩስና፣ ተዝካር ሁሉ ግለሰቡን ከነበረበት ደረጃ ወደ ተሻለ (ቅዱስ) ግላዊም ሆነ ማህበራዊ ደረጃ የሚያሸጋግሩ ናቸው፡፡ ባጠቃላይ ፍኖተ ሰላም አካባቢ የልደት፣ የሰርግና የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔዎች የመዋቅራዊነት፣ የተደጋጋሚነት፣ የትደምተከተላዊነት፣ የታዳሚ፣ የውጤትና የቅዱሳዊነት ባህሪ ታይባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5 መደምደሚያ

ይህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ የምርምሩ ግኝቶችና ማብራሪያዎች እንዲሁም የምርምር ግኝቶች ጠቀሜታዎች ላይ ያተኩራል፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በፍኖተ ሰላም አካባቢ ማህበረሰብ ላይ ያተኮረ ሲሆን የተተኮረበት ጉዳይ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምንነትና አከባበር ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ሲጠና የአካባቢው ማህበረሰብ ለህይወት ሽግግር ደረጃዎች ያለውን አመለካከት በስነ-ቃሉ አማካንንት እንዴት እንደሚገልጽ ማወቅ፣ የህይወት ዘመን ሽግግር ደረጃዎች ከበራ ስርዓተ አፈጻጸም እንዴት እንደሆን መረዳት፣ ጉዳዩን በጥናት ደረጃ ማስተዋወቅንና የተፈጠረውን ክፍተት ማጥበብ የሚሉ የምርምር ፕሮብሌሞች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

እነዚህን ፕሮብሌሞች ለመረዳት ማህበረሰቡ የህይወት ዘመን ሽግግር ደረጃዎችን ከበራ ምክንያት በማድረግ ምን መልእክት ያስተላልፋሉ? እና የአከባበር ስነ-ስርዓቱ ሂደት ምን ይመስላል? የሚሉ ዋና ዋና የምርምር ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ እነዚህ የምርምር ጥያቄዎች የህይወት ሽግግር ደረጃዎች የሚገልጹ ስነ-ቃሎችን በሚከወኑበት አውድ ውስይ በመረዳት በመተንተንና የማህበረሰቡን አመለካከት እና እውቀት በመጠኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የማህበረሰቡን አመለካከት እና እውቀት ሙሉ በሙሉ መረዳት ያላስቻሉ በርካታ ችግሮች ተከስተው ነበር፡፡ ከችግሮች መካከል ዋናው ምርምሩ ትኩረት ካደረገባቸው ጉዳዮች ውስጥ ልደትና ሞት በታቀደው ጊዜ የሚገኙ ሁነቶች አለመሆናቸው፣ ሴት ከመሆኔ ጋር ተያይዞ ለመመልከት ያልቻልኳቸው ጉዳዮች መከሰታቸው፣ ብዙዎች ክብረ በዓላት የሚከወኑት በተመሳሳይ ጊዜ እና በቡድን መሆናቸው፣ እንዲሁም የአከባበር ስርዓታቸው ረዥም ጊዜ የሚወስድ መሆን መሆኑ ልደትን፣ ጋብቻን እና ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚከናወኑ ክበራዎችን እና ምንነታቸውን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት አስቸጋሪ አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

ሆኖም በምልከታ ያላገኛቸውን መረጃዎች በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት በመሰብሰብ የሚከተሉት የምርምር ግኝቶች ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

## 5.2 የምርምር ግኝቶች

1. **በህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ የሚከበሩ ክብረ በዓላት ከማህበረሰቡ የእምነትና የአምልኮ ስርዓት ጋር የሚያያዙ መሆናቸው፡-**

ማህበረሰቡ የህይወት ሽግግሮችን ምክንያት በማድረግ የሚከውናቸው ክብረ በዓላት ከሚከተለው የእምነት ስርዓት ጋር በእጅጉ የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህም ሲባል ልደትን፣ ጋብቻን እና ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚከበሩ በዓላት ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ዶግማ እና ቀኖና ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ወንድና ሴት ህጻናት ክርስትና የሚነሱበት ቀን መለያየትን ስንመለከት ወደ አዳም እና ሄዋን ታሪክ ይወስደናል፡፡ የጋብቻ ስነ-ስርዓት መነሻ ስንመለከት እንዲሁ ወደ አብረሃም እና ሳር ህይወት ይመራናል፤ እንዲሁም የለቅሶ እና ተዝካር ስነ-ስርዓቶች መፈጸም ዋና ምክንያት ነፍስ ከአምላክ ጋር እንድትኖር ሲባል መሆኑ ከአምልኮ ስርዓታቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያሳያሉ፡፡

2. **የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ከማህበረሰቡ መልካም እሴቶች ጋር የተቆራኙ መሆናቸው፡፡**

ግለትም ማህበረሰቡ የህይወት ሽግግሮችን ምክንያት በማድረግ የሚፈጽማቸው ክብረ በዓላት እና ከክብረ በዓላቱ ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ስነ-ቃላዊ አገላለጾች ከማህበረሰቡ መልካም እሴቶች ጋር በእጅጉ የተያያዙ ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ መልካም እሴቶች የሚላቸው ሃይማኖተኛነት፣ ጀግንነት፣ ፍቅር፣ ታታሪነት፣ ሀገር ወዳድነት ተደጋግመው የሚገልጹ መሆናቸው ይህንን ያሳያል፡፡

3. **የህይወት ዘመን ሽግግር ደረጃዎች ከበራ የማህበረሰቡን የእርስ በርስ ግንኙነት ማጠንከሪያ መሆናቸው፡፡**

ማህበረሰቡ ልደትን፣ ክርስትናን፣ ጋብቻን እና ሞትን ምክንያት በማድረግ የሚፈጽማቸው ከበራዎች የሚከወኑት በህብረት ወይም በጋራ መሆኑ በመካከላቸው ያለው የእርስ በርስ ትስስር እንዲጎለብት ከማድረጉም ባሻገር ደስታን፣ ሀዘንን እንዲሁም ችግርን በጋራ እንዲካፈሉ ማድረግ እንዳስቻለ አሳይቷል፡፡

4. **የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ከበራዎች ማህበረሰቡ ለህይወት ሽግግሮች ያለውን አመለካከት መግለጫዎች መሆናቸው፡፡**

በህይወት ሽግግሮች ከበራ ላይ ማህበረሰቡ ለልደት፣ ለሰርግና ለሞት ያለውን አመለካከት መረዳት አስችሏል፡፡ በልደት አከባበር ላይ የሚቀርቡ ምርቃቶች ለአቅመ ኃብቻ እንዲደርስ፣ በዘመኑ የተወደደ፣ የተከበረና የተሳካለት እንዲሆን የሚገልጹ ናቸው፡፡

እንዲሁም ሰርግ የትውልድ፣ የዘር ማስቀጠያ መሆኑን በአፈጻጸማቸው ጊዜ በሚጠቀሙባቸው ትዕምርቶች፣ ቃል ግጥሞችና ምርቃቶች ይገልጻሉ፡፡ የሰርግ ምርቃቶች ሙሉ በሙሉ ባለትዳሮች ወደፊት በሚወልዷቸው ልጆች ላይ ያነጣጥራል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የእነሱ ትዳር መመስረት ዘር ለመተካት መነሻ መሆኑን ነው፡፡

ምርምሩ ሞት ለማህበረሰቡ ከአለም በስጋ መለየት እንጅ ህይወት በሌላ ዘላለማዊና ሰማያዊ አለም ይቀጥላል ብለው የሚያምኑ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ በቃል ግጥሞቻቸው፣ በምርቃቶቻቸው የሚያስተላልፏቸው መለእክቶች እና ከሞት በኋላ የሚከናወኑ ተዝካሮች ህይወት ቀጣይ እንደሆነች የሚያሳዩባቸው ተግባራት ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወደ ተደሙ ዘመዶቻቸው የሚሄዱበት ነው ብለው የሚያምኑ መሆናቸውን አስገንዝቧል፡፡

5. **የህይወት ዘመን ዑደት ደረጃዎች ክብረ በዓል ማህበረሰቡ ግላዊ ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ማሳያ መሆናቸው፡፡**

ማህበረሰቡ በክርስትና፣ በሰርግና በሞት ዙሪያ በሚያከብራቸው ክብረ በዓላት ከማህበሩ አባላት የሚለይበትን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ደረጃ እንደማሳያ ይጠቀምባቸዋል፡፡ ክርስትና የህጻኑ ግላዊ ማንነት የሚጀምርበት ሲሆን ቤተሰቦቹ ደግሞ ማንነታቸውን የሚያድሱበት እና የሚያጠነክሩበት ነው፣ የሰርግ ስነ-ስርዓት የሙሽሮች ቤተሰቦች ሲተጫጩ የሚከተሉት የመደብ ምርጫ እና በሰርጉ ቀናት የሚደግሱት ድግስ ማህበራዊ ደረጃቸውን የሚገልጹባቸው ናቸው፣ እንዲሁም በሞት ጊዜ በሚከወኑ ስርዓቶች፣ የአገናነዝ ስርዓት፣ የቀብር ቦታ፣ የፍታት ስርዓት፣ የአለቃቀስ ስርዓቶች መለያየት መሰረት የሚችና የቤተሰቦቹን ማንነትና ማህበራዊ ደረጃ ማሳያዎች ናቸው፡፡

6. የህይወት ዘመን ሽግግር ደረጃዎች ክብረ በዓላት ማህበረሰቡ ስነ-ልቦናዊ እርካታ የሚያገኙባቸው መሆናቸው፡፡

ማህበረሰቡ ልጁን ክርስትና ስላስነሳ፣ ልጁን ስለዳረ፣ ስለቆረበ፣ ስለመነኮሰ፣ ተዝካር ስለደገሰ፣ ወዳጁን አልቅሶ ስለቀበረ ከሚያሳስቡትና ከሚያስጨንቁት ጉዳዮች ይገላገላል፡፡ በመሆኑም በእነዚህ የህይወት ሽግግሮች ምክንያት በማድረግ የሚከበሩ ሃይማኖት ሰራሽ እና ባህል ሰራሽ ክብረ በዓላት ማህበረሰቡ ስነ- ልቦናዊ እርካታ ያገኛል፡፡

## 5.3 የምርምር ግኝቶች ጠቀሜታ

ከላይ የተዘረዘሩት የምርምር ግኝቶች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

1. በህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ዙሪያ ሰፊና ጥልቅ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልግ ተመራማሪ እንደ መነሻ ይሆናሉ፡፡
2. በፍኖተ ሰላም አካባቢ የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ምን እንደሆኑ፣ እንዴት እንደሚከበሩ፣ በስነ-ቃል አማካኝነት እንዴት እንደሚገለጹ ያስተዋውቃል፡፡
3. በፍኖተ ሰላም አካባቢ በልደት፣ በሰርግና በለቅሶ አከባበር ጊዜ የሚስተዋሉ ባህላዊ እንጓለጾች ከነክዋኔያቸው ምን ገጽታ እንዳላቸው ሰንዶ ለተተኪው ትውልድ የማስተላለፍ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡
4. የፍኖተ ሰላምን አካባቢ ማህበረሰብ ለማወቅና እውቀቱን ለመረዳት፣ ለመተርጎም የሚያስችል ሃይማኖታዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና ስነ-ማህበረሰባዊ ምርምር ለማካሄድ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


መልስ ሙሉጌታ፡፡ "ባህላዊ የወሊድና የገለብ ስነ-ስርዓት ፎክሎራዊ ገጽታ በአክሱም ከተማ የክርስትና እምነት ተከታዮች" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 2002 ዓ.ም፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡

የኔአሳብ የሰራሁ፡፡ "የቆሎ ተማሪዎች ፎክሎራዊ እይታ በፍኖተ ሰላም አካባቢ." አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 2002 ዓ.ም፡፡

Alemayehu Belay. "The Rites of Passage in the Sidama Society." Sociology and and Social Administration, Un Published BA Thesis, 1991.

Almaz Ejerso. "The Rites of Passage of Oromo People in Seyyo District of Qellem." Applied Sociology, Un Published BA Thesis, 1986.

Ayele Lire. "The Rites of Passage Among Hadya Ethnic Group," Applied Sociology, Un Published BA Thesis, 1986.

Bascom, William R. Four Functions of Folklore. *Journal of American Folklore*. 67:333- 349. 1954

Bauman, Richard. *The Field Study of Folklore in Context*. In Handbook of American Folklore, Richard Dorson, Bloomington: Indian University Press, 1983; 362-368. .

Bauman, Richard and Charles, Brigs L. "Poetics and Performance As Critical Perspective on Language and Social Life." *Annual Review Of Anthropology*;vol19, (1990), pp59-88

Bell, Catherine. *Ritual Perspectives and Dimensions*. New York: Oxford University Press, 1997.

Ben-Amos, Dan, "Context in Context." *Westeren Folklore*, vol, 52, no214, 1993, PP 209-226.

David, Gray. E. *Doing Research in the Real World* . Sage Publications London. Thousand- Oaks New Delhi, 2004.

Flick, Owe. *An Introduction to Qualitative Research.* Sage publication. Los Angles, London, New Delhi, Singapore, 2007.

Goldstein, Kenneth S. *A Guide for Field Workers in Folklore.* Hatboro, Pa.: Folklore Associates for the American Folklore Society, 1964.

Grimes, Ronald L. *Deeply into the Bone Re-Inventing Rites of Passage.* Berkeley Los Angeles London: University of California Pres;1943.

Hill, Jeff and Peggy, Daniels. *Life Events and Rites of Passage.* Clifton D.Bryant, Professor, Virginia Tech University, 2008.

Mazama, Ama and Molefi Kete Asante. *Encyclopedia of African Religion* (Eds).

Sage Publications.Inc, 2009.

McCormick, Charlie T. and Kim Kennedy, White (Eds). *Folklore An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art.* (Second Edition). ABC-CLIO, LLC, 2011.

Myrvold, Kristina. *Inside the Gurus Gate Ritual Uses Text Among the Skins in Varanasi.* Sweden: University Lund, 2007.

Rappaport, Roy A. *Ritual and Religion in the Marking of Hummanity.* Cambrige

University press, 1999.

Salamone, Frank A. (Editor) *Encyclopedia of Rites, Rituals and Festivals.* London: Routledge New York, 2004.

Schensul, Jean and Margaret D. Lecompte. *Enhanced Ethinographic Methodes.* University of Colorado. Boulder, 2009.

Schechner, Richard. *Performance Theory.* London and New York: Routledge Classics, 2003.

Scoot, Vandaerstoep W. and Deirdre, Johnston D. *Research Method for Every Day Life.* Jossy Bass, Sanfransisco, 2009.

Van Gennep, Arnold. *The Rites of Passage.* Trans. M. B. Vizedom and G. L. Caffee. Chicago: University of Chicago Press, 1960.

# አባሪዎች

## ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው ወደዚች አለም ሲመጣ ጀምሮ እስከሚለይ ድረስ በምን በምን ገጠመኞች ውስጥ ያልፋል? (ሰው የሆነን ሁሉ የሚያጠቃልሉ ሁነቶች) ድግስ የሚደገስባቸው አጋጣሚዎችን ቢነግሩኝ?

### 1.1. ልደትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

2. እንዴት እናት ስታረግዝ ምን ማድረግ አለባት? ምንስ ይደረግላታል?
3. የመውለጃ ጊዜዋ ሲቃረብ ምን ማድረግ አለባት?
4. በምጥ ጊዜ ምን ይረግላታል? ምንስ ይባላል?
5. ማን(ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ጓደኛ፣ ወዘተ.) ምጀመሪያ ይነገረዋል? ለምን?
6. ማን በዋናነት ያዋልዳል ለምን?
7. ምን ይደረጋል(ምጡ እንዴቀል?) ለምን?
8. ስትገላገል ምን ይባላል? ወንድ ሴት ተመሳሳይ ነው ወይስ የተለያየ?
9. ምን ይበላል? ለምን?
10. እስከ ስንት ቀን ይንከባከቧታል? ለምን? በስንተኛው ቀን ትነሳለች? ለምን?
11. ህጻኑ ወንድ ከሆነ በስንተኛው ቀን ይገረዛል? ለምን?
12. ክርስትና የሚነሱት በስንተኛው ቀን ነው? ለምን? ምን ምን ድርጊቶችስ ይከናወናሉ?

### 1.2. ጋብቻን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

1. ሰው ልጁን ሲድር ለምን ድግስ ይደግሳል?
2. የሰርጉ ስነ ስረአት እስከ ስንት ቀን ሊዘልቅ ይችላል?
3. ከሴቷ ቤትን ከወንዱ ቤት ተመሳሳይ ድግስ ነው የሚደገሰው?
4. ሙሽሮቹ ከሰርጉ ቀን በፊት የሚደረግላቸው የተለየ ነገር ይኖር ይሆን?
5. በሰርጉ ቀን ማን ወደ ማን ይሄዳል? ምን ይዘው? ምንስ እያሉ? ለምን?
6. ሙሽራዋ ቤት ምን አይነት አቀባበል ይደረግላቸዋል?
7. የተለየ ምግብ ነው የሚቀርብላቸው?
8. በስንት ሰአት ሙሽራዋን ይዘው ይወጣሉ? ምንስ እየተባለ ይሸኛሉ?
9. ሚዜዎቻቸው ምን አይነት ጊዜ ያሳልፋሉ?
10. መልስ በስንተኛው ቀን ይጠራሉ?
11. እስከ ስንተኛው ቀን ድግሱ ይቀጥላል?
12. ሰዎች ያለ ድግስ በያገቡ ምን ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል

### 1.3. ሞትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

1. ሰው ሞትን ምን እያደረገ ይጠብቀዋል?

2. እንደሚሞትት ሲያውቀው ምን ያደርጋል? ከማን ጋር?
3. ሲሞት ምን ይደረጋል? አስከሬኑን ምን ያደርጉታል?
4. ለተለያዩ ሰውች(ህጻን፣ ሽማግሌ፣ ሴት፣ ወንድ፣ ቄስ፣ ጨዋ፣ ጀግና፣ ተራ፣ ሌባ...)የተለያየ የአገናነዝ፣ የፍታት፣ የቀብር፣ የወይታ ... ስርዓት አለ ወይስ ተመሳሳይ ነው?
5. ሟች መሞቱ በቅድሚያ ለማን ይነገራል? ምን ተብሎ? ለምን?
6. ሰው ወደ ለቅሶ ቤት ሲገባ ምን እያለ ነው ሲዎጣስ?
7. በስንት ሰአት ህይወቱ ያለፈ በዕለቱ ይቀበራል/ ያድራል?
8. የት ይቀበራል? ለምን?
9. አስከሬኑ ወደ ቀብር ከመሄዱ በፊት ምን ይደረጋል?
10. በስንት ሰአት ወደ ቀብር ይሄዳል?
11. ቀብር ቦታ ምን ምን ድርጊቶች ይከናወናሉ? (ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜ፣ ከቀብር በኋላ)
12. የተለያዩ ሰዎች በተለያየ ቦታ ነው የሚቀበሩት? ለምን?
13. ለስንት ቀናት ይለቀሳል? ለምን? የቦታ እና የአቅጣጫ ለውጥ አለ?
14. ሃዘንተኞች የሚለብሱት የተለየ ልብስ አለ? ለምን? እስከ ስንት ቀን ይለሳሉ?
15. ከሞት በኋላ በስንት በስንተኛው ቀን ይዘከራል? ለምን? የምን ተምሳሌት ነው?

### 1.4.ጠቅላላ ጥያቄዎች

1. ሰው በተረትና ምሳሌው አማካኝነት እንዴት ብሎ ይገልጻቸዋል?
2. ሰው ደስ ብሎት የሚያከናውነው የቱን ነው፣ በመከፋትስ?

### ለቤተ ክህነት ሰዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. እንዷት እናት ምጥ ሲይዛት የሚደረጉላት እንክብካቤዎች ከእምነታቸው ጋር የሚያያዝበት መንገድ ይኖር ይሆን?
2. እናቶች ሲወልዱ ረዳትና አገላጋይ ድንግል ማርያም ናት ለምንድን ነው? የተሰጣት ቃልኪዳን አለ?
3. ልጆች በተወለዱ በሰባት ቀናቸው ይገረዛሉ ለምን ይሄ ቀን ተመረጠ ባይገረዙስ ምን ይሆናሉ?
4. ልጆች ክርስትና ሲነሱ የሚከናወኑ ነገሮችን ቢነግሩኝ? ክርስትና ባይነሱ ምን ይሆናሉ? ቅባ ቅዱስ፣ ማተብ፣ ጥምቀቱ፣ እና ሌሎች ክንውኖች የምን ምልክት ናቸው? ለምንስ ይፈጸማሉ?
5. በሰርግ ጊዜ የሚከናወኑ ድርጊቶች ሀይማኖታዊ ናቸው ወይስ ባህላዊ የትኛው ያመዝናል?
6. ሰው እርጅና ሲቃረብ፣ ሞት ሲመጣ ይቆርባል፣ የመነኩሳል፣ ይናዘዛል፣ ለምንድን ነው እንዲህ የሚያደርጉት?

7. ሰው ሲሞት በነጭ ክር ነው የሚገነዘው ለምንድን ነው የአገናነዝ ስርዓቱ ለሁሉም(ለሴት፣ ለወንድ፣ ለቄስ፣ ለጨዋ፣ ለዲያቆን፣ ለሽማግሌ) ተመሳሳይ ነው?
8. የሚከፈነውም በሰሌን ነው ይህስ የተለየ ትርጉም አለው?
9. የአቀባበር ስርዓቱስ የተለየ ነው?
10. ፍታት ማለት ምን ማለት ነው የሚፈታላቸው ለምንድን ነው ለሁሉም ሰው ነው የሚፈታው?
11. ከቀብር በኋላ በተለያዩ ቀኖች ይዘከርለታል እነዚህ ቀኖች የተመረጡበት ምክንያት ምንድን ነው? ከመቃብሩ ላይስ ደም የሚፈሰው ለምንድን ነው?
12. የሟች ነፍስ ምን እንዳትሆን ነው በምድር የሚከናወንላቸው?
13. የቁም ተስካር ምንድን ነው እንዴትስ ይከናወናል?

## የልደትና ክርስትና ምርቃቶች

1. ለእትመ አዳም (ለእትመ ሄዋን) ያድርሰው (ያድርሳት)፣
2. በሰርጉ (በሰርጓ) እንብላ፣
3. ሃይማኖቱ የጸና ምግባሩ የቀና ይሁን፣
4. ወንዝ እሚያሳፍር አገር እሚያስከብር ይሁን፣
5. ለጠላቱ እሚመክት ለወዳጁ እሚፈተፍት ይሁን፣

## የሰርግ ቃል ግጥሞች

1. እንዳላይህ፣

   ዳመናው ጣለ በላይህ፡፡

2. ካባ ልበስ ምንድነው ልበስ ምንድነው፣

   ሞትና ሰርግ አንድ ነው ልበስ ምንድነው፡፡

3. ሙሽር አበባ፣

   አይዞህ ልብህ አይባባ፡፡

4. ሎሚ ጣልባት በደረቷ፣

   የጨዋ ልጅ ናት መሰረቷ፡፡

5. እያ ንሳ ንሳ፣

   እንዳታበላት ዳጉሳ፡፡

6. የሙሽሪት እናት በላይ ይቀመጡ፣
የሙሽሪት አባት በላይ ይቀመጡ፣
አሳድገዋታል እየቆነጠጡ፡፡
7. ሙሽር አበባ፣
በጊዜ ይዘሃት ግባ፡፡
8. ልካለች ልካለች ሙሽሪት ልካለች፣
የጉችማው ቅቤ አይቀርም ብላለች፡፡
9. ውሃ በብርሌ ኀልታ ሄዳለች፣

አትቀርም ሙሽሪት እሙች ብላኛለች፡፡
10. ሙሽራው ባንድ እሊጋ፣
ሙሽሪት ባንድ እሊጋ፣
ይመስላሉ መልዓክ ከንፉን የዘረጋ፡፡
11. የሙሽራው (የሙሽሪት) አባት የስንዴ ክምር፣
እንዴት አማረበት እገሌን ሲድር፡፡
12. ሙሽር መኮንን፣
እንዳታበላት ኀመን፡፡
13. እሽ ሩሩ በላት ባሊጋ፣
ገና ህጻን ናት ገና ሊጋ፡፡

## የሰርግ ምርቃቶች

1. ለጠላቱ እሚመክት ለወዳጁ እሚፈተፍት ይሁን፣
2. ወንድ ወልዳችሁ ለፈረስ፣ ሴት ወልዳችሁ ለበርኖስ አድርሱ፣
3. አስራ አምስት ውለዱ፣ አምስቱ ለፈረስ፣ አምስቱ ለመቅደስ፣ አምስቱ ለበርኖስ ይሁኑ፡፡
4. አጥር ቆስቋሽ ነገር አመላላሽ አያድርግሽ፣
5 . በወንድ ልጅ ተበከሪ፣
6. የምትወልዱት ልጅ መንፈሳዊ ቢሆን እንደ እንጦስ እንደ መቃርስ፣ ስጋዊ ቢሆን እንደ ቆስጠንጢኖስ እንደ እኖሬዎስ ይሁን፣

## የለቅሶ ቃል ግጥሞች

1. የሰው ሁላ ቤቱ ሻጣው ይመዘዛል፣
   ኧረ ይህ ካህንስ ምሰሶው ይጎዛል፡፡
2. አሰለፍ ናት እንጅ ና ብላ ና ብላ፣
   አፈር እንደ እንጀራ ሊበላ ነው ብላ፡፡
3. እንደነ ጊዮርጊስ እንደነ ተክልዬ ታቦት መሆን ትቶ፣
   አፈር ሊያለብሱት ነው ሰው ሁኖ ተገኝቶ፡፡
4. እስኪ እኛ ዝም በሉ ይጮሃል በአፋፉ፣
   እኒህ ልማደኞች ዛሬም ተዘረፉ፡፡
5. በሮቹ ጥቋቁር ገበሬው ደንቆሮ፣
   አይናገርም ወይ ዘር አለቀ ብሎ፡፡
6. እንደ አባይ ደንበሌ እንደ ሀምሌ ሙላት እንደ ትሳስ ምርት፣
   እንደዚያ ነበረ ጌታ የእንተ ቤት፡፡
7. ሞሰቡ ይህ አይደለም የበላንበቱ፣
   ዋንጫው ይህ አይደለም የጠጣንበቱ፣
   ያማ ትልቅ ነበር እንደባለቤቱ፡፡
8. የተወለደ እለት የታጠቀው ቁምጣ፣
   ትላንትና ማታ ሸምቀቁ ተፈታ፡፡
9. በሮች ወይፈናፍን መሬቱ ዳገት፣
   ትሻል ነበር አዝሜ ተው ተው ለማለት፡፡
10. አብየ ጠባይህን ስጠው ለቀሪ ሰው፣
    እንዳንተ ለማይሞት ለማይበሰብሰው፡፡

## ለቅሶ እና ተዝካር ላይ የሚቀርቡ ምርቃቶች

1. ሞት ለፎ ድንጋይ ገርፎ፣
2. የሞት በደለኛ አይያዝ በዳኛ፣

3. ሞት አይለመድ፣ ጎሽ አይጠመድ፣ ሎርቃ አይታጨድ፣

4. ብልህ ሲሞት ልቡን ንጉስ ሲሞት ግንቡን ውረስ፣

5. ሲሞት ሲተካ ሲፈጭ ሲቦካ፣

6. ሞት በአቤል ተዝካር በሮቤል ተጀምሯል፣ የነበረ፣ የሚኖር ነው፡፡

7. ነፍሱን ይማረው እጥቁን ያለምልመው፣

8. ነፍሱን ከነ አብረሃም ከነ ያዕቆብ አጠገብ ያሳርፍልን፣

9. ከተዋቃሽ መልዓክ ይማርልን እየተባለ ይመረቃል፡፡

# የፎቶግራፍ አባሪዎች



ሙሽሮች የተዘጋጀላቸው ዳውጃ ላይ ተቀምጠው



ሙሽራዋ በአሳዳሪ ታዝላ ስትወጣ



ፍታት ስነ-ስርዓት



ሙሽራው ሲወጣ የሚደረግ ባህላዊ ክዋኔ





የወንድ ሚዜዎች ሽማግሌ ፊት ተርበው ሲጠየቁ

ሳዳሪ ከሚዜዎች የተረከባቸውን አልባሳት ለሴት ቤተሰብ ቆጥሮ
ያስረክብ